ክፉ ይሆናል:: ሰይጣን ራሱ መንገዱን ይመራል:: ነገር ግን በእርሱና በእነርሱ ላይየሚወርደው ፍርድ በሌሎቹ ላይ ከወረደው የከፋ ይሆናል:: በዚህ የዓለም ታሪክ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፣ ምክንያቱም የጎግና የማጎግ ጦርነት የሰው ዘር ድጋፍ ሲገኝ እንደማይችል ያረጋግጣል:: በ1000 የበረከት ዓመታት ጊዜ የሰው ዘር ኃጢአተኛ በመሆን ይቀጥላል (ይቆያል):: እግዚአብሔር ዓለምን በእሳት በማጥፋት አዲስ የከበረ ዓለም በመፍጠር ከሰው ጋር ያሰውን የመጨረሻውን ግቦች የሚፈጽመው በዚህ መንገድ ብቻ ነው:: ይህን አዲሱን ዓለም የሚፈጥረው

«እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ!» ባለው መሰረት ነው::





የሦስቱ የዋናዎቹ መዋጀት መያያዝ የጋራ ግብ

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

በመጀመሪያው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ሶስት ሕዝቦችን ለይቶ ማሳየቱን አግኝተናል:: (*1ቆሮ.10:31-32*) እነርሱም:-

1. የዓለም ሕዝቦች (አሕዛብ)

2. የእስራኤል ሕዝብ

3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እነዚህ ሦስት ሕዝቦች በሦስት ወፋፍራም መስመሮች፣ እያንዳንዱ የራሱን ዓላማ በመያዝ እንደሚሄድ ተመልክተዋል:: ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉም በዓለም ወደማይናወጠው ሁኔታና የደህንነት ታሪክ ያመራሉ:: እርሱም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: ይህም ሰው ቢገነዘበውም ባይገነዘበውም ይሆናል::

የሦስቱን የዋናዎቹን የመዋጀት ታሪክ መያያዝ ስናጠና ሦስት አመለካከቶች እንዳሉ ልንረዳ ያሻል:: ይኸውም:-


1. አህዛብ እንደሚዋረዱ (ዝቅ እንደሚሉ)

2. የእስራኤል ሕዝብ ከፍ እንደሚሉ

3. የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ (መንግሥተ ሰማይ) እንደምትሔድ::

እነዚህ ሦስቱ ሕዝቦች ከሚመጣው ንጉስ (ከጌታ ኢየሱስ) ታሪክ ጋር የሚያያዙት እንዴት ነው? በዚህ ጥያቄ ላይ እንወያያለን:: ቅርብ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ስላለው ስለ ራሳችን አቋም እንደገና ለመመርመር እድል ይኖረናል::

በመጀመሪያ የክርስቶስ ዳግም መምጣት የአንድ ጊዜ ሁኔታ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል:: ጌታ የሚመለሰው በመደጋገም ብዙ ጊዜ ሳይሆን አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: ስለዚህ እውነት ያለው አንድ ነገር ቢኖር የክርስቶስ ዳግም መምጣት በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ የተለየ ውጤት ስላለው ነው በጊዜው እያንዳንዱ ግለሰብ ከእነዚህ ከሦስቱ ሕዝቦች በየትኛው ውስጥ መገኘቱን እናያለን:: ይህ ጥያቄ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን ሁኔታና የዘላለም ደህንነቱን እንዲወስን ያደርገዋል:: ያ! ሕዝብ የክርስቶስን ዳግም መምጣት በተለያዩ መንገድ መገናኘቱን በቀላሉ ለመግለጽ የሚቻለው ከራሱ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ነው:: እያንዳንዳችን ከሌላው ሕዝብ ጋር በተለያየ መንገድ ግንኙነት ያለን ግለሰቦች ነን:: ለምሳሌ ያገባ ሰው ለሚስቱ ባል ብቻ ሳይሆን ለልጆች አባት፣ ለወላጆቹ ልጅ፣በአጠገቡ ለሚኖሩት ጎረቤት አብረውት ከሚሠሩት ጋር የሥራ ባልደረባ ነው:: የክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት አንድ ጊዜ የሚሆን ሁኔታ ነው:: ነገር ግን በተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች ላይ የተለያዩ ውጤቶች ይኖረዋል:: ለአሕዛብ፣ ለእስራኤል ሕዝብ፣ ለቤተክርስቲያኑ ይመጣል:: ነገር ግን ሁሉም በተለየ መንገድ ይያዛሉ::








በእርግጥ የክርስቶስ መምጣት ዋናው ትዕይንት ነው:: የዓለም ታሪክ በሙሉና የደህንነት ታሪክ ወደ አንድ ሁኔታ ብቻ እያመራ ነው:እርሱም ይህን ዓለም ወደሚፈጽመው ወደ ክርስቶስ ነው:: አሳዛኙ ነገር አብዛኛውን የዚህ ዓለም ሕዝብ ይህን እየተጠባበቁት አይደለም:: ይህን ታላቅ ሁኔታ ምን ማለት እንደሆነ በበለጠ በግልጽ መረዳትየሚያስፈልገን ስለዚህ ነው:: በደህንነት "ታሪክ"ቻርት ላይ የጌታ መመለስ በቅደም ተከተል የተመለከተ ነው:: የክርስቶስ ዳግም መምጣት የሚጀምረው ለራሱ ስለሆነው ሕዝብ ነው:: በደሙ የተገዙ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና ወደ ሰማያዊ ክብር ይወሰዳሉ::ከዚህ በኋላ ጌታ ከሕዝቡ ጋር በዓመጸኛው ሕዝብ ላይ ሊፈርድ፣የእስራኤልን ሕዝብ ለማዳንና የመሲሁንየሰላም መንግስት ለማነገስ (ለመመስረት) ይመጣል:: አሁን ከላይ እንደተጠቀሰው የክርስቶስን ዳግም መምጣት በቅደም ተከተል እንመለከታለን::

## 1. ጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ መመለሱ

ዳግም ለተወለዱት አማኞች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሙሽራቸው በመሆን ይገለጣል:: «በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንበመንግስተ ሰማይ እንደ በጉ ሚስት ሆና ትታያለች»:: ራስዋን ስላዘጋጀች «ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ ዕግር ልብስ» እንድትጎናጸፍ ተሰጣት:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ይህ የተጣራው ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ እንደሆነ ተገልጿል:: *(ራዕ.19:7-8፣ 1ቆሮ.1:31)*:: ይህ ዳግም የተወለዱ አማኞች ምልክት ነው:: በመቀጠል መጽሐፍ በሰማይ ስለሚከናወነው «የበጉ ሰርግ» ይናገራል::የበጉ ሰርግ በታላቅ ሲነገር የማይቻል የደስታ ጊዜ ይሆናል::*(ራዕ.19:7-9)*

ይህ ታሪክ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ ያለውን የማይደመሰሰውን ሕይወት የሚገልጽ ነው:: በሌሎቹ ነገሮች መካከል በወንድና በሴት መካከል ያለው ጋብቻ ታላቅ ሚስጥር እንዳለው ጽፏል:: ከዚህ ሚስጢር በስተጀርባ ጋብቻ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ ስላለው ከፍተኛ ሚስጢር ይናገራል *(ኤፌ.5:31-32)*:: ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ዳግም የተወለዱት አማኞች ከጌታ ኢየሱስ ሙሽራ ጋር ለዘላለም አንድነት እንዳላቸው ይገልጽልናል::

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ሙሽራውን (ቤተ ክርስቲያኑን) ወደ ሰማያዊ ቤቷ ሊወስድ የሚመጣበትን ሁኔታ «መነጠቅ» በሚል ሀሳብ ይገልጸዋል::

*«ጌታ ራሱ በትዕዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምጽ፣ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ:: ከዚያን በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን» (1ተሰ.4:16-17)*

ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት አንድ ቀን እንደገና ተመልሶ እንደሚመጣ ለደቀ መዛሙርቱ ነገሯቸዋል:: የሚከተለውን አስደናቂ ተስፋ ሰጥቷቸዋል::

*«በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሔዳለሁ፣ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ፣ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ.14:2-3)::*

ጌታ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ ማንኛውም አማኝ አያውቀውም:: ምክንቱም አብ በስልጣኑ ለራሱ ብቻ ስለያዘው (ስለጠበቀው) ነው (ማቴ.24:36::) ነገር ግን ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ «የተባረከውን ተስፋ» (ቆላ.1:27):: በልቡ የጠበቀ አንድ ምኞት ብቻ ይኖረዋል፣ ይኸውም ከጌታ ጋር ለመኖርና ወደ ቤቱ የመሄድ ምኞት ነው::


ለ2000 ዓመታት የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ለዚህ ለተባረከው ጊዜ ራሳቸውን ሲያዘጋጁ ቆይተዋል:: ከጌታቸው መመለስ በስተቀር ሌላ በናፍቆት (በጉጉት) የሚጠብቁት የላቸውም:: መቅረዛቸውን በዘይት ሞልተው ሙሽራውን ለመቀበል ይወጣሉ (ማቴ.25:1-13):: ልባቸው «ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን» የሚሻ ነው:: ምክንያቱም «ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና» (ቆላ.3:1-3):: ዓለምን የካዱና ምንም ነገር ከቶ ከክርስቶስ እንደማይለያቸው ሆነው በክርስቶስ ላይ የተጠማጠሙ ስለሆኑ ይህ ነገር ብቻ ወደ ግባቸው ይመራቸዋል (ያደርሳቸዋል) (ፊል.3:14):: ጌታ ይህን ተስፋ ከቶ አያስቀረውም::

በጥንቱ የግሪክ ትርጉም (1ቆሮ.15:52) ኢን አቶሞ (ስቃ ሮቋቄቂቂ) «በአንድ አቶም» ነው በሚል የተጻፈ ነው:: ጌታ ሲመጣ በቅጽበት ዓይን ከእርሱ ጋር ይሆናሉ:: የግሪኩ ቃል አቶሞስ (ሮቋቄቂቂቋ) የሚለው ቃል ፍቺው ሊከፋፈል የማይቻል አጭር ጊዜ ማለት ነው:: መነጠቅ በጊዜ ሊመጠን በማይቻል ቅጽበታዊ ጊዜ የሚሆን ነው:: በዚህ ጊዜ በምድር ላይ ያሉት ያልሞቱት አማኞች «አንቀላፍተው ያሉትን» አይቀድሟቸውም:: (1ተሰ.4:15) ይህ ጥቅስ ጌታ ኢየሱስ





ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በምድር ሳይሆን በአየር ላይ እንደሚገናኛት ያስተምረናል:: በደህንነት ታሪክ ላይ ያለው ሥዕላዊ ቻርት «በአየር ላይ የመገናኛ ቦታ» በማለት ያመለክተዋል:: (1ተሰ.4:17) በዚህ ነጥብ ላይ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚወጣው አረንጓዴ መስመር (የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን) ወደ ታች ዝቅ እያለ ከሚወርደው ቡናማ መስመር (የእግዚአብሔር ልጅ) ጋር ይገናኛል:: ከዚያ ቦታ ለዘላለም የተገናኙ ይሆናሉ:: ይሄ ነገር ሲከናወን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያሉት አማኞች ከግባቸው የደረሱ ይሆናሉ:: በሰማያዊው አባታቸው ቤት ይገባሉ፣ በዚያም «ለዘላለም ከጌታ ጋር» ይሆናሉ (1ተሰ.4:17):: ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ የኃጢአት ዋጋ የሆነውን የሞት ዕዳ ስለ ከፈለላቸው እንዳቸውም አይፈረድባቸውም:: (ዮሐ.5:24) በታላቁ አስቃቂ በሆነው የመከራ ዘመን ውስጥ አያልፉም:: ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው ያ ጊዜ በዓመጸኛው ሕዝብ ላይ የሚወርደው ፍርድ ስለሆነ ነው:: ሊመጣ ካለው መከራ ያመለጡ ይሆናሉ:: (1ተሰ.1:10) ስለሆነም የክርስቶስ ኢየሱስ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ ትሔዳለች:: በምድር ላይ ያለው አስቃቂ ፍርድ ሳይሆን የሚጠብቃት ሰማያዊ ክብር ነው::



## 2. የኢየሱስ ክርስቶስ ለአህዛብ መመለስ፡-

ጌታ ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ የእግዚአብሔርን ልጅ (እርሱን) እውነተኛውን መሲህ በተቃወሙትና በእርሱ ምትክ የክርስቶስን ተቃዋሚ በተቀበሉና ባልዳኑት ሕዝቦች ላይ ፈራጅ በመሆን ይገለጣል፡፡ የራዕይ መጽሐፍ የሚመጣውን ጌታ *«የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን»* ፍርድ የሚፈጽም አድርጎ ይገልጸዋል (*ራዕ. 19:15*)፡፡ በራዕ.16:14 ላይ ዮሐንስ ይህን ቀን *«ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን»* በማለት ገልጸዋል፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢያት *«የጌታ ቀን»* ብለው ጠርተውታል፡፡ ይህ ቀን በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞላ አስፈሪ ቀን ነው፡፡ ቀጥሎ የተጠቀሱት ይህንን ቀን ያመለክታሉ፡፡

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፣ አልቅሱ፣ ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ እንደሚመጣ ጥፋት ይመጣል» (ኢሳ.13:6)፡፡*

*«እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ፣ ኃጢአተኞችዋንም ከእርስዋ ዘንድ ሊያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል» (ኢሳ.13:9)፡፡*

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና ለቀኑ ወዮ! እርሱ ሁሉን ከሚችል ከአምላክ ዘንድ እንደ ጥፋት ይመጣል»* (*ኢዩ.1:15*)፡፡

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፣ እግዚአብሔር መስዋእትን ዘጋጅቶአልና፣ የጠራቸውንም ቀድሶአል፣ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ዝም በሉ»* (*ሶፎ.1:7*)፡፡

*«የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም»* (*አሞ.5:18*)፡፡

ፍርድ በእርግጥ ይመጣል፡፡ (በ*ሐሥ.17:31)* መሠረት እግዚአብሔር «ቀን ቀጥሮአል በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው» በዓለም ላይ ሊፈርድ የሚመጣው ይህ «ሰው» ማን ነው? መልሱ በዮሐንስ ወንጌል ይህ ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ልጅ በስተቀር ሌላ እንዳልሆነ «ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም» በማለት በግልፅ ተጽፏል (*ዮሐ.5:22*)፡፡





ጌታ ኢየሱስ በጠፉት በዓለም ሕዝቦች ላይ ሲፈርድ ተመልሶ ሲመጣ «በታላቁ ንጉሥ ከተማ» (ማቴ. 5:35) በኢየሩሳሌም የሚከናወን ይሆናል፡፡ ነቢዩ ዘካርያስ በመጽሐፉ «እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረዘይት ላይ ይቆማሉ» ብሏል፡፡ *(ዘካ.14:4)* ደቀ መዛሙርቱ ዓይን ፊት ወደ ሰማይ አርጎበት ወደ ነበረው ሥፍራ ይመለሳል (*የሐሥ.1:9-11)* ነገር ግን ከእርገቱ አንድ የተለየ ነገር አለ፡፡ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሆኖ ሲመጣ የአለሙ ፈራጅ ብቻውን አይደለም፡፡ ነገር ግን «በሰማይ ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉታል» ተብሎለታል፡፡ *(ማቴ.24:30፣ ራዕ.19:14)* ስለሆነም ጌታ ከቅዱሳኑ ጋር በዓለም ሊፈርድ ይመጣል፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ ደም የተዋጁ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው፡፡*(1ተሰ.3:13፣ ይሁዳ 14)* መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቦታ «ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ» (ከክርስቶስ ጋር) ይናገራል *(1ቆሮ.6:2)*፡፡

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ የክርስቶስ ዳግም መመለስ ወደታች በሚወርዱ መስመሮች በአረንጓዴና በቡናማ ቀለም የተመለከቱ ናቸው፡፡ ሁለቱ ቀለሞች የእግዚአብሔር ልጅ ከቅዱሳኑ ጋር በዓለም ሕዝቦች ሊፈርድ እንደሚመጣ ያመለክታሉ፡፡

በዚህ የፍርድ ጊዜ ልንመረምራቸው የሚያስፈልጉ ሁለት ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነርሱም ፡-

1. የአርማጌዶን ጦርነት
2. የሕዝብ መፈረድ ናቸው

### የአርማጌዶን ጦርነት

መጽሐፍ ቅዱስ *በራዕይ ምዕራፍ 16* ውስጥ አርማጌዶን ስለተባለው ቦታ ይናገራል *(ራዕ16:16)*፡፡ አርማጌዶን ማለት የሚጊዶን ተራራ ማለት ነው፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ሚጊዶን ወደ ተባለው ስፍራ ትኩረት እንድናደርግ ያደርገናል፡፡ ይህ ቦታ ከእስራኤል በስተ ሰሜናዊ ምስራቅ ባለው በኢዝርኤል ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ ነው *(1ኛነገ.9:15)* በዚህ ቦታ ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ በእግዚአብሔርና በሚመጣው ንጉስ በጌታ ኢየሱስ ላይ ያለው ጥላቻ ይካሄዳል፡፡ በቅርቡ በአርማጌዶን ላይ ከፍተኛ ፍርድ ይካሄዳል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ተቃዋሚ ከሚያመጣው የመከራ ዘመን ፍጻሜ ላይ ክፉ መናፍስት ከሰይጣን፣ ከክርስቶስ ተቃዋሚና ከሀሰተኛው ነቢይ ጋር በሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

*«ከዘንዶውም አፍ፣ ከአውሬውም አፍ፣ ከሀሰተኛውም ነቢይ አፍ፣ ጓጉንቸር የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ» (ራዕ.16:13)::*

እነዚህ መናፍስቶች በሰይጣን አታላይነት የክርስቲያን ተቃዋሚዎች ከሆኑት ብዙ ሠራዊትን ከዓለም ይሰበስባሉ::


*«ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፣ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያሰከትቷቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ» (ራዕ.16:14)::*

ታላቅ ሠራዊት ከዓለም በዚህ «ሁሉን በሚገዛው በታላቁ በእግዚአብሔር ቀን» ሕብረት አድርገው የመሰባሰባቸው እውነታ እግዚአብሔር ለርኩሳን መናፍስት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የሚፈቅድላቸው መሆኑን ያሳያል:: እግዚአብሔር ይህን መንገድ የመረጠበት ምክንያት የክርስቲያን ተቃዋሚ የሆኑትን የሕዝብ ብዛት በአንድነት ለመሰብሰብ (ለማከማቸት) ነው::

*«በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቱአቸው» (ራዕ.16:16)::*

ከዚህ ውጪት የተነሳ በቅድስቲቱ ምድር፣ በኢዝርኤል ውስጥ ባለው ሸለቆ እስራኤልን የሚወርር ታላቅ ሠራዊት ይከማቻል:: የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ፍርድ በግልጽ ይናገራል::

*«አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ:: በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ፡ መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቆችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባርሪያዎችንም፣ የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር እራት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ» (ራዕ 19:17-18)::*








ይህ ሠራዊት «በአምባላይ ፈረስ ላይ» ከሚቀመጠውና ከሠራዊቱ ጋር ጦርነት ለማድርግ ራሱን በሚያዘጋጀው በክርስቶስ ተቃዋሚ የሚመራ ይሆናል::

*«በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ» (ራዕ.19:19)::*

*በራዕይ 19:11* «በፈረስ ላይ» ተቀማጩ ማን እንደሆነ እናገኘዋለን::

*«ሰማይ ተከፍቶ አየሁ:: እነሆም አምባላይ ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል በጽድቅም ይፈርዳል፣ ይዋጋልም:: ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፣ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ:: ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው:: በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል፣ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል»* (ራዕ.19:11-13፤ ዮሐ. 1:1)::

ይህ ጥቅስ «በፈረስ ላይ የሚቀመጠው» መጪው ንጉስ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያል:: የሚከተሉት ሠራዊት «በሰማይም ያሉት ጭፍሮች» በመባል የተጠሩ ሲሆን «ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የለበሱ» ናቸው በመባል ተገልጸዋል *(ራዕ.19:14)*:: ቀደም ብለን እነዚህ ባሕርያት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ባሕርያት እንደሆኑ ተመልክተናል:: ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ለመፍረድ ይመጣል:: በአርማጌዶን የሰው ልጆች አመጸኝነትና በክርስቶስ ላይ ያለው ጥላቻው ጣሪያውን የመታ (የደረሰ) ይሆናል:: በክርስቶስ ተቃዋሚ መሪነት ብዙ ሠራዊት ከመላ ዓለም ከመጪው ጌታ ጋር ለመዋጋት ወደ ጦርነት ለመሔድ ይዘጋጃሉ:: ይህ ዕብደት ነው ብለን ልንገልጸው እንችላለን:: ሕዝቦች ለፍርድ መዘጋጀታቸው ግልጽ ነው:: የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ» (ራዕ. 19:16) ወደ አርማጌዶን ሜዳ ለፍርድ የሚመጣው ስለዚህ ነው::

*«አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል:: እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል:: እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል» (ራዕ. 19:15)::*

ከዚህ በኋላ ነቢያት በብሉይ ኪዳን አስቀድመው የተነበዩለት «የጌታ ቀን» ይመጣል:: በዚህ ጊዜ «አመፃን ይጨርሳል» *(ዳን.9:24)*:: አመጸኝነት ከመላ ዓለም ይደመሰሳል (ወደ ፍጻሜው ያመጣዋል):: አዳኙ ከእግዚአብሔር ተልኮ ከኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር ውጭ በቀራንዮ መስቀል ላይ ዓለምን የማዳን ሥራውን ፈጽሟል *(ዕብ13:12)*:: በዚያን ቀን *«ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ»* የዓለም ፈራጅ በመሆን *«የእግዚአብሔርን የቁጣውን መጥመቂያ»* ለመርገጥ ይገለጣል *(ራዕ.14:19-20)* ::

በመጀመሪያ የሚፈረድበት «ተቃዋሚውና ራሱን ከፍ የሚያደርግ» ነው:: *(2ተሰ.2:4)* እርሱም በአርማጌዶን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ የሚዘጋጀው «የክርስቶስ ተቃዋሚ» ነው:: ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተገለጸው በጠቅላላ የተደመሰሰ ይሆናል:: «የምድር ነገስታትና ጭፍሮቻቸው» «የዓመጽን ሰው» ያመሰኩና መጪውን ጌታ ለመዋጋት የተከተሉት ሁሉ በአርማጌዶን የጦርነት ሜዳዎች ላይ ይገደላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ *«በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ»* ይላል *(ራዕ.19:19-21)*: ይህ ፍርድ አስፈሪ ፍርድ ነው:: ምክንያቱም የተገደሉት ደም እስከ ፈረሶች ልጓም የሚደርስ ርቀቱ ሺህ ስድስት መቶ ምዕራፍ ሆኖ የሚደርስ ነው *(ራዕ.14:20)*: የግሪኩ ቃል ስታድያ (Stadia) በእስፖርት ሁኔታዎች ጊዜ ለመለኪያ የሚጠቀሙበት ነበር:: በ(King James Translation) ትርጉም ምዕራፍ በመባል ተተርጉሟል:: እርሱም 185 ሜትር ርዝማኔ ያለው ነው:: በሮማውያን መለኪያ ደግሞ 192 ሜትር ርዝመት ያለው ነው:: ከዚህ በመነሳት 1600 × 185 ወይም 1600 × 192 ስፋት ያለው የምድር ርዝመት ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህም ወደ 300 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው፣ የተገደሉት ሰዎች ሬሳ ከፍታው ግማሽ ሜትር የሆነ ክምር የሚገኝበት ነው:: እንዴት ያለ ተወዳዳሪ የሌለው ጥፋት ነው! ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ከኢየሩሳሌም 300 ኪሎ ሜትር ዲያሜትር ያለው ክብ ስዕል ብንስል በኢዝራኤል ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው የሚጊዶን (የአርማጌዶን) የጦር ሜዳ ከኢየሩሳሌም 150 ኪሎ ሜትር ያህል የራቀ ሆኖ ነው የምናገኘው:: ስለሆነም ይህ ቦታ የሚገደሉት ከሚወድቁበት እጅግ ሰፊ ከሆነው የመሬት ስፋት ጥቂቱ ነው:: ይህም በክርስቶስ ተቃዋሚ ተታልለው የሚመጣውን ንጉስ ለመውጋት ከመላ ዓለም የሚመጡት ሕዝቦች ብዛት ምን ያህል ብዙ እንደሆኑ ለመገመት ያስችለናል:: ያለ ጥርጥር ከዚህ በፊት በአርማጌዶን እንደሚሆነው ጦርነት ሞትና ደም ያለ የሚመስል ዓለም የስጠችው ምስክርነት አይኖራትም (የላትም):: «በህያው እግዚአብሔር እጅ በፍርድ መውደቅ የሚያስፈራ ነው»:: *(ዕብ.10:31)*

## ፍርድ በአሕዛብ

በነቢዩ ኢዩኤልና በማቴዎስ የተገለጸው የአሕዘብ መፈረድ ከአርማጌዶን ጦርነት በኋላ የሚከናወን ነው::

*«የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል:: አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል» (ማቴ.25:31-32)::*





*(ማቴዎስ 25:31-46)* የሚናገረው እንዳንዶች እንደሚያምኑት ስለ መጨረሻው ፍርድ ሳይሆን ስለ አሕዛብ መፈረድ ነው:: ይህም ከሚከተሉት ሀሳቦች የተነሳ ነው::

1. ጌታ ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ይመለስና (ቁ.31) በኢየሩሳሌም በክብር ዙፋን ላይ ይቀመጣል *(ዘካ.14:9፤ ኤር.3:17)*:
2. እንደ *(ማቴ.25:31-32)* አባባል እሱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይገዛል፣ በዓለምም ሕዝብ ላይ ይፈርዳል *(ኢዩ.3:2-12፣ መዝ.93:1-2፤ 94:1-7፤ 97:1-7)*:
3. በመጨረሻ ጊዜ በሙታን ላይ እንደሚፈርደው ራዕይ 20:11-15 ሳይሆን በሕይወት ባሉት ብቻ ነው የሚፈርደው::
4. በአሕዛብ ላይ የሚፈርደው «ከእነዚህ ወንድሞች» ለተባሉት ባሳዩት ምህረትና ርኅራኄ ላይ በተመረኮዘ ነው:: «እነዚህ ወንድሞች» የተባሉት «የንጉሡ ወንድሞች» የእስራኤል ልጆች (ህዝቦች) መሆናቸው ግልጽ ነው:: *(ማቴ.25:34-40)* ለእስራኤል ያደረጉት ምህረት የፍርዱ መለኪያ ነው::
5. «ብሩካን» የተባሉት ሕዝቦች ምህረትን ያደረጉት «ወንድሞች» ለተባሉት ብቻ ሳይሆን ለሰማያዊው ንጉስም ነው:(ማቴ 25:40)
6. በቁጥር 40 ስለዚህም በእነዚህ ወንድሞች ላይ ባሳዩት ምህረት ምህረቱን በእነርሱ ላይ በመዘርጋት ወደ አንድ ሺህ ዓመት ምድራዊ መንግስቱ እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል:: *(ማቴ.25:34-46)*
7. «የተባረኩት» ሕዝቦች ምህረትን ስላደረጉ ወዲያውኑ የሚድኑ አይደሉም:: ይህ ከሆነ ንጉሡ በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለ ዓለም ኃጢአት መሞቱ በከንቱ ነው ማለት ነው:: የተባረኩት በሰማያዊው መንግስት በምድር ላይ ሲኖሩ በእውነትና በትህትና ንስሐ በመግባት በተፈጸመው በንጉሡ የማዳን ሥራ ማመን ይኖርባቸዋል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አባልነት የተገባቸው አይደሉም:: በመሲሁ መንግስት ፍጻሜ ገደማ ብዙዎች እንደሚያደርጉት ንጉሡን ይክዱታል:: *(ራዕ.20:7-10)*
8. እነዚህ ወንድሞች በእርግጥ የእስራኤል ልጆች ናቸው:: አህዛብም የእስራኤል ህዝብ ባሳዩት ርህራሄ መሠረት እንደዚሁ ንጉሱም ለእነርሱ ይራራላቸዋል:: ኢዩ 4:1-21


9. የንጉሡ «ወንድሞች» ንጉሡ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ የተወለደባቸው ሕዝቦች ተወላጆች ናቸው:: እንደ *(ሮሜ9:1-5)* ባለው መሠረት የንጉሡ ሥጋዊ ወንድሞች ናቸው፣ ምክንያቱም ንጉሡ የተወለደው ከይሁዳ ነገድ ነውና:: ከእይሁድ ነገሥታት ትውልድ ሀረግ ካሉት ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በሥጋና በደም ዕብራዊ ነው *(ዕብ.2:14-16)* ::

10. በኃጢአታቸው ምክንያት በዓለም ሙሉ የተበታተኑ ቢሆኑም «ወንድሞች» ናቸው:: ነገሥታት፣ መሳፍንት፣ መስዋዕት፣ መስዊያ፣ መቅደስ፣ ደህንነት፣ በውስጣቸው ያደረ መንፈስ ቅዱስ ስላልነበሯቸው የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት አልነበራቸውም *(ሆሴ.3:4-5፤ ማቴ.23:37-39)* ::

11. የዚህ ፍርድ መመዘኛው (ማቴ 25:31-45) በእርግጥ ርህራሄ ነው:: አህዛብ ለእስራኤል ህዝብ ርህራሄን በማሳየታቸው በዚሁ መጠን የሰማዩ መንግሥት ንጉሥ ለእነዚህ አህዛብና ለእያንዳንዱ ዘመዶቻቸውም ጭምር ርህራሄን ያሳያል ርህራሄ (ቁጥር 33-40)

12. በኢዩ.3:1-17 እግዚአብሔር በእስራአል ላይ በፈጸሙት በደል እደሚፈርድባቸው የሚናገር ክፍል እናገኛለን:: *(ማቴ.25:31-46)* የሚፈረድባቸው ለእስራኤል ባሳዩትና ባላሳዩት ምህረታቸው የተነሳ ነው *(ማቴ.25:41-46)*::

በአሕዛብ ፍርድ የሚሆነው በኢየሩሳሌም ነው::እዚያ በዓለሙ ሁሉ ላይ በሚፈርደው ፊት አሕዘብ ሁሉ ይቀርባሉ::መጽሐፍ ቅዱስ «በፍርድ ሸለቆ» የብዙ ብዙ አሕዛብ ክምችት እንደሚሆን ይናገራል *(ኢዩ.4:14)*:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የፍርድ ሸለቆ» የተባው «የኢዮሳፌጥ ሸለቆ» ተብሎ ተጠርቷል *(ኢዩ.3:2)* ይህ ስፍራ በሞርያ ተራራና በኢየሩሳሌም ባለው በደብረ ዘይት ተራራ መካከል ያለው የቄድሮን ሸለቆ ነው:: በዚህ ቦታ መጪው ንጉስ ሊፈርድባቸው አሕዛብን ሁሉ ይሰበስባል::








*«እግዚአብሔርም በጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮሀል፣ በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል:: ሰማይና ምድርም ይናወጣሉ፣ እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፣ ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ ይሆናል » (ኢዩ.4:16)::*

*«ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፣ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነ፣ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፣ በለስም በብርቱ ንፋስ ተናውጣ ቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፣ ሰማይም እንደ መፅሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ:: ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ:: የምድር ነገስታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለፀጋዎችም ሐይለኞዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች አለቶች ተሰወሩ:: ተራራዎችና አለቶችንም በላያችን ውደቁ፣ በዙፋኑም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን፣ ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቷልና፣ ማንስ ሊቆም ይችላል አሏቸው» (ራዕ.6:12-17 )*::

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ግልጽና ለመረዳት የሚቻሉ ቀላል ስለሆኑ ሌላ መጨመር አስፈላጊ አይደለም::

በአሕዘብ ፍርድ ጊዜ ጌታ ልዩነት ማድረጉ ግልጽ ነው:: ^ርሱ «እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል» *(ማቴ.25:32)*:: ሰዎች ከየትኛው ክፍል እንደሚሆኑ የሚወስናቸው በእግዚአብሔር ምርጦች ሕዝብ ላይ ባላቸው አቋም ነው:: ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ምህረት የፍርዱ መለኪያ ነው:: ለእስራኤል ምህረትን ያደረጉና አይሁድን በስደታቸው ጊዜ የረዷቸው ሕዝቦች ስለ «ታናናሾቹ ወንድሞቹ» ከጻድቁ ፈራጅ ምህረትን ይቀበላሉ:: በእግዚአብሔር አብ የተባረኩ ይሆናሉ፣ ወደ መሲሁ የሰላም መንግስት እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል *(ማቴ.25:34)*:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት «የሚምሩ ብፁአን ናቸውና ይማራሉ» ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው *(ማቴ.5:7)*:: «ምህረትም በፍርድ ላይ ይመካልና» *(ያዕ.2:13)* ነገር ግን ይህ ወዲያውኑ ይድናሉ ማለት አይደለም:: ይህ ከሆነ በመልካም ሥራ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ይቻላል ማለት ነው:: ይህ ከጥያቄ ውጪ የሆነና ደህንነት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሆነውን የአዲስ ኪዳን መልእክትንና እርሱ በግልጽና በማያሻማ መንገድ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሎ ያተመውን ቃል የሚቃረን ነው *(ዮሐ.14:6፤ ሮሜ.3:21-28)*:: ሆኖም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት የተፈቀደላቸው በሺው የሰላም ዓመታት ጊዜ ውስጥ ንስሐ የመግባትና ወደ መሲሁ የመመለስ ዕድል አላቸው:: ማንኛውም ሰው ምህረት በማድረጋቸው ንጉሡ ከባረካቸው ጭምር ንስሐ መግባት አለበት::

እስራኤልን የጠሉትና ንጉሡንም መጥላታቸውን የገለጹት ሕዝቦች ሁሉ ወዲያውኑ «ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት» ይጣላሉ *(ማቴ.25:41)*:: በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከክርስቶስ ዳግም መምጣት ቀጥሎ ዝቅ ብሎ ወደ ታች ወደ ዘላለም ፍርድ የሚወርደው የቀጭኑ ሰማያዊ መስመር ፍቺ ይህ ነው::

«ከበጎቹ» ከሆኑትና፣ ወደ መሲሁ መንግስት እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በስተቀር ያልዳኑት የዓለም ሕዝቦች በእግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅድ ወደ ፊት ቦታ የላቸውም:: ምክንያቱም የክርስቶስን ተቃዋሚ የተከተሉና ያመለኩ፣ እግዚአብሔርን የካዱና ጠላቱ የሆኑ ስለሆኑ የሚጠብቃቸው አስፈሪው ፍርድ ብቻ ነው *(ራዕ.13:8፤ ሮሜ.1:28-32)*:: ማንኛውም ሰው ያለፈውንና የአሁኑን የዓለምን ሁኔታ በትኩረት የሚመለከት ከሆነ የዓለም ሕዝቦች ወደዚህ እያመሩ እንዳሉ ለመረዳት አያደግተውም:: በግልጽና ያለ ጥርጥር ወደታች ማለትም ወደ መቅሰፍት፣ መደምሰስ፣ ፍርድና ወደ ዘላለም ጥፋት እያሽቆለቆሉ ናቸው::

## 3. የኢየሱስ ክርስቶስ ለእስራኤል ሕዝብ መመለስ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ለእግዚአብሔር ምርጦች ሕዝብ ንጉሳቸውና መሲህ በመሆን ይመጣል:: እስራኤል እስከዚህ ቀን ድረስ ንጉሷን ያልተቀበለች ብትሆንም ይህ ሁኔታ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚቀጥል ሆኖ እንደማይቀር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: አዳኙ (ጌታ ኢየሱስ) በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የሕዝብ መሪዎች ለነበሩት ለጸሐፍትና ለፈሪሳውያን እንዲህ በማለት ነግሮአቸው ነበር:: *«እላችኋለሁና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም» (ማቴ.23:39)::*

በዚያን ጊዜ የሕዝቡ መሪዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መሲህ አድርገው አልተቀበሉትም ነበር:: *በነቢዩ (ኢሳያስ 9:16)* «ይህን ሕዝብ የሚመሩ ያስቷቸዋል፣ ተመሪዎችም ይጠፋሉ::» ተብሎ ተነግሯልና:: ስለሆነም መላ ሕዝቡን ለሁለት ሺህ ዓመታት ደምና ለቅሶ ለተሞሉበት መከራ ዳረጉት:: የክርስቶስ ተቃዋሚ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚያመጣው ታላቁ መከራ ለእስራኤል ሕዝብ አሰቃቂ የሆነ የሀዘንና የስደት ጊዜ ይሆንባቸዋል:: ከእያንዳንዱ ነገድ 12,000 ከአስራ ሁለቱ ነገድ የሆኑት 144.000 ብቻ ታላቁን መከራና ስቃይ ይቋቋሙታል:: *(ራዕ.7:4-8)* ሊቋቋሙት የሚችሉት በአንድ ምክንያት ብቻ ነው::ምክንያቱም እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ*(ራዕ.7:2-4)* ከጠላቶቻቸው





የተጠበቁ እንዲሆኑ በግንባራቸው ላይ ስላተመባቸው ነው *(ራዕ.7:3 ፤ሕዝ.9:4-6)*:: እንደ *ዘካ.13:8* መሠረት በመጨረሻዎቹ ቀናት ከእስራኤል ሕዝብ አንድ ሦስተኛው ብቻ የሚቀሩና የጌታችንን ስም የሚጠሩ ይሆናሉ:: እነርሱም ወደ እርሱ ይጮኻሉ፣ ጌታም ይመልስላቸውና

*«እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ፣ እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው (ዘካ.13:9)»* ይላል:: እስራኤል ወደ ፊት ካለባት ከፍተኛ ችግር ባሻገር መጪውን መሲህ ለመገናኘት ክፍ እያለች ነው::

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት በተለያዩ ሕዝቦች ላይ (በቤተ ክርስቲያን፣ በእስራኤልና በዓለም ሕዝቦች) የተለያዩ ሁኔታዎች እንደሚፈጥር ጠቅሰናል:: የእርሱ መመለስ ለዓለም ሕዝቦች ለፍርድ ሲሆን ለእስራኤል ሕዝብ ግን ለመጨረሻና ለዘላለም ሊያድናቸው መሲህ ሆኖ ይመጣላቸዋል::

ጌታ ሲመለስ «በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጡትን አሕዛብ ሁሉ ለማጥፋት» ይመጣል (*ዘካ.12:9*):: በዚያኑ ጊዜ «በዳዊት ቤት ላይ፣ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ» ያፈስስላቸውል *(ዘካ.12:10)*:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለሰው አንድ ጊዜ ብቻ ስለሆነ በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ይህን የሚያመለክተው አረንጓዴና ቡናማ መስመር አንድ ቀጥ ያለ መስመር ብቻ ነው::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ በሚመለስበት ጊዜ የሚገለጸው በታላቅ ክብር ነው:: ይህ ሁኔታ ለእስራኤል ለብዙ ሺህ ዓመታት ቃል ኪዳን ስለተገባለቸው መሲህ ተስፋ መፈጸም የሚሆን ብቻ አይደለም:: የመንቀጥቀጥና የድንጋጤም ጊዜ ነው የሚሆንባቸው:: ምክንያቱም «የወጉትንና» በመስቀል ላይ «የቸነከሩትን» ስለሚለያዩት ነው:: «የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ» *(ራዕ.1:7)*:: በዚህ ጥቅስና *(በማቴ.24:29-31)* ላይ «ፍዩል» (Phule) የሚለውን የግሪክ ቃል እናገኛለን ትርጉሙም የምድር ነገዶች፣ ወይም ወገኖች ማለት ነው::

በእስራኤል ምድርና በመላ የዓለም ሀገሮች ተበታትነው ያሉትን የእስራኤልን ትውልዶችን የሚያመለክት ነው:: በዕብራይስጥ ቋንቋ መሬትን ኧርዝ (Eretz) ይሏታል ትርጉሙም:- ምድር ማለት ነው:: ኤሬትስ እስራኤል ማለት እስራኤል ምድር ማለት ነው:: ስለዚህም *(ራዕ.1:7)* የሚያመለክተው በመላ ዓለም ተበታትነው ያሉትን አስራ ሁለቱን ነገዶችና በእስራኤል ምድር ያሉትን አስራ ሁለቱን ነገዶች ነው:: የሚመጣው መሲህ በመስቀል ላይ የተሰቀለው የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ማንም ከእነርሱ የገመተ አልኖረም:: ሕዝቦች ሁሉ እርሱን በጲላጦስ ፊት ካዱት፣ *(ሐሥ.3:14-15)* «ከቄሳር በስተቀር ንጉስ የለንም» (*ዮሐ.19:15*):: ብለው መሪዎቻቸው

በሎኹ ጊዜ እርሱ ገዢያቸው እንዳልሆነ በመቁጠር መካዳቸው ነበር *(ሉቃ.19:14)* ለብዙ ጊዜ በግልጽ የካዱትን ያከብሩታል፣ ይገዙላታል:: ይህ ግንዛቤ መላ እስራኤልን ከመሪዎቻቸው ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ ወደ እውነተኛ ንስሐ ያመጣቸዋል::

*«ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ፣ ያለቅሱለታል፣ ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኃዘን ያዝኑለታል» (ዘካ.12:10)::*

ልጅ የሞተበት በተለይም የበኩር ልጅ የሞተበት ማንኛውም ሰው ቤተሰብ ስለ ልጁ በብርቱ እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ ይታወቃል:: የእስራኤል ሕዝብ በመጨረሻው ጌታ ኢየሱስ መሲአቸው መሆኑን ሲገነዘቡ የሚያለቅሱትና የሚያዝኑት ልክ እንደዚሁ ነው:: መስስ ብለው ወደ ኋላ ሲመለከቱ ከእርሱ ርቀው ከመንገድ ወጥተው በራሳቸው መንገድ መሔዳቸው ተረድተው ሲያዝኑ መከራ ተቀባዩ ስለ ሆነው አገልጋይ የሚናገረው ታላቁ *የኢሳ.53:1-12* የንስሃ ዝማሬያቸው ይሆናል:: ነቢዩ ዘካርያስ እስራኤል መሲሁን በሚቀበሉበት ጊዜ የሚገቡትን ንስሐና ሐዘን በሚከተሉት ቃላት ገልጸዋል:: (ኢሳ. 53:6) በቃል ኪዳን የመጀመሪያ ነበሩ:: አሁን ግን የመጨረሻዎቹ ሆነዋል:: *(ማቴ.19:30፣ 20:16)*:: ነቢዩ ዘካርያስ እስራኤልን መሲሁን በምትቀበልበት ጊዜ የሚገቡትን ንስሃና ሐዘንን በሚከተሉት ቃላት ገልጾታል::

*«ምድሪቱም ታለቅሳለች፣ እያንዳንዱ ወገን ለብቻው፣ የዳዊት ቤት ወገን ለብቻቸው፣ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የናታን ቤት ወገን ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣የሌዊ ቤት ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የሰሜኢ ወገን ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የቀሩት ወገኖች ሁሉ እያንዳንዱ ወገን ለብቻቸው ያለቅሳሉ» (ዘካ.12:12-14)::*

*ማቴ.24:30* በእስራኤል ምድር የሚኖሩት ነገዶች ሁሉ እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ ይናገራል:: መጽሐፍ ቅዱስ *በዘካ.12:12-14* ባለው ክፍል ስለ አንድ ምክንያት በተለይ ሴቶች እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ በማጠንከር ይናገራል:: ፈርሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሴቶች በተለይም ከይሁዳ ነገድ የሆኑት በሚያረግዙበት ጊዜ የመሲሁ እናት የመሆን ዕድል እንዳላቸው ማሰት መሲሁ ከእነርሱ እንደሚወለድ ይገምቱ ነበር የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ልጅ መሲህ መሆኑን ባለመገንዘባቸውና ባለመቀበላቸው ምክንያት ወደ ፊት ገና ይወለዳል ብለው ይጠብቃሉ:: ዛሬም ቢሆን መሲሁ በሥጋ እንደሚመጣ ሃይማኖታውያን በሆኑት በአይሁዶች ዘንድ የታወቀ ነገር ነው:: አንድ ጊዜ አንድ አይሁዳዊ አንድ እርጉዝ ሴት ብዙ ሰዎች በተሳፈሩበት አውቶቡስ ውስጥ ስትገባ የሚያደርጉትን ነገረኝ ሃይማኖቱኛ





አይሁድ በዕድሜ የገፉ ቢሆን እንኳን ተነስቶ መቀመጫ ይሰጧታል:: በዕድሜ ወጣት በመሆኗና መቆም እንደምትችል ራሷን አድርጋ በመገመት ለሰውየው አክብሮት በመስጠት እንቢ ብትል እንኳን በዕድሜ የገፋው ሰው በመነሳት «እባክሽን ተቀመጭ በማህጸንሽ የተሸከምሽው መሲሁ ሲሆን ይችላል:: በፊቱ ልነሳና ልቁም» ይላታል:: በዚህ ስለ መሲሁ ስላላቸው ጥበቃ ልንስቅ እንችል ይሆናል:: እኛ ግን ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ከንጉስ ዳዊት ዘር የሆነችው ማርያም መሲሁን መውለድዋን እናውቃለን *(ሉቃ.2:1-14፤ ገላ.4:4፤ ሮሜ.1:3፤ 2ጢሞ.2:8)*:: የእስራኤል ሕዝብ መሲሁን እንዴት በትኩረት እንደሚጠብቁ ይህ ምሳሌ ሲሆነን ይችላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ለመላው እስራኤል ከፍተኛ ሀዘን እንደሚሆንባቸው ግልጽ ነው:: ምክንያቱም የሚጠብቁት መሲህ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት መጥቷልና:: የእስራኤል ሕዝብ አሁን ግን ያንን የመሲሁን የመወለድ ታምር ባለመቀበላቸው፣ እርሱ ሲመጣ እርሱ መሆኑን ሲያዩና ሲገነዘቡ፣ ያዝናሉ መራራ ለቅሶም ያለቅሳሉ::

ሕዝቡ ንጉሡንና መሲሁን መራራ በሆነ ሀዘንና በእውነተኛ ንስሐ ወደ እርሱ በመመለስ ሲቀበሉት የፀጋ ሰዓት ይመጣላቸዋል:: ከዚህ በኋላ ታማኙ ጌታ ኃጢአታቸውን ይደመስስላቸውና *(ሮሜ.11:27)* በመላ የእስራኤል ቤት ላይ ምህረትን ሲያፈስላቸው (ሕዝ. 39:25) መላ እስራኤል ይድናሉ (ሕዝ. 39:29) የዳኑት *(ሮሜ.11:26)* የእግዚአብሔር ሕዝቦች በንጉሳቸው መሪነት ወደ መሲሁ የሰላም መንግስት ይገቡና ለሺህ ዓመት የእግዚአብሔር የወንጌል መልእክተኞች ይሆናሉ::

ስለዚህ ወደፊት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የተከበረ ጊዜ አላቸው:: አንዳንዶች እንደሚያምኑት ጌታ ሕዝቡን የጣላቸው አይደለም:: ለጥቂት ጊዜ ሕዝቡን ትቷቸው ነበር:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ልጅ አላመኑም ነበርና:: በአጭር ቀናት ውስጥ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት የተነገሩት ትንቢቶች በዓይናችን የሚፈጸሙ ይሆናሉ:: የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ወደ ቅድስት ምድራቸው እየተሰበሰቡ ናቸው:: እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚዋጅበትና የሚቀበልበት ጊዜ እየቀረበ ነው:: እስራኤል ወደ መዳኗ በከፍተኛ ደረጃ እየቀረበች ነው::

**የወደፊቱ ሶስቱ የሰው ዘር ክፍሎች:-**

| | | |
|---|---|---|
| **ቤተ ክርስቲያን -** | **ወደ ቤቷ መሔድ -** | **ክብር** *(1ኛ ተሰ.4:17 ዮሐ.14:3)* |
| **እስራኤል -** | **ወደ ከፍታዋ መሔድ -** | **መሲሁን ለመገናኘት (ሮሜ 11:26 ኢሳ.59:20)** |
| **አህዛብ -** | **ውርደት -** | **ለፍርድ (25:41)** |


የሦስቱ የዋናዎቹ የማዳን መስመሮች ትይይዝ በመዋጀት ታሪክ ፍጻሜ ላይ

## የመሲሁ የሰላም መንግስት

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ከእግዚአብሔር የተቀበለው ታላቅ ራዕይ ዳን. 2:1-45 ስለ አራቱ መንግስታት፣ ስለ ባቢሎን፣ ስለሜዶንና ፋርስ፣ ስለግሪክና ስለሮም የሚናገረው በተሰጠው በዘላለማዊና በማይደመሰሰው መንግስት ተስፋ የሚደመደም ነው::

*«በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሳል፣ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፣ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፣ ታጠፋቸውማለች፣ ለዘላለምም ትቆማለች» (ዳን.2:44)::*

በዚህ ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነገርለት መንግስት ገና ወደ ፊት የሚመጣ ነው:: እንዳለፉት እንደዚህ ምድር ነገሥታት በሰው ሳይሆን ጊዜው ሲደርስ በራሱ «በሰማይ አምላክ» የሚመሠረት ይሆናል:: ይህ ጊዜ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሲመጣ መሆኑን በማዳን ታሪክ ተምረናል:: ጌታ ለፍርድ በሚገለጥበት ጊዜ የምድር መንግስታት ሁሉ፣ አመጽና ኃጢአት ለዘላለም ከምድረ ገጽ ላይ ይጠፋሉ::








በክርስቶስ ተቃዋሚና በአስቃቂ አስተዳደሩ መደምሰስ ለብዙ ሺህ ዓመታት የቀየው የአሕዛብ ዘመን ያበቃል ያከትማል *(ሉቃ.21:24)*: የአመጽ ጀማሪና የመጀመሪያ አመጸኛ የሆነው «ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ» *(ራዕ. 12:9)* የተባለው በዓለም የማሳትና የማጥፋት ሥራውን ለአንድ ሺህ ዓመታት አይሠራም:: አሕዛብን እንዳያስት ሰይጣን ለሺህ ዓመት ታስሮ ወደ ጥልቁ ይጣላል *(ራዕ.20:1-3)*:

ስለሆነም ዓለም ሊመጣ ላለው ለመጨረሻው መንግስትና ለማዳን ታሪክ የተዘጋጀች ትሆናለች *(ራዕ.19:19-21)*: ይህ መንግስት የመሲሁ «የሰላም መንግስት» ወይም «የሺህ ዓመት መንግስት» በመባል ይታወቃል:: በስሙ እንደተጠቀሰው ይህን መንግስት የሚመሠርተው የእስራኤል ሕዝብ መሲህ በሆነው በእውነተኛው የሰላም አለቃ በሆነው እንጂ በሌላ ሲሆን አይችልም:: *(2ሳሙ.7:1-29፤ ሉቃ.1:31-35)* ይህ መንግስት በምድር ላይ የሚቆየው ለሺህ ዓመታት ነው *(ራዕ.20:1-10)*: ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግስት (የሰማይ መንግስት) ለዘላለም የጸና ሆኖ ይመሠረታል *(ራዕ.11:15፤ 22:5)*:

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር መንግስት በዚህ ምድር ላይ ይመሠርታል በሚል ላይ ያረፈ ነበር:: አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረውና በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እንደሚታየው የሺሁን ዓመት መንግስት ወደ ዓለም ፍጻሜ የሚመራው የማዳን ታሪክ የተያያዘ ነው:: ሆኖም ይህ የሺው ዓመት መንግስት ከሰማይ መንግስት ጋር አንድ አድርጎ ማየት አያስፈልግም:: ነገር ግን ይህ መንግስት በምድር ላይ የእግዚአብሔር አገዛዝ የሆነ ነው:: በዚህ መንግስት የእስራኤል ህዝብ፣ አሕዘብና ቤተ ክርስቲያን የራሳቸው የሆነ ሥራ አላቸው::

በዚህ ላይ ተመሥርተን እንደ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም እስከ ሺሁ ዓመት መንግስት ዓመት የማይፈጸሙትን ብዙ ትንቢቶች እንመርምር::

### 1. እስራኤል - የመላ ዓለም በረከት

ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለፈርዖን «እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፣ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ» በማለት ተናግሮት ነበር *(ዘፀ.4:22-23)*: የበኩር ልጅ የሆነው እስራኤል ከብዙ ዓመታት በፊት ከግብፃውያን የባርነት ቀንበር የዳኑ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን በዓለም ሕዝብ መካከል ከመበታተንና ከስደትም ነፃ የወጡ ይሆናሉ *(ዘፀ.14:30)*: ጌታ ሲመለስ

የእስራኤል ሕዝብ ሲድኑና ጌታን ሲቀበል እስራኤል የአሕዛብ ራስ ትሆናለች *(ዘዳ.28:13)*:: በመሲሁ የሰላም መንግስት ጊዜ እስራኤል ለዓለም በረከት ትሆናለች:: በንጉሡ አገልግሎት ዓለምን ወደ ሰላም የምትመራ ትሆናለች:: (ኢሳ.19:24) ጌታ በመንግስቱ ያላቸውን መብትና ሥራ እንዲህ በማለት አውጆላቸዋል::

*«እስራኤል ሆይ፣ አንተ ባርያዬ ነህ በአንተ እከብራለሁ» (ኢሳ.49:3)*

*«በምድር አሕዘብ ሁሉ መካከል ለክብረ ለምና ለምስጋና አደርጋችኋለሁ» (ሶፎ.3:20)::*

*«ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፣ እናንተም የካህናት መንግስት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» (ዘፀ.19:5-6)::*

ስለዚህ በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ በአሕዛብ መካከል መሪ ትሆናለች:: በቅድስናና በመንፈሳዊ መንገድ አገልጋይ በመሆን ለመላ ዓለም ታላቅ በረከት ትሆናለች:: *(ዘፍ.12:3፤ 26:4፤ 28:14)*

## እስራኤል - ለጌታ የመልእክተኛ ህዝብ

እስራኤል ወደ ምድሯ ስትመለስ፣ በመሲሁ ዘመን እውነተኛ ተልዕኮዋንና ወንጌል በመላ ዓለም ማሰራጨቷን ትፈጽማለች::

*«ከጽዮን ሕግ፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና» (ሚክ.4:2)::*

*«ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ» (ኢሳ.43:21)::*

ጌታ ሕዝቡን ቃሉን እንዲያውቁና ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲሰብኩ ይጠቀምባቸዋል:: ያም ታላቅ ውጤት ያለው ይሆናል:: ምክንያቱም *«በዚያ ዘመን ከአሕዛብ ቋንቋ ሁሉ አሥር ሰዎች የአንዱን የአይሁዳዊ ሰው ልብስ ዘርፍ ይዘው፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰምተናልና ከእናንተ ጋር እንሂድ ይሉታልና»* (ዘካ. 8:23)::

እንደ ተርሴሱ ተወላጅ እንደ ሳዖል ይሆናል:: ከተለወጠ በኋላ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆነ:: ወንጌልን በመስበክ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ በመመለስና አብያተ ክርስቲያናትን በያለበት በማቋቋም የሮምን መንግስት የገለባበጠ ሆነ:: በተመሳሳይ መልኩ በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ የተለወጠውና የዳነው እስራኤል ወንጌል የሚሰብክና ብዙ አሕዛብን ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመልስ ይሆናል:: በዚህ አኳኋን እስራኤል «ከእግዚአብሔር እንደሚወርድ





ጠል፣ በሣር ላይ እንደሚወርድ ካፊያ» በምድር ላይ በረከት ትሆናለች *(ሚክ.5:7፤ ኢሳ.19:24፤ዘካ.8:13)*:: ከዚህ በኋላ ማንኛውም ሰው *በዮሐ.4:22 «መዳን ከአይሁድ ነው»* የሚለውን በእውነት ግልፅና ተፈፃሚ ይሆናል::

## 2. አሕዛብ – አብረው የመንግሥቱ ወራሾች መሆናቸው

«የክርስቶስ *ዳግም መምጣት*» በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በሺው ዘመን *መንግስት* ጥቂት አሕዛብ ብቻ ወደ *መንግስቱ መግባታቸውን ተመልክተናል* *(ማቴ.25:31-40)*:: ለማስታወስ ያህል የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆኑት ለእስራኤል ምህረት ያደረጉት በአሕዛብ ፍርድ ጊዜ ምህረትን አግኝቶ እንደ ንጉሡ ቃል «የተባረኩ» ሆነው ወደ ሺሁ ዓመት መንግስት እንዲገቡ የተፈቀደላቸው መሆናቸውን ተመልክተናል:: እንደ ገና ጠንከር አድርገን መናገር የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር «የተባረኩት» ምህረትን ስላደረጉ ብቻ የማይድኑ መሆናቸውን ነው:: ይህ ከሆነ የአዳኙ ለዓለም ኃጢአት በመስቀል ላይ መሞቱ ከንቱ ነው ማለት ይሆናል:: በእውነትና በትክክል ንስሐ በመግባት በተፈጸመው በንጉሡ የማዳን ሥራ ማመን አለባቸው:: ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ይህ በትክክል እንደሚከናወን ይመሰክራሉ:: በሺሁ ዓመት መንግስት ኃይለኛ በሆነው የወንጌል መልእክት ብዙ አሕዛብ ወደ ኢየሩሳሌም «የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን» ለመፈለግ ተሰብስበው ይመጣሉ *(ዘካ.8:22)*:: በሙሉ ልባቸው ወደ ጌታ ይመለሳሉ:: *(ዘካ.2:11)* ክርስቶስንም ጌታቸውና ንጉሣቸው አድርገው በመቀበል (ኢሳ. 19:19-20) ራሳቸውን ለእርሱ ብቻ ያስገዛሉ:: መላ አሶር፣ መላ ግብፅና መላ እስራኤል ይመጣሉ (ኢሳ.19: 21-25):: ጌታም እነርሱን በመቀበልና በመባረክ የሚከተለውን ይላቸዋል::

*«ሕዝቤ ግብፅ የእጄም ሥራ አሦር ርስቴም እስራኤል የተባረከ ይሁን» (ኢሳ.19:25)::*

እነዚህና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ ከልባቸው ንስሃ የሚገቡትንና ጌታን የሚፈልጉትን ጌታ የሚቀበላቸው መሆኑን ግልጽ ያደርጉታል:: እውነተኛ ወራሽ ከሆኑት ከእስራኤል ጋር የመሲሁን መንግስት አብረው የሚወርሱ ይሆናሉ *(ኢሳ.19:25)*:: ጌታ ኢየሱስ በአሕዛብ ፍርድ ጊዜ ለመንግስቱ ለተወሰኑት የሚያውጀውን ቃል

*«እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግስት ውረሱ » (ማቴ.25:34)::*

## 3. ኢየሱስ ክርስቶስ - የመላው ዓለም ንጉስ

በዚህ ምድር ላይ የሺው ዓመት መንግስት በእግዚእብሔር ልጅ ሲመሠረት፣ በእርሱ ብዙ የመጽሐፍ ክፍሎች የተፈጸሙ ይሆናሉ::

*«እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ፣ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ» (መዝ.2:6)::*

*«እግዚአብሔር ነገሠ፣ ምድር ሐሴትን ታድርግ፣ ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው» (መዝ.97:1)::*

*«አቤቱ፣ ሥራህ ሁሉ ያመሰግኑሀል፣ ቅዱሳንህም ይባርኩሀል፣ የመንግስትህን ክብር ይናገራሉ፣ ኃይልህንም ይነጋገራሉ፣ ለሰው ልጆች ኃይልህን የመንግስትህን ግርማ ክብር ያስታውቁ ዘንድ:: መንግስትህ የዘላለም መንግስት ናት፣ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው» (መዝ.145:10-13)::*

እነዚህና ሌሎች የብሉይና የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ሆኖ እንደሚገዛ ስላለው እውነት ይመሰክራሉ:: ከብዙ ጊዜ በፊት ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔር ልጅ ከአባቱ መንግስትን መቀበሉን የሚያሳየውን ታላቅ ራዕይ ተመልክቷል:: ራዕዩም

*«በሌሊት ራዕይ አየሁ፣ እነሆም፣ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፣ ወደ ፊቱም አቀረቡት:: ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩም ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግስትም ተሰጠው፣ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፣ መንግሰቱም የማይጠፋ ነው» የሚል ነው (ዳን.7:13-14)::*

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በታወጀበት ጊዜ እንኳን ተስፋ የተሰጠው የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው ንጉስ እንደሚሆን ነበር:: *«ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን ዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም»* (ሉቃ.1:32-33)::

ነቢዩ ኢሳይያስ፣ የሚመጣውን ገዢ፣ የተገነዘበው አንድ ቀን ይህን ዓለም በመለኮታዊ ኃይልና ስልጣን የሚገዛ አድርጎ ነበር::

*«ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣አለቅነትም ጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ኃያል አምላክ፣የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሉ ይጠራል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው*





*ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሰቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም:: የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል» (ኢሳ.9:6-7)*

ስለሆነም የኢየሱስ ክርስቶስ መንግስት ሁሉን ያቀፈና ያጠቃለለ ይሆናል:: «እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል «ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዝ (ኤፍራጥስ ማለት ነው) እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል» *(መዝ.72:8)* ጌታ በኢየሩሳለም ብቻ ሳይሆን *(ኢሳ.24:23)* «በምድር ሁሉ ላይም» ንጉስ ይሆናል *(ዘካ.14:9)*:: መንግስቱ በምድር ላይ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በመላ ዓለም እንዴት እንደሚሰፋና እንደሚሞላ የሚገልጽ ይሆናል::

እነዚህን ጥቂት ጥቅሶች ስንመረምር፣ ወዲያውኑ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር የሚመጣው መሲህ፣ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠውና በታላቁ የሰላም አገዛዝ የሚገዛው ገና እንደሆነና እንዳልተፈጸመ ነው:: የተስፋው ንጉስ እስከ አሁን የተጠላ ንጉስ ነው:: ካለፈው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሕዝብ ጩኸት «ይህ በላያችን ሊነግስ አንወድድም» «ከቄሳር በስተቀር ንጉስ የለንም» የሚል ነው:: *(ሉቃ.19:14፤ ዮሐ.19:15)*

በአሁኑ ጊዜ ዓለም በሩህሩሁና በጻድቁ «የነገሥታት ንጉስና የጌቶች ጌታ» በሆነው አገዛዝ ስር አይደለችም (*ራዕ.19:16:*) ነገር ግን ሊመጣ ባለው በፀረ ክርስቶስና በገዢዎቹ እጥፉ በሆኑት የዓለማት ኃይላት ሥር ናት::. ሆኖም በሺሁ ዓመታት መንግስት በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው አስደናቂና ክብር የተሞላበት የክርስቶስ ኢየሱስ አገዛዙም በምድር ላይ የተፈጸመ ይሆናል:: «በትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም፣ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል» የሚለውና (*ዘፍ.49:10)* «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ» የሚለው በእውነት የተፈጸመ ይሆናል:: *(ፊል.2:10-11)* የሰማይ ኃይላትም በደስታ በመሞላት «ሃሌ ሉያ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሶዓልና» ይላል (*ራዕ.19:6)*::

## 4. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን – ከንጉሡ ጋር የምትገዛ

በሺው ዘመን መንግስት ቤተ ክርስቲያን የት ናት? ብለን እንጠይቅ። ከእስራኤልና ከአሕዛብ ጎን በመጪው ሺህ ዓመት ቤተ ክርስቲያን የተለየ ሥራ አላት። መልስ ብለን እንደገና በትኩረት እንመልከት። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን «የክርስቶስ አካል» ናት። ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ የቤተ ክርስቲያን አባል ነው (*1ቆሮ.12:27*)። ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማትለይ ከእርሱ ጋር የተያያዘች መንፈሳዊ አካል ናት (*ቆላ.1:18*)። የመነጠቅ ጊዜ ሲመጣ፣ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ጉዞዋን የፈጸመች በመሆን «ከጌታ ጋር ሁልጊዜ» ትሆናለች (*1ተሰ.4:17*)። ራሱን ጌታን በመምሰል አስደናቂ ወደ ሆነው ሰማያዊ ክብር የተለወጠች ትሆናለች።የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ከአባሉቹ (ዳግም ከተወለዱት አማኞቹ ጋር ለዘላለም የተባበረ ይሆናል።አባሎቹም ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ክብር ለዘላለም ተካፋዮች ይሆናሉ።(*2ተሰ.2:14፤ቆላ.3:4፤ 1ቆሮ.1:9*)

ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ስትሆን፣ ከእርሱ ጋር ለዘላለም የምትኖር ብቻ ሳይሆን አብራ የምትገዛ ትሆናለች (*2ጢሞ.2:11-12*።) ጌታ በግልጽ «እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ፣ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል ለነሳው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጠጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» ይላል (*ራዕ.3:21*።) ጌታ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር (ሲመለስና በደሙ ከተገዛችው ቤተ ክርስቲያን) (1ኛተሰ. 3:13) በምድር ላይ መንግስቱን ሲያቋቁም አብረው ተካፋይ ይሆናሉ። አክሊል የተሰጣቸውና የተመረጡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። እነርሱም ከንጉሳቸው ጋር አብረው ይገዛሉ። ዓለምን ሲፈርድ አብረው የሚፈርዱ ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ስለዚህ ነገር እንዲህ ይላል።

*«ዙፋኖችንም አየሁ፣በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግንባራቸውና በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፣ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» (ራዕ.20:4።)*

ሐዋርያው ጳውሎስ «ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ «እስረግጦ ተናግሯል (*1ቆሮ.6:2*)። ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ከንጉሳቸው ጋር ሆነው በሚፈርዱበት ጊዜ በመላእክት ላይም እንደሚፈርዱ ተናግሯል። ቃሉም *«በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ እታውቁምን» የሚል ነው (1ቆሮ.6:3።)*





እነዚህ እረፍተ ነገሮች እጅግ አስደናቂ ናቸው። የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በእግዚእብሔር ጸጋ ከፍ መደረጓንና ያላትን ከፍተኛ ስፍራን ያመለክታሉ። ባላት ባሕርይ በማያጠራጥር ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ» የተባረከች ናት (*ኤፌ.1:3*)። በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል በምድር ያለች የእግዚአብሔር ሕዝብ ናት የምታገኘውም ምድራዊ በረከትን ነው። (*ኢሳ.60:21*) የማንዘነጋው ነገር ቢኖር የከበሩት የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች የተለወጡና ወደ ፊትም ምድራዊ አካል ሳይሆን መንፈሳዊ፣ የከበረ ሰማያዊ እካል ያላቸው ይሆናሉ (*ፊል.3:21፤ 1ቆሮ.15:40-49*)። ስለሆነም በምድር ላይ የገጽታቸው ሁኔታ ጌታ ከትንሣኤ በኋላ ያለው ገጽታ ይሆናል። ወደ ክብር ስለተለወጡ፣ ለሰማያዊ ዓለም የተገቡ በመሆናቸው የማይታዩ (መንፈሳዊ አካል ያላቸው) ይሆናሉ። ጌታ ከትንሣኤው በኋላ እንዳደረገው (በመብላትና በመጠጣት ማለት ነው) በምድር ሕይወት ተካፋይ ይሆናሉ። (ማቴ.26:29፤ ሉቃ.24:39-43፤ ዮሐ.20:27) በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል በሺሁ መንግስት ዘመን ለዚህ ዓለም ኑሮ የተገባች ትሆናለች። ጌታዋንም በሥጋዋ የምታገለግል ትሆናለች። ይህም ማለት በተፈጥሮ በሥጋና በደም ማለት ነው (ዕብ.2:14)። በሺው መንግስት ዘመን አይሁድ የከበረው ጌታ ተገዢዎች ሲሆኑ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ግን ከከበረውና በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ጌታ ጋር እብረው የሚገዙ ይሆናሉ። (2ጢሞ.2:12፣ ማቴ.19:18)

## 5. ኢየሩሳሌም - ለዓለም የደህንነት ማዕከል

ሁልጊዜ ኢየሩሳሌም በምድር ላይ የእግዚእብሔር ዋና የዓለም ከተማ በመሆን ቆይታለች። እግዚእብሔር ክብሩ በኢየሩሳሌም እንጂ በሌላ ከተማ እንዲቀመጥ ፈቅዶ አያውቅም። በብሉይና በአዲስ ኪዳን «የታላቁ ንጉስ ከተማ» በተባለችው እንጂ (መዝ.(48):2፤ ማቴ.5:35)።

በነቢዩ ሕዝቅኤል ዘመን የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌም ተለየ። ምክንያቱም እስራኤል ሕዝብ ንስሃ ያልገቡ ፀመሆናቸውና ወደ እግዚአብሔር ባለመመለሳቸው ነበር (ሕዝ.11:22-24)። ይህም ቢሆን ጌታ ከተማዋን አይጣላትም ነበር ነቢያቱ እነጋገር «ኢየሩሳሌምን ዳግመኛ ይመርጣል» (ዘካ.2:12) በኢየሩሳሌም መካከል እኖራለሁ» (ዘካ. 8:3) «እንደገና ወደ መቅደሱ» ይመጣል (ሚል.3:1፣ ሕዝ.43:1-5)።

እነዚህ ትንቢቶች በከፊል የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ኢየሩሳሌም በገባና «ቅደሱን ባነፃ» ጊዜ ተፈጽመዋል። (ሉቃ.19:46-47) ሆኖም ገና በሙላት

አልተፈጸሙም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ሆኖ የሺሁ ዓመት መንግስት ለመትከል ሲመለስ፣ በዚያን ጊዜ የጌታ ክብር በኢየሩሳሌም ወደ ተሠራው አዲሱ ቤተ መቅደስ ይመለሳል:: (ሕዝ.43:1-5) የኢየሩሳሌም ጎዳናዎች በአጠቃላይ በደስታ ይሞላሉ:: ምክንያቱም ጌታ ለከተማዋ ከሰጣት በረከተቶችና ሰላም የተነሳ ይህ ይሆናል (ኤር.33:9-11):: ሕዝቡ ከትልቅ ደስታ ጋር ሐዋርያት በታላቅ ምስጋና

**«ክብሩን አይተናል»** ይላሉ:: (*ዮሐ.1:14*)

ኢየሩሳሌም በዓለም ላይ የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ትሆናለች (*መዝ*.(87):3):: ምክንያቱም ጌታ በአካል በእርሷ ውስጥ ስለሚገኝ:: ከተማዋ «የቅድስና»፣ «የጽድቅና»፣ «የእምነት» ከተማ ብቻ አትሆንም (ኢሳ.1:26-27፣ 4:3-6):: ነገር ግን በሚያንጸባርቅና አስደናቂ በሆነው በእግዚአብሔር ውበት የምታንጸባርቅ ትሆናለች (ኢሳ.62:1-3):: ወደ ከተማዋ ርኩስ የሆነ ሁሉ አይገባባትም (ኢሳ.52:1፤ ዘካ.2:11):: በፈረሶች ላይ ያለው ሻኩራ ላይ እንኳን «ለእግዚአብሔር የተቀደሰ» የሚል ጽሑፍን የያዘ ይሆናል:: (ዘካ.14:20)

*«በዚያም ዘመን ኢሩሳሌምን የእግዚአብሔር ዙፋን ብለው ይጠሯታል፣ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርስዋ ይሰበሰባሉ፣ ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሔዱም» (ኤር.3:17)::*

በሺሁ ዓመት የጌታ በምድር ላይ ተገልጾ መገኘት በአሕዛብ ላይ ትልቅ ሚና ይኖረዋል:: ምክንያቱም :-

*«ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ታላቅ ይሆናልና፣ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፣ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ፣ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ሆኗልና፣ ይላል የሠራዊት ጌታ» ስለሚል ነው:: (ሚል.1:11)*

አህዛብ «ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ዘንድ... በየዓመቱ» ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣሉ:: (*ዘካ.14:16*) እርስ በእርሳቸው :-

*«ከጽዮን ሕግ፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና፣ ብዙዎች አሕዛብ ሔደው ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፣ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፣ በፍለጋው እንሔዳለን» ይባባላሉ:: (ሚል.4:2)*
የእስራኤል ልጆችም ይህችን ከተማ ይናፍቋታል:

*«በኤፍሬም ተራሮች ላይ ያሉ ጠባቆች ተነሱ ወደ ጽዮን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር እንውጣ ብለው የሚጮኹበት ቀን ይመጣል» (ኤር.31:6)::*





ንጉስና መሲህ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት የተነሳ በሺው ዘመን መንግስት ጊዜ በዚህ ምድር የእግዚአብሔር ዋና ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም ለመላው ዓለም የደህንነት ማዕከል ትሆናለች:: ሰዎች ወደዚህች ከተማ በመምጣት ደህንነትን ይፈልጋሉ፣ ደህንነትንም በዚህች ከተማ ያገኛሉ:: ምክንያቱም «ሕግ ከጽዮን፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና»(ሚክ.4:2)

*«ስለ ጽዮን ዝም አልልም፣ ስለ እየሩሳሌምም ጸጥ አልልም ፣ጽድቅዋ እንደ ጸዳል፣ ማዳንዋም እንደሚበራ ፋና እስኪ ወጣ ድረስ» (ኢሳ.62:1)*

## 6. ጽድቅና ሰላም - የመንግሥቱ ባሕርያት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሺሁ ዓመት መንግስት አገዛዙን ሲመሠርት ረጅምና አስቃቂ በሆነው በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላምና ፍትህ ያለው አገዛዝ በምድር ላይ ይሆናል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ «የጽድቅ ንጉስ» ብቻ ሳይሆን «የሰላምም ንጉስ» ነው (ዕብ.7:2):: ፍትህ የሌላቸው አገዛዝ ያከትማሉ:: ጦርነቶችና አመጸኝነት ተወግደው በመንግስቱ ታሪክ ብቻ ሆነው ይቀራሉ::

*«በዘመኑ ጽድቅ ያብባል፣ ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው» (መዝ.(72):7)::*

*«ዓይኑም እንደምታይ አይፈርድም! ጆሮውም እንደምደትሰማ አይበይንም:: ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል! ለምድርም ድሆች በቅንነት ይበይናል! በአፉም በትር ምድርን ይመታል፣ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል» (ኢሳ.11:3-4)::*
*«የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ! የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል» (ኢሳ.11:5)*

### የሺሁ ዓመት ጽድቅ

ክድካማቸው የተነሳ ግብረ ገባዊነት ያላቸው ክግብ ሲያደርሱ ያልቻሉትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኃይላቸው ሲመሠርቱ ያልቻሉትን ገና ቤተ ክርስቲያናትም ለመፈጸም የሞከሩትንና የደከሙበትን፣ በመሲሁና የእግዚአብሔር ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ርህራኄና ትክክለኛ አገዛዝ ስር እውን ይሆናሉ:: ለሕዝብ ሁሉ ትክክልና ፍጹም የሆነ አስተዳደር ይሆናል:: የብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔር ልጅ ሲመለስ ምን እንደሚሆን አውጀዋል:: አዋጁም:-

*«እነሆ! ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጥ የሚነሳበት ዘመን ይመጣል ይላል እግዚአብሔር፣እርሱም እንደ ንጉስ ይነግሳል፣ይከናወንለታልም፣በምድርም ፍርድንና*

*ጽድቅን ያደርጋል። በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፣ የሚጠራበትም ስም፡- እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው (ኤር.23:5-6)።*

ጻድቁ ንጉስ «ለችግረኞች ሕዝብ በጽድቅ ይፈርዳል፣ የድሆችንም ልጆች ያድናል፣ ክፉውንም ያዋርዳል» (መዝ.(72):4)። የደካሞችን ጩኸት ይሰማል፣ «ከግፍና ከጭንቀት ነፍሳቸውን ያድናል» (መዝ.72:14)። ክፉውን ይመታል፣ «በአፉም በትር ምድርን ይመታል፣ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል» (ኢሳ.11:4)።

*«የዋሃን ደስታቸው በእግዚአብሔር ይበዛል። በሰዎች መካከል ያሉ ችግረኞችም ሐሤትን በእስራኤል ቅዱስ ያደርጋሉ። ጨካኝ ሰው አልቆአልና፣ ፌዘኛውም ጠፍቶአልና ለኃጢአትም ያደፈጡ ሁሉ ይቆረጣሉና»* (ኢሳ.29:19-20)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች በሺሁ ዓመት መንግስት ኃጢአተኞች መኖራቸውንና ኃጢአተኞችም እንደሚፈረድባቸው ጭምር ያመለክታሉ (ኢሳ.65:20) ሁልጊዜ እውነተኛ ጽድቅ በኃጢአት ላይ የመፍረድንም ነገር አጣምሮ የያዘ ነው። ሰይጣን የታሰረና ሰዎችን የማያታልል ስለሆነ በሽው ዘመን መንግስት ያለው ፍርድ ከምንጊዜም ይልቅ የጠነከረ ይሆናል (ራዕ.20:13)። ይህ በማንኛውም መንገድ ለመበደል በሚያስብ ግለሰብ ላይ የበለጠ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን የሚያበዛ ነው። የእውነተኛው ፍትህ ንጉስ ፍጹም የሆነ ጻድቅ ፈራጅ ይሆናል። በዚህ ዘመን በሰውና በእግዚአብሔር ላይ የሚደረገው ኃጢአት እንደ በፊቱ ሳይሆን የቀነሰ ይሆናል።

የሰማያዊ ንጉስ የአገዛዙ ሥርዓት ብለን የምንጠራው የተራራው ስብከት በዚህ ቦታ የሚነበብ ብቻ አይሆንም። (ማቴ. 5:7-29) የፍጹም ጽድቅ የሞራል መለኪያ ይሆናል። በመሲሁ ዘመን፣ እምነት፣ ተስፋ ፍቅርና መልካምነት ከሕዝብ ሁሉ የሚፈለጉ ይሆናሉ። ይህን እውነተኛ ጽድቅ መፈጸምና ማድረግ የሚችለው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ «የጽድቅ ንጉስ» የሆነው ብቻ ነው።

## የሺሁ ዓመት ሰላም

ቃየል አቤልን ከገደለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ዓለም የማያቋርጥ የጦር ሜዳ ሆናለች (ዘፍ.4:8)። ይህ በሺዎች ዓመታት የሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያልተለወጠና አሁንም ያለ ነገር ነው። ዘለቄታ ያለው ሰላም በሕዝቦች መካከል እንዲኖር (ትጥቅን ለማስፈታት) የተደረጉ ስምምነቶች፣ የሰላም ስምምነቶችና ሌሎችም ጥረቶች ሁሉ ውጤት አልባ ሆነዋል። ክፋት የተሞላባቸው ጦርነቶችና ጥፋት አልጠፉም። በተቃራኒው ግድያ እየበዛ ሄዷል። ዛሬ የዘመኑ ቴክኖሎጂ





ባፈራቸው የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም የሚደረጉት ጦርነቶች ከምንጊዜውም ይልቅ የሚያስከፉና አስፈሪዎች ሆነዋል።

ዓለም (በዳን.7:1-28) በተጠቀሱት አስፈሪ አራዊት አገዛዝ ኃይል እስካለች ድረስ እነዚህ የጥፋት ሁኔታዎች የማያቆሙ ናቸው። ሰይጣን «ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ» የሆነና በዚያው የሚቀጥልም ስለሆነ። (ዮሐ.8:44) በእርሱ ቁጥጥር ስርም ያሉት ሁሉ ከእርሱ የሚወርሱት ሌላ ሳይሆን ግድያን፣ ጦርነትን፣ ሞትንና ጥፋትን ብቻ ነው። በመሲሁ ዘመን እነዚህ አስከፊ ሁኔታዎች ያበቁ ይሆናሉ። የነገሥታት ንጉስ (ራዕ.19:16) የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው «የሰላም አለቃ» (ኢሳ.9:6) ሆኖ ዓለምን «በብረት በትር» (መዝ.2:9) እየገዛ (ኤር.23:5) «ፍርድንና ጽድቅ» ሲያደርግ ሲገመቱ የማይችሉ ነገሮች ይከናወናሉ።

*«በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፣ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል፣ ሰይፋቸውን ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፣ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም» (ኢሳ.2:4።)*

ይህ ለረጅም ጊዜ ይጠበቅ የነበረው የመንግስታት ትጥቅ የመፍታት ጅማሬ ይሆናል። የጦር መሣሪያዎች ይደመሰሳሉ፣ ለጦርነት የሚደረገው ጥሪ ያበቃል። ታንኮች ቀልጠው ማቀዝቀዣ መሥሪያ ይሆናሉ። ለወታደሮች የሆነው ባጀት ለበጎ ሥራ የሚውል ይሆናል። ወታደሮች ከሥራቸው የተሰናበተ ይሆናሉ። የመከላከያ ሥርዓት የተሻረ ይሆናል። ለመጀመሪያ ጊዜ የአውቶሚክ ኃይል ለሰላም ሥራ ጥቅም ላይ ይውላል። ዛሬ ተረት መስሎ የሚታየው የሚነገረው ነገር በሺው ዘመነ መንግስት እውን ሆኖ ይታያል። ይህም እውነተኛና ፍጹም የሆነው ሰላም በምድር ላይ (ሉቃ. 2:14) እውን ሆኖ ይታያል። ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰላም ንጉሥ» ከሆነው በቀር ይህን፣ ማንኛውም ሰው፣ መንግስት፣ ድርጅት፣ የሰው ሀሳብና ማንኛውም ዓይነት ትምህርት ሊመሠረት አይችልም።

## 7. የፍጥረት መዋጀት - የሁሉም ነገር መታደስ

የሺውን ዓመት መንግስት በረከቶች ካለፈው የዓለም ጊዜና ከደህንነት ታሪክ ጋር ልናወዳድረው አንችልም። ይህ ጊዜ በጣም የተለየ ጊዜ ይሆናል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የከበረው ጌታ በኢየሩሳሌም መሪ ስለሚሆንና ሰላምና ፍጹም የሆነ የጽድቅ አገዛዝ በምድር ላይ በእርሱ በኩል ስለሆነ ብቻ አይደለም። የመሲሁ የሰላም መንግስት ውጫዊ ገጽታዎች አስቀድመው በዓለም ላይ ከነበሩት መንግስታት የተለዩ ይሆናሉ። ከዚህ ቀጥሎ ጥቂቶቹን በምሳሌነት እንመልከታቸው።

*ኢየሩሳሌም «የትልቁ የንጉሡ ከተማ» የሆነችው በምድር ላይ ካሉት ይልቅ ከፍ ባለው ተራራ ላይ ትሠራለች» (ኢሳ.2:2)::*

*ፀሐይ «አሁን ከምታበራው ይልቅ ሰባት እጥፍ የደመቀች ትሆናለች ጨረቃም «አሁን ፀሐይ ያላትን ድምቀት ያህል ትደምቃለች» (ኢሳ.30:26)::*

የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ሰው እንኳን ጎልማሳ ሆኖ ይቆጠራል:: የዕድሜ እርዝማኔ አዳምና ማቱሳሉ እንደኖሩበት ለብዙ መቶ እመታት የረዘመ ይሆናል (ኢሳ.65:20፣ ዘካ.8:4፣ ዘፍ.5:1-32):: የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ በሚሞትበት ጊዜ የተረገመ ኃጢአተኛ እንደሆነ ተደርጎ ይገመታል (ኢሳ.65:20::)

እንሰሳትና እራዊት ለማዳዎች ይሆናሉ፤ እርስ በእርሳቸውም አይበላሉም:: ተኩላዎች ከበጎች ጋር፣ ነብሮች ከፍየሎች ጋር አብረው ይተኛሉ:: ታናሽ ብላቴና ጥጆችን፣ የአንበሳ ደቦሎችንና ከብቶችን በአንድነት አብሮ ይመራቸዋል:: ከብቶችና ድቦች በአንድ መስክ ላይ ለግጦሽ አብረው ይሰማራሉ:: አንበሳ ገለባ ይበላል፣ ሕፃን ልጅ ከዚህ በፊት መርዘኛ ከነበሩት ከኮብራና ከእፉኝት ጋር ይጫወታል:: በምድር ላይ በእንስሶችና በእራዊት ላይ ሰላም ይሆናል (ኢሳ.11:6-8፣ 65:25፣ ሮሜ.8:19-25)::

በአዳም ኃጢአት ምክንያት የተረገመችው ምድር ከእርግማን ትፈታና እስራኤል እንደ ገና እንደ ኤደን ገነት ታብባለች:: (ዘፍ.3:17-19፤ ኢሳ.27:6፣ 51:3 ፤ሕዝ.36:35) በረሃዎች ለም ምድር፣ ምድረ በዳዎች ፍሬ የሚያፈሩ ይሆናሉ:: (ኢሳ.41:18-19) ተራሮች በእህል በወይን ጠጅና ዘይት የተሞሉ ይሆናሉ:: ሰዎች በወቅቱ ያርሳሉ ያመርታሉ፣ ይተክላሉ:: የወይን ፍሬያቸውንም ይሰበስባሉ (አሞ.9:13-14):: ምርቱ የተትረፈረፈ ከመሆኑ የተነሳ ረሃብ ያለፈ ሙት ነገር ይሆናል:: (ኢሳ. 49:10፤ ኢዩ.2:19-24)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች በቂ ናቸው:: እነዚህ ትንቢቶች በመላ የዓለም ታሪክ ውስጥ ያልተፈጸሙ እንደሆኑ እንገነዘባለን:: ነገር ግን ወደ ፊት እንደሚሆኑ እንጠባበቃለን:: እነዚህ እውነተኛ የምድር ዳግም ልደት ስለሆነው ስለ መላ ዓለም መታደስ ይናገራሉ (ማቴ.19:28):: እግዚአብሔር ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ የተናገረው «የመታደስ ዘመን» ይሆናል:: (ሐሥ.3:21) የክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ተፈጥሮን በሙሉ ያካተተ ነው:: በሰማያዊው ንጉስ አገዛዝ ሥር ፍጥረት ሁሉ ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ ይመለሳል:: ዛሬ ፍጥረት ሁሉ «የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል» (ሮሜ.8:19):: ጌታ ኢየሱስ የመሲሁን ሰላማዊ መንግስት ሊመሠርት እስከ





ሚመጣበት ጊዜ ድረስ ፍጥረታት «ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥተው፣ ወደ እግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነጻነት» ከቶ እይደርሱም (ሮሜ.8:21)::

## 8. የሺሁ ዓመት መንግስት ፍጻሜ የዓለም ዘመን ፍጻሜ

በሺሁ ዓመት መጨረሻ ላይ ሰይጣን እንደገና ከእስራቱ ይፈታና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማሳት ኃይሉን ይገልጻል::

«ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፣ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አህዛብ ጎግንና ማጎግን እዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፣ ቁጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው» (ራዕ.20:7-8)::

ሰይጣን ከእስራቱ የሚፈታበት ምክንያት በሺው ዓመት መንግስት የሚኖሩት ሕዝቦች የራሳቸው ምርጫ እንዲኖራቸው ነው:: (ጌታን ኃይሉንና ክብሩን ለሺህ ዓመታት የተለማመዱትን ወይም ለሺህ ዓመታት በጥልቁ ታስሮ የነበረውን የተሸነፈውን ጠላት ሰይጣንን) :: እያንዳንዱ ሰው የራሱን ምርጫ ይወስናል:: ሆኖም ውጤቱ ለማመን በጣም የከበደ ይሆናል:: በጌታ ላይ ዓለም አቀፍ የሆነ የሕዝብ አመጽ ይሆናል:: ከአራቱ የምድር ማዕዘናት ጎግና ማጎግ በመነሳት ወደ ኢየሩሳሌም ዘመቻ ያደርጋሉ:: (ጎግና ማጎግ ዓመጸኛ ሕዝቦች መግለጫ ሲሆን በመሳሳት በሕዝ.38 እና 39 ላይ ካለው ማጎግ ጎግ ጋር እንዳናገናኘው ልንጠነቀቅ ይገባናል)::

*«ወደ ምድር ስፋት ወጡ፣የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ»*(ራዕ 20:9)

አንድ ጊዜ የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ በዓለም ከተታለሉት ሕዝቦች ጌታንና ሰማያዊ ቅዱሳንን በአርማጌዶን ጦርነት ላይ ለመዋጋት ብዙ ሠራዊት ሰብስቦ ነበር:: አሁን ደግሞ ሰይጣን ራሱ በመሲሁ የሰላም መንግስት ዘመን የነበሩትን ሕዝቦች በንጉሳቸውና በቅዱሳን ላይ ጦርነት እንዲያደርጉ ያስታቸዋል:: በዚህ ቦታ ጦርነት አይካሄድም:: ለዚህ ለመጨረሻውና ከፍተኛው ለሆነው በእግዚአብሔርና በከበረው ጌታ ላይ ለተደረገው አመጽ ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን መልስ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ተጽፎ ይገኛል::

*«እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው»* (ራዕ.20:9)::


ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ «የነጩ ዙፋን ፍርድ» ተብሎ በሚጠራው ፍርድ ሰይጣን ይፈረድበታል (ራዕ.20:10-15)::

## ሦስቱ የድነት ዋና መስመሮች በጊዜና በዘላለማዊነት ማቋረጫ መንገድ ላይ መገናኘት

# የመጨረሻው ፍርድ

ይህ ፍርድ የዚህ ዓለም የመጨረሻው ፍርድ ይሆናል:: ከዚህ በኋላ የሚሆን ሌላ ፍርድ የለም:: የሚከናወነውም በመጨረሻው ቀን በዓለም ፍጻሜና በዘላለማዊነት ማቋረጫ መንገድ መካከል ነው:: ከዚህ እግዚአብሔር ለብዙ ሺህ ዓመታት ከሶስቱ የሰው ዘሮች ጋር ያደረገውን የደህንነት ታሪክ የሚያመለክቱት ሦስቱ ዋናዎቹ የደህንነት መሰመሮች ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ:: ከእስራኤልና ከአሕዛብ የዳኑት ሕዝቦች ሁሉ (በአጠቃላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን) ወዲያውኑ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር ይገባሉ (ኢሳ 65:17፤ 2ጴጥ 3:13፤ ራዕ. 21: 1-2):: ነገር ግን በዘመናት ሁሉ አመፀኞች የሆኑትና ያልዳኑት ሕዝቦች በእግዚአብሔር ፊት በመጨረሻ የነጩ ዙፋን ፊት በፍርድ የሚቀርቡ ይሆናሉ:: ፍርዱም:-

1. በሰይጣን ላይ ራዕ 20:10
2. አሁን ባሉት ሰማይና ምድር ላይና ራዕ 20:1፣
3. ባልዳኑት ሕዝቦች ላይ የሚሆን የእሳት ፍርድ ነው:: (ራዕ 20:15)




## የሰይጣን መፈረድ

ሰይጣን የሚፈረድበት የዓለምን ሕዝቦች በእግዚአብሔርና በመሲሁ ላይ እንዲያምፁ ካደረገ በኋላ በሺው ዓመት መጨረሻ ላይ ነው:: (ራዕ 20:98)

«ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳትና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣሉ፣ ለዘለዓለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ::» ራዕ 20:10

ይህ የትልቁ አሳች ፍፃሜ





ይሆናል በመጨረሻ የሚፈረድበት የሰይጣን ሰስትዮሽ ከሆኑት የመጨረሻው ዲያብሎስ ነው:: እርሱ አንድ ጊዜ ሰውን በመፈተን ለውድቀት በመዳረግ ያደረሰና ለብዙ ሺ ዓመታት ሰውን በኃጢአት ሕይወት፣ በአመጽና በሞት የገዛ ነው:: የእግዚአብሔ:ር ልጅ በጎልጎታ መስቀል ላይ እስካሸነፈው ድረስ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እቅድ ላይ ያሴርም ነበር:: ይህ የእግዚአብሔርና የሰው ልጆች ጠላት የሆነው ክፉ በቅርብ ጊዜ የመጨረሻ ፍርዱን ያገኛል:: ይህም የሚሆነው የክርስቶስ ተቃዋሚና ሀሰተኛውን ነቢይ ወደ ተጣሉበት የዘላለም ጥፋት በመጣል ይሆናል (ራዕ. 19:20):: ከዚህ ፍርድም በኋላ « የዚህ ዓለም አምላክ » አይሆንም ኃይሉ ለአንድ ጊዜና ለዘለአለም የተሰበረ ይሆናል (ዮሐ 12:31):: በዚያ ቀን ኢየሱስ ክርስቶሰ በጎልጎታ መስቀል ላይ የጀመረው ድንቅ የሆነው ድል ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነትን ያገኛል:: ከዚህ በኋላ « ዘንዶው፣ የቀደመው እባብ፣ ዲያብሎስ፣ ሰይጣን » (ራዕ 12:9) የተባለው አያስትም፣ አያጠፋም፤ ኃጢአትና ሞት ከዚህ በኋላ ከቶ አይኖሩም::

## የሰማይና የምድር መፈረድ

በሰይጣን ላይ ፍርድ ከተካሄደ በኋላ፣ የመጨረሻው ፍርድ በዚህ ዓለም ላይ ይሆናል::

*« ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፣ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ፣ ስፍራም አልተገኘላቸውም» (ራዕ 20:11) «ምድር ከሰው ውድቀት ጀምሮ በሰው ኃጢአት ምክንያት በሞትና በአመፅ ስለተበከለች ከእግዚአብሔር ፊት ልትሸሽ ይገባታል (ኢሳ 24: 1-3)::*

ሰማይም ከእግዚአብሔር ፊት ሊሸሽ ይገባዋል:: ምክንያቱም የብርሃን መልእክ የነበረው ሉሲፈር (የንጋት ኮከብ) በኃጢአት ስለ ወደቀ፣ ሰይጣን (ጠላትም) ስለ ሆነና ክፉ መናፍስት በሰማይ ስፍራ ይገዙ ስለነበር ነው (ኤፌ 2:2፣ 6:12፤ ኢዮ 15:15)::

ይህ ፍርድ ሲከናወን የዓለም ፍፃሜ ይሆናል:: « ሰማያትና ምድር፣ ባሕርና የብስ » ከመሰረታቸው ይናወጣሉ (ሐጌ 2:6) :: ምድርም እንደ ሰከረ ሰው ትንገዳገዳለች፣ እንደ ዳስ ትወዛወዛለች» (ኢሳ 24:20) :: ምድርም « እንደ ልብስ ታረጃለች» «እንደ ጢስም በንና» ትጠፋለች (ኢሳ 51:6):: ሰማያትም « እንደ

መፅሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ» (ኢሳ 34:4፤ ራዕ 6:14) ። የሰማይም ፍጥረታት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣሉ፣ ሰማይ በሙሉ ከግምት በላይ በሆነ ሁኔታ በታላቅ ድምፅ ይጠፋሉ (2ኛ ጴጥ. 3:10፣12 ኢሳ. 24:19፣20)። ጌታ ኢየሱስ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ብሏል (ማቴ. 24:35)። በዚያን ቀን ይህ ቃል ይፈፀማል። ሰማይ በጠቅላላ በምድጃ ውስጥ እንዳለ እሳት ይነድዳል። የሚታዩት ነገሮች ሁሉ እንዳሉ ይጠፋሉ። በራዕይ 20:11 «ስፍራ አልተገኘላቸውም» ተብሎ እንደተፃፈው ከዚህ ፍርድ በኋላ ከትላልቆቹ ከዋክብት ጀምሮ እስከ ትንሿ አተም ድረስ ምንም አይቀሩም። ስለሆነም የሚታየውና የማይታየው አሮጌው ፍጥረት ወደ ፍፃሜው ይመጣል። ይህም የእሳት ፍርድ ፍጥረት ላደረገው አመፅ የኃያሉ እግዚአብሔር ምላሽ ነው (ራዕ. 20:8-9)። በተጨማሪም በሰማይና በምድር ላይ ባለው ኃጢአት ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር የፅድቅ ፍርድ ይሆናል። በታላቁ ነጩ ዙፋን ላይ ያለው ትክክለኛው ፈራጅ ጌታ ኢየሱስ ነው። ምክንያቱም አባቱ ፍርድን ሁሉ ለእርሱ ሰጥቶታልና።

*« ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም፤ የሰው ልጅም ስለ ሆነ የፍርድ ስልጣን ሰጠው » ዮሐ 22:27*

ፃድቅ የሆነውና ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአተኞች ሁሉ ኃጢአት ስለተፈረደበት በዚህ ምክንያት አባቱ እርሱ ብቻ ዓለምን በፅድቅ እንዲፈርድ ሥልጣንን ይሰጠዋል (ሐሥ. 17: 31)። በመጨረሻው ፍርድ ሰማይና ምድር ከእርሱ ፊት የሚሸሹት ስለዚህ ነው።

## ያልዳኑት ኃጢአተኞች ፍርድ

በራዕይ 20: 11-15 ያለው የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ባልዳኑት ኃጢአተኞች ላይ የሚሆነው የመጨረሻው ፍርድ ነው። ያለ እግዚአብሔርና ያለ ክርስቶስ የሞቱት የማያምኑት ሰዎች እግዚአብሔር በሕያዋንና በሙታን ላይ እንዲፈርድ በወሰነው ፊት ለፍርድ ይቆማሉ (ሐሥ. 10:42፤ 1ጴጥ 4:5)።

*« ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፣ መፃሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መፅሐፍም ተከፈተ፤ እርሱም የሕይወት መፅሐፍ ነው፣ ሙታንም በመፃህፍት ተፅፎ እንደ ነበር እንደ ስራቸው መጠን ተከፈሉ » ራዕ 20: 12።*





አማኞች በነጩ ዙፋን ፍርድ አይቀርቡም። ጌታ ኢይሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኃጢአታቸውን ፍርድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምትክ ሆኖ ስለ ተሸከመላቸው አይፈረድባቸውም። እንዲሁም በእርሱ ላይ ባላቸው እምነት ከሞት ወደ ሕይወት ስለተሻገሩ ኃጢአታቸው ዳግም አይታሰብም (ሕዝ. 33:16፣ ማክ 7:19)። በታላቁ የነጩ ዙፋን ፊት የሚቀርቡት ያላመኑ፣ ኃጢአተኞች፣ አመፀኞችና የጠፉት ብቻ ናቸው።

*« ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፣ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈሉ» (ራዕ 20: 13)።*

የዚህ ፍርድ መስኪያ ከሺው ዓመት በፊት ጌታ በሚመሰስበት ጊዜ አሕዛብ ለእስራኤል ካሳዩት ምህረት ከሚደረገው ፍርድ የተለየ ነው። ነገር ግን በነጩ ዙፋን ፍርድ ሰዎች በፍርድ ፊት በመቅረብ እግዚአብሔር እንደ ሥራቸው መጠን ይፈርድባቸዋል። መፅሐፍ ቅዱስ ሰው በስራው ስራ እንደሚፈርድበት ይነግረናል። ምክንያቱም ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር ፊት የሚፀድቀው በሥራው ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለው እምነት ነው። (ገላ 2:16፤ ሮሜ 3:20፣28፤ ኤፌ 2:8-9)።

የነጩ ዙፋን ፍርድ አንድ ሰው የዳነ ነው ወይስ የጠፋ ነው በሚል ጥያቄ ላይ የሚያነጋግር ሀሳብ አይደለም፤ የፍርዱ ጥያቄ ያለቀው ሰውዬው ምድራዊ ሕይወቱ ባበቃ ጊዜ ነው። የነጩ ዙፋን ፍርድ ግን ንስሐ ያልገባው ኃጢአተኛ ሊቀበል ያለውን ቅጣትና የፍርድ መጠን የሚወስን ነው። አዳኙ ጌታ ስለ ገሊላውያን ከተማዎች ስለ ኮራዚ፣ ስለ ቤተ ሳይዳና ስለ ቅፍርናሆም ባለቀስ ጊዜ የተናገረው ከእነዚህ ከገሊላውያን ከተማዎች ይልቅ በፍርድ ቀን ለሰዶም እንደሚቀልላት ነው። ምንም እንኳን ጌታ ኢየሱስ በእነዚህ ከተማዎች ታላላቅ ታምራቶችን ቢያደርግም ሕዝቡ ንስሐ አልገባም ነበር (ማቴ. 11:20-24)። ስለሆነም ሰዎች በሚፈረድባቸው ጊዜ የፍርዱ መጠን የተለያየ ይሆናል። የጠፉት በሙሉ እኩል የሆነ ፍርድ አይቀበሉም። የሚፈረድባቸውም እግዚአብሔርን ባወቁት መጠን፣ ስለ ድነት በተረዱት መጠንና ለሕሊናቸው በመታዘዛቸው መጠን ነው። « ያወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል»፡- « ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፣ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል » (በሉቃስ 12:48ኦ ተብሎ ስለተፃፈ ነው።

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ ማንኛውም ሰው በታላቁ በነጩ ዙፋን ፊት የሚቀርብበት ምክንያት ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ባለመቀበሉ ነው። ነገር ግን የቅጣቱና የፍርዱ መጠን እንደ ሥራው መጠን ይሆናል። በፍርዱ ጊዜ ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ የሰራው ስራ የተመዘገበበት መጽሐፍ ይከፈታል። ልክ እንደ ግል ማህደር በማይጠፋ አመዘጋገብ የማንኛውም ሰው ኃጢአት የተመዘገበ ነው። ማንኛውም በንግግርና በሥራ፣ በሀሳብና በተቃውሞ የተደረገ ኃጢአት የተገለጠ ይሆናል። በዚያም ቀን « ፃድቅ የለም አንድ ስንኳ » በሮሜ 3:10 ተብሎ እንደተፃፈው ቃል ጋር ማንኛውም ሰው የሚስማማ ይሆናል።

የሰማያዊ መዝገብ መጽሐፍ በሚከፈትበት ጊዜ በቀኝና በግራ ያሉት ይለያሉ። ለዚህ ማስረጃ የሮሜ መልዕክት «ቸርነት የሚያደርግ የለም፣ አንድስንኳ የለም » ይለናል (ሮሜ. 3:12) ። ያልዳነው ኃጢአተኛ በታላቁ በነጩ ዙፋን ፊት ለራሱ የሚያሳየውና ለራሱ የሚከላከልበት ምንም ነገር አይኖረውም። ምክንያቱም ስራዎቹ በሙሉ በእግዚአብሔር በኩል የተደረጉ አይደሉምና (ዮሐ 3:21) ። ለእግዚአብሔርና ለሰው ጥቅም የተደረጉ መልካም ራስን የመስዋት ስራዎች በክርስቶስ ፍቅርና ለእግዚአብሔር ክብር በመሆን ካልተደረጉ ዋጋ ቢስ መሆናቸውን ስናይ ይህ የሚያስጨንቀን እውነታ ይሆናል። ሁላችንም እግዚአብሔርን ስናገለግል የምናደርግባቸውን ምክንያቶችና ዓላማዎቻችንን አጥብቀን መመርመር ይገባናል።

የሰዎች መልካም ሥራና ምግባር በምድር ያደረጉት የተፃፉበት መፃሕፍት ብቻ የሚከፈቱ አይደሉም። እግዚአብሔር በሰባቱ የመገለጥ መፃሕፍት እንደገለፀው በሰዎች ላይ ይፈርዳል። ሰባቱም እንደሚቀጥለው ተዘርዝረዋል። እግዚአብሔር ሰዎችን በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የመገለጥ መፃሕፍት ያለ መለየት በተጠያቂነት ስለሚሰጡት መልስ ይይዛቸዋል። የመገለጡ መፅሐፍት የሚከተሉት ናቸው፦

1. ፍጥረት፣ ተፈጥሮና ሰማይ (መዝ. 19:1-7፤ ሐሥ. 14:17፤ ሮሜ 1:19-20)
2. ሕሊና (ሮሜ 2:12-16)

እግዚአብሔር አይሁድንና ክርስቲያኖችን፣ ቀጥሎ ባሉት 5 መፃሕፍት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል።

3. የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መፅሐፍ ቅዱስ (መዝ (138):2 ፤ ዮሐ 17:17)





4. ኢየሱስ ክርስቶስና የማዳን ሥራው (ዮሐ 14:6፣9 ፤ 2ቆሮ 5:19-20)
5. መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ 16:7-11)
6. በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት (ዮሐ. 4: 22 ፤ ሮሜ 9:4-5)
7. በአሕዛብ ታሪክ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት (ዘዳ.32:8፤ኤር18:1-10)።

እግዚአብሔር በጠፉት ኃጢአተኞች ላይ ፍርዱ ፍፁም ትክክል ሆኖ እናገኘዋለን፣ ምክንያቱም ከእነዚህ መፃሕፍት ቀጥሎ « የሕይወት መፅሐፍ » ይከፈታል በእርሱ ውስጥ ማንኛውም ዳግም የተወለደ ሰው ስም ተመዝግቦአል። በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ስማቸው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ይገኛል (ራዕ 3:5፤ ሉቃ. 10:20፤ ፊል 4:3)። ነገር ግን ያልዳኑት ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ ባለማመናቸው ምክንያት ስማቸው ከዚህ ከሕይወት መፅሐፍ ውስጥ ይደመሰስና የሚጠፋ ይሆናል (መዝ. (69): 28፤ ዘፀ 32:32።

*« በሕይወት መፅሐፍ ስሙ ተፅፎ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ» (ራዕ 20:15) ።*

የጠፉት ሰዎች ዕድል ፈንታ እጅግ አስደንጋጭ ይሆናል። መፅሐፍ ቅዱስ ስለ «መከራና ጭንቀት» (ሮሜ 2:9) «ስለ ለቅሶና ጥርስ ስለማፋጨት» (ማቴ. 22:13) ፤ «በውጭ ስላለው ጨለማ» (ማቴ. 8:12)፤ ስለ «ቁጣና ጥፋት» (ዘዳ. 5:9) ፤ «ስለ እቶኑ እሳት» (ማቴ. 13: 42)፤ «ስለ ወሕኒ» (ማቴ. 5:25) «ስለ ገሀነም» ፤(ማር. 9:45) «ስለ ዘላለም ቅጣት» (ማቴ. 25:46)፤ ይናገራል። ደግሞም «ስለማይሞተው ትል» ይናገራል (ማር. 9: 48)፤ «ስለማይጠፋውም እሳት» (ማር. 9: 48)፤ «በዲን ስለሚቃጠል ባህር» (ራዕ. 19: 20) ይናገራል። መፅሐፍ ቅዱስ ለፍርድ « በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ እንደሆነ» ይናገረናል (ዕብ. 10:31) ፤ ለሚጠፉት ሰዎች « አለመወለዳቸውም የሚሻል እንደሆነም» ይናገራል (ማቴ. 26: 24)፤ «የስቃያቸውም ጢስ ከዘለዓለም እስከ ዘላለም» ይወጣል (ራዕ. 14:11)። መፅሐፍ ቅዱሳችን ከዘላለም እስከ ዘላለም ብሎ የተረጎመው ዋናው የግሪኩ ትርጉም መጨረሻ የለሽ እንደሆነ ያመለክታል።

ስለሆነም የመጨረሻው የሆነው አሮጌው ዓለም፣ የሺህ ዓመት መንግስት ባልዳኑት ሕዝብ ላይ በሚካሄደው በእግዚአብሔር ፍርድ ያከትማል:: ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፍርዱ የእሳት ፍርድ ይሆናል:: በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የተካሄዱትን ሦስት ፍርዶች በአጭሩ እንመልከታቸው::

## በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስቱ የፍርድ ሂደቶች

1. የውኃ ፍርድ - የጥፋት ውኃ (ዘፍ. 6 እስከ 8)
2. የደም ፍርድ - የጎልጎታ መስቀል (ዮሐ. 19:30)
3. የእሳት ፍርድ - የትልቁ የነጭ ዙፋን (ራዕ. 20: 10-15)





## የእግዚአብሔር የማዳን ሀሳብ መፈፀም


# አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

በታላቁ ነጩ ዙፋን የሚደረገው ፍርድ የአሮጌው ዓለም ፍፃሜ ይሆናል:: አሁን ፍፁም ወደ ተለየው ዓለም «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር» ወደ ሆነው እንገባለን:: ይህን ፍፃሜ የሌለውንና ለዘላለም በበረከት የተሞላውን አዲሱን ዓለም እንመልከት::

### 1. ዘለዓለማዊነት

በራዕ 21 እና 2 ለዳኑት ለእግዚአብሔር ዝቦች የዘላለማዊነት ጅመሬ ምን እንደሚመስል ይገልፃል:: ዳግም የተወለዱት አማኞች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ::

የእግዚአብሔር ልጅ »ለዘላለም እንደማይጠፉ» ተናግሯል:: ዮሐ 3:16 የዘላለም ይህወት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ህይወት ነው:: የዘላለም ሕይወት ለዘላለም መኖር ያለበት ሕይወት ነው:: ማንም ሰው ይህን ሕይወት ከራሱ ሊያገኘው አይችልም፣ ምክንያቱም «ሁሉ ኃጢዓትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» (ሮሜ.3:23):: «ልጁ የሚያምኑት የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐ. 3:36):: ይህ የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው በክርስቶስ እምነ ዳግም ሲወለድ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስንና የማዳን ሥራውን በሙሉ ልቡና ሕይወቱ ያልተቀበለ ሰው ዳግም ልደትን አያገኝም::



ስለሆነም የመጨረሻው የሆነው አሮጌው ዓለም፣ የሺህ ዓመት መንግስት ባልዳኑት ሕዝብ ላይ በሚካሄደው በእግዚአብሔር ፍርድ ያከትማል፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፍርዱ የእሳት ፍርድ ይሆናል፡፡ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የተካሄዱትን ሦስት ፍርዶች በአጭሩ እንመልከታቸው፡፡

## በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስቱ የፍርድ አይነቶች

1. **የውሃ ፍርድ - የጥፋት ውኃ (ዘፍ. 6 እስከ 8)**
2. **የደም ፍርድ - የጎልጎታ መስቀል (ዮሐ. 19:30)**
3. **የእሳት ፍርድ - የትልቁ የነጭ ዙፋን (ራዕ. 20: 10-15)**





### የእግዚአብሔር የማዳን ሀሳብ መፈፀም


## አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

በታላቁ ነጩ ዙፋን የሚደረገው ፍርድ የአሮጌው ዓለም ፍፃሜ ይሆናል፡፡ አሁን ፍፁም ወደ ተለየው ዓለም «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር» ወደ ሆነው እንገባለን፡፡ ይህን ፍፃሜ የሌለውንና ለዘላለም በበረከት የተሞላውን አዲሱን ዓለም እንመልከት፡፡

**1. ዘለዓለማዊነት**

በራዕ 21 እና 2 ለዳኑት ለእግዚአብሔር ዝቦች የዘላለማዊነት ጅመሬ ምን እንደሚመስል ይገልፃል፡፡ ዳግም የተወለዱት አማኞች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ «ለዘላለም እንደማይጠፋ» ተናግሯል፡፡ ዮሐ 3:16 የዘላለም ይህወት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ህይወት ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ለዘላለም መኖር ያለበት ሕይወት ነው፡፡ ማንም ሰው ይህን ሕይወት ከራሱ ሊያገኘው አይችልም፣ ምክንያቱም «ሁሉ ኃጢዓትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» (ሮሜ.3:23)፡፡ «ልጁ የሚያምኑት የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐ. 3:36)፡፡ ይህ የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ዳግም ሲወለድ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና የማዳን ሥራውን በሙሉ ልቡና ሕይወቱ ያልተቀበለ ሰው ዳግም ልደትን አያገኝም፡፡



ይህም ሰው ለዘላለም ከሚኖረው አዲስ ሰማይና ምድር ለዘላለም ዕድል ፈንታ አይኖረውም:: ወደዚህ ዓለም ለመግባትየሚያስችሉትን ነገሮች የሉትምና፣ ምክንያቱም:-

1. በክርስቶስ ደም ስላልተዋጀና (ኤፌ. 1:7)
2. በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ስላልተወለደ (ቲቶ. 3:5)

ጌታ ኢየሱስ ከብዙ ጊዜ በፊት ታዋቂ ለሆነው ለእስራኤል መምህር ለኒቆዲሞስ « እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውሀና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አይችልም» ብሎ ነግሮታል (ዮሐ. 3:5)::

በንስሐና በዳግም ልደት አዲስ ፍጥረት የሆኑት ብቻ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር ይገባሉ (2ኛ ቆሮ. 5:17) :: ከእግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት የተቀበሉ ስለሆኑ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ::

## 2. ፍፃሜው (መጨረሻው)

እግዚአብሔር ማንኛውንም የማዳን እቅዱን በአዲሱ ሰማይና ምድር ይፈፅማል:: እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ ዓለምን የፈጠረና የተበላሸውንም ያዳነ ብቻ አይደለም:: እርሱ የጎደለውን ሁሉ ያደርጋል:: እንደ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በሦስቱ ሁኔታዎች ውስጥ ይገዛል::

1. የዓለም መፈጠር
2. የዓለም ማዳን
3. የዓለም ፍፃሜ

እንደ ዕብ 12:2 የእግዚአብሔር ልጅ «የእምነታችን ራስና ፈፃሚ» ነው:: ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ለፍፃሜው ዓለም ሰውን እንደሚያድን አጠንክሮ ይናገራል:: መሠረቱና ለዚህ አስፈላጊ የሆነው ነገር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ የተከናወነው የማዳን ሥራ ነው:: ነገር ግን ዳግም የተወለዱት የእግዚአብሔር ልጆች ከግባቸው እስኪደርሱና በሰማያዊ ክብር ዘላለማዊ የሆነውን ሙላት እስኪያገኙ ድረስ በእምነት እንጂ በማየት መራመድ የለባቸውም (2ኛ ቆሮ. 5:7) ::





## 3. የማይናወጠው መንግስት

አማኞች በሙሉ «የማይናወጠውን መንግስት» «የማይጠፋውንና እድፈት የሌለበትን የማያልፈውን መንግስት» ተስፋ ያደርጋሉ:: (ዕብ. 12:28፤ 1ጴጥ 1:4 ) እግዚአብሔር አዲስ ሰማይንና ምድርን ሲፈጥር መንግስቱ ፍፁም ይሆንና በማዳን ታሪክ አዲስ ዘመን ይጀምራል:: ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ እስከ መነጠቅ ቀን ድረስ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወደ ሆነው መንፈሳዊ መንግሥት የክርስቶስን አካል ይሰበስባል:: ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ በምድር ላይ በመሲህነቱ መንግስት ለሺህ ዓመት ይገዛል:: ይህ መንግስት የልጁ (የኢየሱስ) መንግስት ይሆናል:: ሆኖም የመንፈስ ቅዱስና የልጁ መንግስት ወደማይናወጠው ዘላለማዊው አዲስ ሰማይና ምድር ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር አብ መንግስት ይጠቃለላል:: ከዚህ በኋላ ልጁ የተዋጀውን ፍጥረት በሙሉ በአባቱ እግር ስር ካስገዛ በኋላ «እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» (1ቆሮ. 15:28) ::

## 4. የመጨረሻው ግብ

ወደ አዲሱ ሰማይና ምድር የሚገቡት የዳኑት ሕዝቦች ብቻ ናቸው:: ራዕይ 21 እና 22 በጥንቃቄ ብናነብ ሦስቱም የሰው ዘሮች ክፍሎች እንደገና በዘላለማዊው ዓለም ውስጥ መገኘታቸውን እናረጋግጣለን:: እነርሱም

1. የዳኑት አሕዛብ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብርሃን ውስጥ ይመላለሳሉ (ራዕ. 21: 24-26)
2. ከአስራ ሁለቱ የእስራኤላውያን ነገዶች የዳኑት ይገኛሉ:: የአስራ ሁለቱ ነገዶች ስሞች በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም በእንቁ በጌጡት አስራ ሁለት በሮችዋ ላይ ተፅፈው ይገኛሉ (ራዕ. 21:12-13) ::
3. ቤተክርስቲያን በበጉ ሚስትና ሙሽራ በመመሰል በሰማይ ትገኛለች (ራዕ. 21:9)::

ይህ ጌታ የጀመረውን ማንኛውንም ነገር በመጨረሻ ማከናወኑን ወደ ፍፃሜ ማምጣቱን ያረጋግጥልናል:: ማንኛውም ሰው ትክክለኛውን የአዳኙን የክርስቶስ ኢየሱስን መንገድ ቢመርጥ ወደዚህ ግብ ይደርሳል::

**ኢየሱስ ክርስቶስ!!**

*« እኔ መንገድና እውነት፣ ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» በማለት ስላረጋገጠ ነው (ዮሐ 14:6) ::*

## መግለጫ ክፍል 1:

# ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረጎች

የኢየሱስ ክርስቶስ ትስግውትነት (Incurnation) ሰው የመሆን ነገር (የቃስ ሥጋ መሆን) የዘላለማዊው እግዚአብሔር ታላቅ ሚስጢር ነው:: የዚህን ተወዳዳሪ የሌለውን ተዓምራዊ እይታ መረጃ የሚሰጠን መፅሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: ይህ ቀላል የሆነ ጥናት አይደለም:: ስለሆነም የመፅሐፍ ቅዱስን ቅዱሳት መፃሕፍት እርስ በርስ በማስተያየት (በማገናዘብ) ልንተረጉም ይገባናል:: ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ ስብዕና በአዲስ ኪዳን የተዘገበውን ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ጋር በማስተያየት መመልከት አለብን:: ብሉይ ኪዳን መሠረት ያላደረገና በአዲስ ኪዳን ላይ ብቻ ያረፈ የክረስቶ ትስግውትነት ጥናት ግልፅ ስለማይሆን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ልንራመድ እንችላለን:: ስለሆነው ለሚቀጥለው ጥናታችን ሁልጊዜ ወደ ብሉይ ኪዳን በማጣቀስ እንመለከታለን::

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጌታ የአዳኙ የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት የተለያዩ የትውልድ ሐረጎች አሉ:: እነርሱም በ(ሉቃስ 3:23-38) ሌላው ደግሞ (በማቴ. 1:1-17) ውስጥ ይገኛል:: ቀለል ባለ እይታ እነዚህ ሁለት የትውልድ ሐረጎች የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል:: ለምሳሌ ሉቃስ ወንጌል 76 የሆኑ የአባቶች ስም ሲኖሩት የማቴዎስ ወንጌል ደግሞ 42 የአባቶች ስሞችን ይዟል:: ሉቃስ የትውልድ ሐረጉን በዮሴፍ ሲጀምር ማቴዎስ ደግሞ በአብርሃም ይጀምራል:: የሁለቱ የትውልድ ሐረጎች በጥንቃቄ ሲነጻጸሩ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ያሉት ስሞች ተመሳሳዮች ናቸው:: ከዚያ በኋላ የትውልድ ሐረጉ በሁለት የተለያዩ ሐረጎች ይከፈላል:: የመጀመሪያው ከዳዊት እስከ ናታን ሲሆን፣ (ሉቃ. 3: 31) ሁለተኛው ከዳዊት ወደ ሰሞን የትውልድ ሐረግ ያመራል (ማቴ. 1:6) :: በመጨረሻም ሁለቱን የትውልድ ሀረጎች የማርያም እጮኛ የሆነውን ዩሴፍን ይዘግባሉ:: ነገር ግን አንዱ ዮሴፍን የያዕቆብ ልጅ (ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ (ማቴ. 1:16) ብሎ ሲዘግብ ሌላው ደግሞ ዮሴፍን የኤሊ ልጅ አድርጎ ዘግቧል (ሉቃ 2:23):: ዮሴፍ ከናታን ወደ ዳዊትና ከሰሎሞን የሆኑ ሁለት የትውልድ ሐረጎች ሊኖሩት አይችሉም::





### የኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘርንቱ የትውልድ ሐረግ
ሉቃስ እንደዘገበው ሉቃ.3:23-38

ኢየሱስ ክርስቶስ
ማርያም/ ዮሴፍ
ኤሊ
ማቲ
ሌዊ
ሚልኪ
ዮና
ዮሴፍ
ማታቲዩ
አሞጽ
ናሆም
ኤሲሊም
ናጌ
ማአት
ማታትዩ
ሴሜይ
ዮሴፍ
ዮዳ
ዮናን
ሬስ
ዘሩባቤል
ሰላቲያል
ኔር
ሚልኪ
ሐዲ
ዮሳስ
ቆሳም
ኤልሞዳም
ኤር
ዮሴዕ
ኤልአዛር
ዮራም
ማጣት
ሌዊ
ስምዖን
ይሁዳ
ዮሴፍ
ዮናን
ኤልአቄም

ሜልያ
ማይናን
ማጣት
ናታን
ዳዊት
እሴይ
ኢዮቤድ
ቦዔዝ
ሰልሞን
ነዓሶን
አሚናዳብ
አራም
አሮኒ
ኤስሮም
ፋሬስ
ይሁዳ
ያዕቆብ
ይስሐቅ
አብርሃም
ታራ
ናኮር
ሴሮህ
ራጋው
ፋሌቅ
አቤር
ሳላ
ቃይንም
አርፋክስድ
ሴም
ኖኅ
ለሜህ
ማቱሳላ
ሄኖክ
ያሬድ
መላልኤል
ቃይናን
ሄኖስ
ሴት
አዳም

### የኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ዘርንቱ የትውልድ ሐረግ
ማቴዎስ እንደዘገበው ማቴ.1:1-17

አብርሃም
ይስሐቅ
ያዕቆብ
ይሁዳ
ፋሬስ
ኤስሮምን
አራም
አሚናዳብ
ነአሶን
ሰልሞን
ቦዔዝ
ኢዮቤድ
እሰይ
•ዳዊት
ሰለሞን
ሮብአም
አቢያ
አሳፍ
ኢዮሳፍጥ
ኢዮራም
ዖዚያን
ኢዮታም
አንካዝ
ሕዝቂያስ
ምናሴ
አሞጽ
ኢዮሲያስ
ኢኮንያን
ሰላቲያል
ዘሩባቤል
አብዩድ
ኤልያቄም
አዛር
ሳዶቅ
አኪም
ኤልዮድ
አልዓዛር
ማታን
ያዕቆብ
ዮሴፍ/ ማርያም
ኢየሱስ ክርስቶስ

ታዲያ እነዚህ የተሰያዩትን የትውልድ ሐረጎች እንዴት እንገልፃቸዋለን? በማዳን ታሪክ (Salivation History) ውስጥ ምንን ያመላክታሉ? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሁለቱ የጌታችን የትውልድ ሐረጎች እርስ በእርሳቸው አይጋጩም:: ነገር ግን እርስ በእርሳቸው እየተደጋገፉ የእግዚአብሔርን ልጅ ስብዕና ሚስጢር ይገልፃሉ:: በተጨማሪም የአዳኙን፣ የንጉሡንና የመሲሁን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ሆኖ መወለድ የሚገልጡ መለኮታዊ ራዕዮች (መገለጥ) ናቸው::

የደህንነት ታሪክ ቻርት የሁለቱንም የትውልድ ሐረጎች ስሞች ይዟል:: በቻርቱ ዙሪያ በሁለት ትይዩ ቀስቶች ተፅፈዋል:: በስተ ግራ ያለው በርከት ያሉ የኢየሱስ ክርስቶስን የቀድሞ አባቶችን የትውልድ ሐረግ የያዘው በሉቃስ ወንጌል የተመዘገቡት ናቸው:: በስተ ቀኝ ያሉት ደግሞ የአዳኙ የቀድሞ አባታችን የትውልድ ሐረግ የያዘው በማቴዎስ ወንጌል የተመዘገቡት ናቸው:: አብዛኞቹ የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን በማቴዎስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ የዩሴፍ፣ በሉቃስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ ደግሞ የማርያም እንደሆነ ይስማማሉ:: ስለሆነም ሁለት አይነት አቀራረቦች (አቋሞች) ይኖሩናል ማለት ነው:: እነርሱም፡-

1. በሉቃስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ ከማርያም በሥጋ የተወለደው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ መሆኑን ይገልፅልናል (ሉቃስ 3: 23-38) ::
2. በማቴዎስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ እንደ ተስፋ ቃሉ በዮሴፍ በኩል የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥና መሲሁ መሆኑን ያመለክተናል (ማቴ. 1: 1-17) ማለት ነው::

በእግዚአብሔር ልጅ ትስግውትነት (ሰው መሆን) ውስጥ ሁለቱም ማርያምና ዮሴፍ በጣም አስፈላጊ ናቸው:: በመቀጠል ይህንን በበለጠ እንገልፀዋለን::

## 1. የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ እንደ ሉቃስ ወንጌል

አራቱ ወንጌላት ከእግዚአብሔር ቃል ክፍል የሆኑ ድንቅና የተለዩ ናቸው:: እያንዳንዱ በተለያየ ገፅታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስብዕናና ሥራ ይገልፃሉ:: ማቴዎስ ንጉስነቱንና ሥራውን ይገልፃል፣ ማርቆስ አገልጋይነቱን ይገልፃል፣ ዮሐንስ ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅነቱና ክብሩ ላይ ያተኩራል:፤ ነገር ግን ሉቃስ ከሌሎቹ በበለጠ የጌታ የኢየሱስን ስብዕና ይገልፃል:: የሰው ልጅ የሚለው መጠሪያ ገለፃ ለማንያ ሰባት ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል:: በብሉይ ኪዳንም (በዳን. 7:13-14፤ በመዝ. (80):17) ውስጥ ጌታ «የሰው ልጅ» ተብሎ ተጠቅሷል::





በእያንዳንዱ ወንጌላት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጅ በተለያየ መንገድ ይገልፀዋል:: አራቱ ወንጌላት እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ (የሚገላለፁ) ከሆነ የአዳኙን ሙሉ ሰብዕና (ታሪክ) ለማግኘት ሁሉንም ወንጌላቱን መመልከት አለብን:: መፅሐፍ ቅዱስን ስንተረጉም በመንፈስ የተነዱትን ፀሐፊዎች ልዩ የሆነ እይታ በአእምሮ መያዙ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህ ሁለቱን የትውልድ ሐረጎች በተሻለ መንገድ ለመርዳት ይረዳናል:: ስለሆነም በማሳጠር እንመልከታቸው::

- የማቴዎስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ ንጉስነቱ» ላይ ነው::
- የማርቆስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ አገልጋይነት» ላይ ነው::
- የሉቃስ ወንጌል የሚተኩረው «በጌታ ኢየሱስ የሰው ልጅነት» ላይ ነው::
- የዮሐንስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት» ላይ ነው::

## የማርያም የትውልድ ሐረግ ሉቃስ 3:23-38

በመጀመሪያ ሰላምን አብዛኞቹን የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሉቃስ ወንጌል በማርያም የትውልድ ሐረግ ላይ ስለ ማተኮሩ እውነታ ስለ መሰባቸው እንመረምራለን::

ቀደም ብለን እንደ ገለፅነው የሉቃስ ወንጌል በጌታ ኢየሱስ ሰብዕና ላይ የሚያተኩር ነው:: እንደ ሉቃስ ወንጌል የጌታ ኢየሱስን ሰብዕና (ሰው መሆን) በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ የሚገልፅ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌላ መፅሐፍ የለም:: በሁለተኛ ሳሙኤል መፅሐፍ ውስጥ ንጉስ ዳዊት መሲሁና የእስራኤል ንጉስ የሆነው ከእርሱ ዘር እንደሚወለድ ተስፋ እንደተቀበለ ተፅፏል (2ሳሙ. 7:1-29):: ከአንድ ሺ ዓመት በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ በተወለደ ጊዜ ትንቢቱ ተፈፃሚ ሆኗል:: እርሱ የተስፋው የዳዊት ልጅ፣ የዳዊት የትውልድ ሐረግ ቅርንጫፍ፣ ኃያሉ የይሁዳ ንጉስና የእስራኤል ሕዝብ መሲህ ነው:: ሉቃስ በጌታ ስብዕና ላይ የሚያተኩር ከሆነ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ጎላ ብሎ የምናየው በሥጋ (ሰው ሆኖ ስለ መምጣቱ) ስለመምጣቱ ነው (ሉቃ. 3:23-28)::

የኢየሱስ ትውልድ ሐረግ የተያያዙ 76 የትውልድ አባቶችን የያዘ ነው:: ይህም ጌታ በናታንና በዳዊት በኩል እስከ መጀመሪው ሰው እስከ አዳም ድረስ ያለውን የተፈጥሮ ውርስን የሚከተል መሆኑን ያሳያል:: ይህ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ፍፁም ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ይመሰክራል::

(ሕንግዲህ «ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለች» ዕብ 2:14 ተብሎ ተፅፏልና) ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ከተወለደ ጀምሮ በኃጢአት የጠፋ ስለሆነ ክርስቶስ የደህንነት ሥራ ለማከናወን «በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ» ሰው ሆኖ መጣ። በዚህ ምክንያት መፅሐፍ ቅዱስ በአንድ በኩል ዌየሰው ልጅኸ ብሎ ሲጠራው (ሉቃ. 19:10)፤ በሌላ በኩል ደግሞ «የኋለኛው አዳም» ወይም «ሁለተኛው ሰው» ብሎ ይጠራዋል (1ቆሮ. 15:45፣ 47)።

መፅሐፍ ቅዱስ ድንግል የእግዚአብሔርን ልጅ እንደወለደች ያስተምራል (ሉቃ. 1:31-35፣ ኢሳ. 7:14) በሌላ በኩል ደግሞ በመሲሁ እንደ ማንኛውም ሰው የሥጋ አባት የለውም። ስለሆነም በማርያም በኩል በሥጋ እውነተኛው «የዳዊት ልጅ» ነው። ከዮሴፍ ሰብአዊ የሆነ ውርስ የለውም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቻ አባቱ ነውና። የሰው አባት የለውም፣ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ እንጂ (ሉቃ. 1:35፤ ማቴ. 1:18-21) የሉቃስ ወንጌል የትውልድ ሐረግ የሚያጠናክረው ይህንኑ ነው። ዮሴፍ የኢየሱስ አባት አይደለም። ነገር ግን የእርሱ አባት መስሏቸው ነበር (ሉቃ. 3:23) ዮሴፍ ለእግዚአብሔር ልጅ ሞግዚት ብቻ ነበር። ስለሆነም መፅሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሴፍ የወረሰው ስብዕና እንዳለው የሚናገረው የለውም።

ነገር ግን ከማርያም ጋር ያለው የተለየ ነው። መፅሐፍ ቅዱስ ማርያም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች ሴት እንደሆነች ይናገራል (ማቴ. 1:16)። በማርያም በኩል ብቻ ነው የእግዚአብሔር ልጅ ፍፁም ሰው የሆነው «በእርሷ ሰውነት በኩል ነው ጌታችን በሥጋችንና በደማችን የተካፈለው» (ዕብ. 2:14) በእርሷ በኩል ነው የተስፋው «የዳዊት ልጅ» ሆኖ ወደ አዳም ዘሮች የመጣው የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ ማርያም እውነተኛ የዳዊት ቤት ሴት ልጅ ናት ማለት ነው። (ሮሜ 1:3፣ 2ጢሞ. 2:8) የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ከዳዊት ዘር ከሆነ፣ ምድራዊ እናቱ ማርያም ከዳዊት ቤተሰብና የትውልድ ሐረግ የመጣች መሆን አለባት ማለት ነው። በማሳጠር የሚከተለውን ማጠቃለያ እናድርግ (በሉቃ. 3:23-38) ያለው የትውልድ ሐረግ በሥጋ የዳዊት ልጅ ሆኖ የተወለደውን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሰው የሆኑትን አባቶችን ሐረግ የዘገበ ነው። ከአዳም ጀምሮ በዳዊትና በናታን በኩል እስከ ክርስቶስ ያለውን የትውልድ ሐረግ የያዘ ነው። ይህም የዓለሙ አዳኝ ከሰው ዘር የመጣ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ክርስቶስ ስብዕናውን በማርያም በኩል ካገኘና (በሉቃ. 3:23-38) ያለው ከአዳም ጀምሮ ያሉትን ቅድመ አያቶችን የዘገበ ከሆነ ይህ የትውልድ ሐረግ የማርያም የትውልድ ሐረግ ማለት ይሆናል።





በዚህ ትርጉም (አተረጓጎም) ላይ አንድ አስቸጋሪ ነገር አለ ይኸውም የማርያም ስም በዚህ የትውልድ ሀረግ እንዴም አለመጠቀሱና የዮሴፍ ስም በሁለቱም የትውልድ ሐረጎች መጠቀሱ ነው። (ሉቃ. 3:23፤ ማቴ. 1:16) ይህ እንዴት ሊብራራ ይችላል?

## ማርያም የይሁዳ ሕጋዊ ልጅ መሆንዋ

ማርያም የዳዊት ቤት ሴት ልጅ እንደሆነች ቀደም ብለን አረጋግጠናል። ስለሆነም እንደ ንጉስ ዳዊት እርስዋም ከይሁዳ ነገድ ናት እንደ ሉቃስ 3:23-38 ዮሴፍ የኢየሱስ አባት እንዳልሆነ ሆኖም ግን በአባት መመስሉን ጠቅሰናል። ዮሴፍ አንዱ ከናታን ሌላው ደግሞ ከሰሎሞንና ከዳዊት የሆኑ ሁለት የትውልድ ሐረጎች ሊኖሩት እንደማይችል ግልፅ ነው። በሉቃስ የትውልድ ሐረግ ማርያም ያልተጠቀሰችበት ምክንያት አንድ ገለፃ ብቻ አለ። ምንም እንኳን መፅሐፍ ቅዱስ ይህንን በዝርዝርና በግልፅ ባያብራራውም ማርያም ከዳዊት ቤተ ሐረግ ውስጥ መሆንዋ የማይቀር ነው። ይህን እንዴት እናረጋግጠዋለን?

ማንኛውም መፅሐፍ ቅዱስን የሚያውቅ ሰው መፅሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ሲናገር በአመዛኙ ወንዶቹን ብቻ የሚዘግብ እንደሆነ ያውቃል። በጥንት ጊዜ በምስራቁ ዓለም ሕዝባዊ ጉዳዮችን የሚያከናውኑት ቤተሰቦቻቸውን የሚደግፉና ሕዝባዊ ሥራዎችን የሚሠሩት ወንዶች ብቻ ነበሩ፣ ሴቶች ግን በቤት ላለው ሥራ እንደ ልብና ነፍስ ሆነው በቤት ለሚሠራው ሥራ ኃላፊዎች ነበሩ (ምሳ. 31:1-31) ።

አውግስጦስ ቄሳር ግብር ለማስገበር በፈለገ ጊዜ በሮም ግዛት ሁሉና እስራኤልን ጨምሮ የሕዝብ ቆጠራ እንዲደረግ ትዕዛዝ አወጣ። ይህ ሴቶችን የማይመለከት ስለነበር ቆጠራው ቅድሚያ የተሰጠው ለወንዶች ነበር። ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ስንመለከት ይህ ከማርያም ጋር የሆነ እንዳልሆነ እንመለከታለን። በዚያን ጊዜ ለነበረው ልማድና ጠባይ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማርያም ከእጮኛዋ ጋር ሆና ወደ ቤተ ልሔም ለመመዝገብ ተጓዘች።

«ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ወገን ስለ ነበር በገሊላ ካለችው ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ በይሁዳ ወደሆነችው ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይፃፍ ዘንድ ወጣ» (ሉቃ. 2:4-5)።

በእውነት ከሆነ እንደዚህ ያለው ጉዞ ማርያምን የሚጠይቅ አልነበረም። በናዝሬትና በቤተልሔም መካከል ያለው የ170 ኪሎ ሜትር ርቀት በእግር መጓዝን

የሚጠይቅ ነበርና። ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ ቀርቦ ሳለ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ይህን ጉዞ መጓዝ ለእርስዋ አድካሚና የማይቻል ነበር። አደገኛ ጉዞ ስለነበር በእርሷና በሕፃኑ ላይ ችግር ሊፈጠር ይችል ነበር። እድል ቢሰጣት ኖሮ በማንኛው ሁኔታ ይህን ጉዞ አትጓዘውም ነበር። ታዲያ ማርያም ወደ ቤተልሔም ሔዳ በዚህ የሕዝብ ቆጠራ መመዝገብ ለምን አስፈለጋት?

ለዚህ አንድ መልስ ብቻ አለ። ማርያም ግብር ለመክፈል የሚያስችል የሚመዘገብ ውርስ በቤተ ልሔም ይኖራት ይሆናል ስለሆነም ይህን ጉዞ መጓዝ ነበረባት፣ ምክንያቱም ወራሽ ስለነበረች ለርስቷ ግብር ለመክፈል በርስቷ መመዝገብ ነበረበትና።

በዘኍልቁ መፅሐፍ ውስጥ ሴቶች ልጆች ውርስ መውረስ ስለሚገባቸው የተሰጠ የእግዚአብሔር ሕግ ይገኛል። የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች አባታቸው በምድረበዳ ውስጥ ስለሞተና የሚወርሱ ወንዶች ልጆች ስላልነበሩት በእስራኤል መካከል መውረስ እንዲችሉ ጥያቄ ይዘው ከሙሴ ፊት ቀርበው ነበር። ሙሴም ይህን ጉዳይ በእግዚአብሔር ፊት አቀረበና እግዚአብሔርም ሴቶች ልጆች መውርስ እንደሚገባቸው ያለውን ሕግ ሰጠው።

*«የሰለጰዓድ ልጆች እውነት ተናግረዋል፣ በአባታቸው ወንድሞች መካከል የርስት ድርሻ ስጣቸው፣ የአባታቸውን ርስት ለእነርሱ አሳልፈህ ስጣቸው። ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው «ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍ (ዘኁ. 27:7-8) ።»*

በዚህ ሕግ መሠረት ሴቶች ልጆቹ የአባታቸውን ርስት ሁሉ እንዲወርሱ ተፈቀደላቸው። ነገር ግን አንድ የተለየ ሁኔታም ነበር ውርስን የምትወርስ ሴት ልጅ ማግባት ያለባት ከራሷ ነገድ ብቻ ነበር።

*«እግዚአብሔር ስለ ሰለጰአድ ሴቶች ልጆች ያዘዘው ነገር ይህ ነው፦ የወደዱትን ያግቡ፣ ነገር ግን ከአባታቸው ነገድ ብቻ ያግቡ። እንደዚሁም የእስራኤል ልጆች ርስት ከነገድ ወደ ነገድ ምንም አይተላለፍ፣ ከእስራኤልም ልጆች እያንዳንዱ ወደ አባቶቻቸው ነገድ ርስት ይጠጉ። ከእስራኤልም ልጆች እያንዳንዱ ሰው የአባቶቹን ርስት ይወርስ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ ርስት ያላት ሴት ልጅ ሁሉ ከአባቷ ነገድ ባል ታግባ። እንደዚህም ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ምንም ርስት አይተላለፍ፣ከእስራኤልም ልጆች ነገድ እያንዳንዱ ወደ ርስቱ ይጠጋ» (ዘኁ.36:6-9)።*





ስለሆነም ከይሁዳ ነገድ የሆነች ሴት ልጅ ከአሴር ነገድ የሆነውን እንድታገባ አይፈቀድም ነበር። ከተጋባች ወደ አሴር ይዘው ያመጣችው የወረሰችው ውርስ ወዲያውኑ ለአሴር ነገድ ይሆን ነበር። ይህም አልተፈቀደም ነበር። ሴቶች ሊወርሱ የሚችሉት ደግሞ በቤተሰብ መካከል ወንድ ልጅ ከሌለ ብቻ ነበር።

ይህ ሁኔታ በትክክል ማርያምን የሚመለከት ነበር። እርሷ ከዳዊት ቤተሰብ ስለነበረች ከይሁዳ ነገድ ነበረች። ወራሽ ወንድ ልጅ ስላልነበረ ከአባቷ ወርሳ ነበር። ወራሽ ሴት ልጅ በመሆኗ ልታገባ የሚፈቀድላት ከይሁዳ ነገድ ብቻ ነበር። ሕጉ በእርሷ ላይም የሚሠራ ነበርና። ልክ እንደ ማርያም ዮሴፍም «ከዳዊት ቤት ወገን» ስለነበር ከይሁዳ ነገድ የመጣ ነበር። (ሉቃ. 2:4) ይህ ጉዳይ በቤተልሔም በሃይማኖት ሥርዓትና በመንግስታዊ ጉዳይ በሕግ የታወቀ ነበር። ዮሴፍ ማርያምን ሊያጭና እርሷን በማግባት ውርሷን እንዲወርስ ተፈቅዶለት ነበር።

መፅሐፍ ቅዱስ ዮሴፍና ማርያም የመጋባታቸውን እውነታ ያረጋግጥልናል። የሉቃስ ወንጌል ማርያም እጮኛው እንደነበረች በግልፅ ያሳያል (ሉቃ. 2:5)። በዚህ ጉዳይ ላይ ዮሴፍን የሚመለከት ነገር መሆኑ የተረጋገጠ ምክንያት አለ። በእስራኤል የሆነችን ሴት ያገባ ሁለት አባቶች አሉት። ይኸውም ወላጅ አባትና ሕጋዊ የሆነ የሚስቱ አባት ናቸው። በአሮጌው ባሕል መሠረት በሚስቱ የትውልድ ሐረግ ውስጥ የእሱ ስም በግልፅ ይመዘገባል። ስለሆነም ዮሴፍ በሁለቱ የትውልድ ሐረጎ ውስጥ ይታያል። በመጀመሪያ በማቴዎስ ወንጌል የትውልድ ሐረግ ውስጥ ወላጅ አባቱ በሆነው «የያዕቆብ ልጅ» በሚል ተፅፏል (ማቴ. 1:16)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሉቃስ 3:23 በወላጅ አባቱ ላይሆን ሕጋዊ አባት (የማርያም አባት) በሆነው   የኤሊ ልጅ   በሚልተመዝግቧል። አንድ ሰው በሁለት የትውልድ ሐረግ ውስጥ ስሙ ተጠቅሶ ሲገኝ (በእስራኤል የተለመደ ባህል ስለነበር) ምንም ገለፃ የሚያስፈልገው አልነበረም። ምክንያቱም ወራሹ ሴትን አግብቷልና።

በብሉይ ኪዳን ጊዜያት በእስራኤል ሕዝብ መካከል ባለው ባሕል ባል በወራሽ ሚስቱ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ስሙ ይመዘገብ እንደነበር የነህምያ መፅሐፍ ያረጋግጥልናል።

«ከካህናቱም የኤልያስብ ልጆች፣ የአቆስ ልጆች ከገለዓዳዊው ከቤርዜሊ ልጆች ሚስት ያገባ ባለሙያ የተጠራ የቤርዜሊ ልጆች» (ነህ. 7:63) «በስሙም የተጠራ» የሚለው ገለፃ ውርስ የወረሰችውን ሴት ባል በሚስቱ የትውልድ ሐረግ መግባቱን ያረጋግጥልናል። (በአማቹ) በዘኍ 27:1-11 እና 36:1-13 ያለው የሴቶች

የመውረስ ሕግ በዚያን ጊዜ በጥብቅ በሥራ ላይ የዋለ ነበር:: በዚህም ምክንያት በቤተ ልሔም ያለው የማርያምና የዮሴፍ ውርስ በይሁዳ ነገድ ውስጥ መቅረት ነበረበት (ከዳዊት ቤተሰብና ከይሁዳ ነገድ ስለሆኑ) ምንም እንኳን ከቤተልሔም 170 ኪሎ ሜትር በስተሰሜን በዛብሎን ምድር ባለችው በናዝሬት ቢኖሩም ርስታቸው ወደ ሌላ ነገድ መተላለፍ የለበትም ስለሆነም አውግስጦስ ቄሳር ዓለሙ ሁሉ እንዲፃፍ ትዕዛዝ ባወጣበት ጊዜ ረጅምና አድካሚ የሆነውን ጉዞ ወደ ቤተልሔም ለመጓዝ ሁለቱም ተገደዋል:: ምክንያቱም ርስታቸው ስለነበር ነው:: ማርያም በቤተ ልሔም ውርስ ስለነበራት ከባልዋ ጋር ወደ ቤተልሔም ለቆጠራ ለመመዝገብ ሔደች::

ይህ ማርያም ውርስ እንዳላትና ከይሁዳ ነገድ የሆነች ሴት ልጅ ስለመሆንዋ በቂ ማስረጃ ነው:: እስከ አሁን የተነጋገርንበትን ብናጠቃልለው በሉቃስ 3:23-38 የተጠቀሰው ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የማርያም የትውልድ ሐረግ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል::

## 2. የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ እንደ ማቴዎስ ወንጌል

በሚቀጥለው ጥናታችን ሁለት ቀዳሚ ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልገናል::

1. በማቴዎስ 1:1-17 እና በሉቃስ 3:23-38 መካከል ያለው የቤተሰብ ሐረግ ዋነኛ ልዩነት ምንድን ነው?
2. በማቴ 1:1-17 ያለው የትውልድ ሐረግ የዮሴፍ መሆኑን እንዴት እናረጋግጣለን?

በመጀመሪያ ልዩነታቸውን እንመርምር፤ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የማቴዎስ ወንጌል የሚያተኩረው የእግዚአብሔር ልጅ ተስፋ የተደረገው መሲህና የእስራኤል ንጉስ እንደሆነ ነው:: እንደ ማቴዎስ እይታ በፃፈው የትውልድ ሐረግ ላይ ልዩነት አለ፤ በሉቃስ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተሰብ በማርያምና በዮሴፍ በመጀመር በናታንና በዳዊት በኩል አልፎ እስከ አዳም ሲሔድ፣ በማቴዎስ የተዘገበው ያለው የትውልድ ሐረግ ዳግም ከአብርሃም ይጀምርና በዳዊትና በሰሎሞን በኩል አልፎ የማርያም ባል ወደ ሆነው ወደ ዮሴፍ ይደርሳል:: ለእነዚህ ልዩነቶት ምክንያት አሉ:: ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሉቃስ የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ የሚገልፀውና የሚያተኩረው በሥጋ ስለመወለዱ ወይም በእግዚአብሔር ልጅ ስብዕና ላይ (ስብዕናውን) ነው:: ስለዚህ ነው የትውልድ ሐረጉ ወደ መጀመሪያው ሰው ወደ አዳም ያመራው፤ ማቴዎስ የተለየ አቀራረብ አለው:: ምክንያቱም





በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የሚያተኩረው የእስራኤል ንጉስ በመሆኑ ላይ ነው:: ስለዚህ ነው እንደ ሉቃስ አቀራረብ የትውልድ ሐረጉ እንደ ሉቃስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕና ላይ ያልተመሰረተውና ያላተኮረው:: በሌላ መልኩ የመሲሁን ንጉሳዊ የደም ሀረግ ነው የጠቀሰው በጥልቀት ሲታይ ይህ ምን ማለት ነው?

ማቴዎስ የትውልድ ሐረጉን «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መፅሐፍ» በማለት ይጀምራል ማቴ 1:1::

ይህ ጥቅስ የኢየሱስ ክርስቶስን የደም ሐረግ የእስራኤል ሕዝቦች አባቶች ከንጉሳዊ ቤተሰብ ከሆኑትና ዳዊትን በመጥቀስ እስከ አብርሃም ያለውን ያጠናክራል:: ይህን በማድረግ

1. የንጉስ ዳዊት ቤት «ልጅ» ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ነው::
2. «የአብርሃም ልጅ» «ዘር»፣ «ዝርያ» የምድ (አህዛብ ሁሉ የሚባረኩበት ነው:: እንደዚሁም እርሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባለት የኪዳኑ ፍፃሜ ነው:: (ዘፍ 12: 3፣ 18:18፣ ገላ 3:16) የሚለውን እውነት ላይ እንድናተኩር ያደርገናል::

ይህን አስፈላጊ የሆነውን ግንኙነት በተሻለ መልኩ ለመረዳት በብሉይ ኪዳን ያለውን የደህንነትን ታሪክ መለስ ብለን እንደገና መመርመር ይኖርብናል::

እግዚአብሔር አብርሃምን በመረጠበት ጊዜ ከሕዝበ እስራኤል ጋር የደህንነትን ታሪክ የማቀድ ብቻ ሳይሆን የመጪው ንጉስ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ከእርሱ እንደሚሆን መለኮታዊ ተስፋንም ሰጠ:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ምድር፣ ሕዝብና በረከት እንደሚሰጠው ተስፋ ገባለት:: (ዘፍ. 12: 1-39፣ 22:18 ከገላ. 3:16 እስከ ኤፌ. 1:3 ጋር አገናዝቡት):: ከብዙ ዓመታት በኋላ ያዕቆብ የሞቱ ጊዜ በቀረበ ጊዜ አስራ ሁለቱን ልጆቹን ወደተኛበት አልጋ ሊባርካቸው በጠራቸው ጊዜ አራተኛው ልጁ ይሁዳ የተለየ ተስፋ ተቀብሎ ነበር፤ ተስፋውም

የበትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም፣
የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፣
ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፣
የአህዛብ መታዘዝ ለእርሱ ይሆናል የሚል ነበር (ዘፍ 49: 10)::

ከአስራ ሁለቱ ከእስራኤል ነገዶች ይሁዳ የንጉስ ነገድ፣ አንድ ቀን የእስራኤል ንጉስ የሚመጣበት ነገድ ሆነ ይህ ተስፋ ከያዕቆብ በመጀመር በይሁዳ ነገድ ትውልድ በማለፍ አንድ ቀን ነቢዩ ሳሙኤል የበግ እረኛውን ዳዊትን በእስራኤል ላይ ንጉሥ

አድርጎ እስከ ቀባው ጊዜ ድረስ ቀጠለ 1ሳሙ 16: 1-13 በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ይሁዳ የእስራኤል ነገስታት የሚመጡበት ነገድ እንደሆነ ተስፋውን አረጋገጠ:: ዳዊት በኢየሩሳሌም በመላ እስራኤል ሲያስተዳድር እግዚአብሔር ንጉሱና መሲሁ ከእርሱ ዘር እንደሚነሳ ተስፋ ሰጥቶታል:: (2.ሳሙ 7:1-29)

*«ዕድሜህም በተፈፀመና ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሳለሁ፣መንግስቱንም አፀናለሁ» (2.ሳሙ 7: 12-13):*

*«ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፣ ለባርያዬ ለዳዊት ማልሁ፣ ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፣ ዙፋንኑም ለልጅ ልጅ እመሰርታለሁ» (መዝ (89): 3-4) ::*
*«እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ፣ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል:: (መዝ. (89) :27)*

ለሺህ ዓመታት ይህ የታደሰው ተስፋ በዳዊት ንጉሳዊ ሐረግ በኩል አልፎ በመጨረሻ «የዘመኑ ፍፃሜ እስኪደርስና» ለማያዊው ንጉሥ ከድንግል ማርያም በሥጋ ሰው ሆኖ እስከመጣ ጊዜ ድረስ ቀጠለ (ገላ. 4:4):: መልአኩ በናዝሬት የመሲሁን መወለድ ባወጀበት ጊዜ ለዳዊት የተሰጠውን ተስፋ በጥብቅ አረጋገጠ::

*«እነሆም ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል. በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም» (ሉቃስ 1:31-33)::*

ስለሆነም ስለሚመጣው የእስራኤል ንጉስ መሰኮታዊ ተስፋ በአብርሃም ጀመረና፣ በዳዊት መቀባት የእስራኤል መንግስት እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ንጉሳዊ በሆነው በይሁዳ ነገድ ትውልድ በኩል ቀጠለ:: ከዚያም በሰሎሞን ቤትና በሌሎቹም ነገስታት በኩል በመሰኮት የተመሰረተው የእስራኤል መንግስት በባቢሎናውያን እስከተደመሰሰ ጊዜ ድረስ ቀጠለ:: ነገር ግን ተስፋው ሳይነካ በባቢሎናውያንም ማራኪነት ሳይደመሰስ፣ በዳዊት የዘር ሐረግ በኩል የዘላለሙ ንጉስና መሲሁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መጣበትና ተስፋው በክብር እስከተፈፀመበት ጊዜ ድረስ ቀጠለ::





በዳዊት የተጀመረውን ንግስና ጨምሮ መላው የእስራኤል ነገስታት በእግዚአብሔር የተቀቡ ነበሩ:: በዕብራይስጡ «የተቀባው» ለሚለው ቃል «መሲህ» የሚለው ነው:: የተቀባው (መሲሁ) ክርስቶስ የመጣው ለዳዊት ተስፋ ከተሰጠው ሐረግ ነው:: ከዳዊት ቤተሰብ የሆነ በእስራኤል የነገሰ ማንኛውም ንጉስ ለሚመጣው ንጉስ መንገድ የሚያዘጋጀና ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ነበር::

ይህን የደህንነት ታሪካዊ መግለጫ በአእምሮአችን ብንይዝ በማቴዎስ ስለተመዘገበው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ለመረዳት ችግር አይገጥመንም:: ከአብርሃም እስከ ዳዊት፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ያለው ጊዜ ሦስት ዋና ዋና ጊዜያት ሲኖሩት እያንዳንዱም ጊዜ 14 ትውልዶችን የያዘ ነው (ማቴ 1:17):: እነዚህ ሁሉ ትውልዶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከእስራኤል መንግስት ጋር ግንኙነት አላቸው:: ሆኖም ይህ መስመር ከአብርሃም ከዳዊትና ከዮሴፍ እስከ ክርስቶስ ድረስ ሁለት ሺ ዓመታት ጊዜን ወስዶአል:: የእግዚአብሔር ልጅ ስም በዚህ የነገስታትና የተስፋዎች የትውልድ መስመር የመጨረሻው ሆኖ መመዝገቡ መሲህ መሆኑን አስረግጦ ለማስረዳት የታቀደ ዕቅድ ነው:: ይህም የእግዚአብሐር ልጅ የእስራኤል ንጉስ እንደሆነ ካተኮረው ከእርሱ መሰረታዊ እይታ ጋር ይስማማል::

በማቴዎስ ያለውን የትውልድ ሐረግ ከተረዳን የሚነሳውን ሌላውን ጥያቄ ለመፍታት ይረዳናል:: ሁለቱን የትውልድ ሐረጎች ስንመረምር ማቴዎስ ከሉቃስ ይልቅ የዘገበው ጥቂት የአባቶችን የትውልድ ሐረግን ነው:: ማቴዎስ ከጥቂቶች ታዋቂዎች በስተቀር ሁሉንም የትውልድ ሐረግ አላካተተም:: ለምሳሌ ሠቃት የሌላቸውንና ኃጢአተኞችን ባዕድ አምላኪ የሆኑ ነገስታትን ትቷል:: ምክንያቱም በማዳን ታሪክ ውስጥ አላስፈላጊ ናቸውና:: ይሄ ችግር የሚያመጣ አይደለም፤ ምክንያቱም ማቴዎስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ተስፋ የመፈፀሙን ነገር ሊናገር ስለፈለገ እንደሉቃስ ሁሉንም የትውልድ ሐረግ መዘርዘር አላስፈለገውም:: ስለዚህ ነው የማቴዎስ ወንጌል በበለጠ ስለ እግዚአብሔር ልጅ መንፈሳዊና ምሳሌያዊ ፍች የያዘው:: የሉቃስን የትውልድ ሐረግ ግን የምንረዳው የክርስቶስን የደም ሐረግ እስከ አዳም በመሄድ ለማረጋገጥ እንደሆነ ነው::

ስናጠቃልለው በማቴዎስ ያለው የትውልድ ሐረግ ለስምን የዩሴፍን ቤት እዳመሰከተ የሚያሳየውን ጥያቄ ለመግለፅ እንገደዳለን::

## የዮሴፍ የትውልድ ሐረግ ማቴ 1:1-17

በሉቃስ 3:23-38 ያለውን የቤተሰብ መስመር የማርያምን የትውልድ ሐረግ በመጀመሪያ እይታ ለመገንዘብ ችግር ቢኖርም በተቃራኒው በማቴ 1:1-17 ባለው ስለ ዮሴፍ ይህ ችግር አይኖረንም:: ምክንያቱም የእርሱ ንጉሳዊ በሆነ የደም ሐረግ ሕብረት ስለመኖሩ በግልፅ የታተተ ነው::

«ያዕቆብ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደችውን የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ» (ማቴ. 1:16) ስለሆነም ዮሴፍ የያዕቆብ የሥጋ ልጁ ነበር እንጂ የኤሊ ልጅ አልነበረም (ሉቃስ 3:23):: ያለ ምንም ጥያቄ ዮሴፍ ከዳዊትና ከስለሞን የትውልድ ሐረግ የሆነ ነው:: ስለሆነም በማንኛውም ጊዜ ወደ አያቶች መለስ በማለት እነዚህን ንጉሳዊ ቤተ ሰቦች መጥቀስ ይችላል:: በማቴዎስ ባለው ንጉሳዊ የትውልድ መስመር መስረት ማንኛውም ሰው የዳዊትን የስለሞንና የዮሴፍን የቤተሰብ መስመር በመጥቀስ ጌታ ኢየሱስ በዳዊት ዙፋን ላይ የንጉስነት መብት እንዳለው ማረጋገጥ ይችላል:: ይህ መብት ተቀባይነት ያገኘ ነበር:: ምክንያቱም ዮሴፍ ማርያምን ስላገባና የኢየሱስ አሳዳጊ አባት ስለሆነ ነው (ሉቃ 3:23፤ 4:22):: የማርያም የትውልድ ሐረግ በዳዊት በኩል ወደ ናታን ቤት ስለሚሄድ ይህ ማረጋገጫ በእርሷ በኩል የሚጎድለው ነገር አለው (ሉቃ. 3:31):: ምንም እንኳን እነዚህ ከዳዊት የመጡ ዝርያዎች ቢሆኑም በእስራኤል ላይ በንግስና አልገዙም ነበር:: ስለሆነም ከዳዊት ከሰሎሞንና ከዮሴፍ ንጉሳዊ መስመር ውስጥ የሆኑ አይደሉም::

ነገር ግን ይህን ሃሳብ እንደገና ማጠናከር ይኖርብናል:: ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ የዮሴፍን ልጅ ቢባልም እንኳን ከዮሴፍ ጋር ምንም ዓይነት ተፈጥሮአዊ ግንኙነት አልነበረውም:: ክርስቶስ ከንፅህት ድንግል የተወለደና እግዚአብሔር ብቻ አባቱ የሆነ ማንነት ነው (ሉቃስ 31:35፤ ኢሳ 7:14):: ስለሆነም ከዮሴፍ ጋር በስጋ ዝርያ የሚገናኙበት ምንም ነገር የለም:: ዮሴፍ አሳዳጊው (ሞግዚቱ) ብቻ ነበር:: ይህ በማቴዎስ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ በበለጠ መንፈሳዊና ምሳሌያዊ ጠባይ እንዳለው ይበልጥ ያጠናክረዋል:: ምክንያቱም ኢየሱስ ከዮሴፍ በሥጋ የተወለደ አይደለምና:: በሥጋ የንጉሳዊ ቤተሰብ ስለመሆኑ ስህተት ከሌለው መሰረታዊ ከሆነው ከመፅሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም (ማቴ 1:16)::





መግለጫ ክፍል 2:

# ከመፅሐፍ ቅዱስ የጊዜ ቆጠራ ጋር ያለው ችግር

የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚከናወን ከሆነ የዓለም ታሪክ ቀናትን እንድንጠቀም እንገደዳለን:: ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሚለው በእኛ የጊዜ ቆጠራ ላይ እናርፋለን:: ነገር ግን ይህ ካሌንደር (የጊዜ አቆጣጠር) ትክክል ስላልሆነ ችግር ይኖረናል::

## የእግዚአብሔር ልጅ ሰው የሆነው መቼ ነው?

በንጉሱ በአውግስጦስ ዘመነ መንግስት የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ ወደዚህ ወደ ተረገመው ዓለም በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ይህን ልዩ የሆነውን ታሪካዊ ቀን ለመመዝገብ ካሌንደር (የቀን መቁጠሪያ) በእጁ የያዘ ታሪክ ፀሐፊ አልነበረም:: ከዓለሙ አዳኝ ልደት ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ ነው አንድ ሰው ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣትን ዘመን ፍለጋ የጀመረው:: ይህም ተደርጎ የነበረው ሮም በነበረው ጳጳስ በዳግማዊ ዮሐንስ ከ533-535 እ.አ.አ. ነበር:: እጅግ የከበረው የአዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ እንደተወለደ መርምሮና ጥናት እንዲያደርግ ዳዮኒስስ ኤክሲገስ ለተባለው ምሁር መነኩሴ ሥራውን ሰጠው:: ዲዮኒሰስ ኤክሲገስ ዝርያው ከስኬዝ የሆነና በሮም ከ500-550 ዓ.ም. ድረስ የኖረ ነበር:: በሮማውያን ነገስታት ጊዜ ላይ በማረፉ ምክንያት በምርምሩ ጥቂት ስህተት ገባበት:: ብዙ ነገስታት ለዓመታት በአንድነት ገዝተው ስለነበር በዚህ ምክንያት የምርምሩ ውጤት ትክክል አልነበረም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በዜሮ ዓመት ላይ ሳይሆን ስድስት ወይ ሰባት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር ::

ይህም ቢሆን ሁል ጊዜ በጥናታችን የምንጠቀመው ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን (Traditional) አሁን በእጃችን ባለው ካሌንደር ነው:: ፍላቪየስ ጆሴፉስ የተባለው አይሁዳዊ የሆነው ታሪክ ፀሐፊ «ጥንታዊ» የአይሁዶች ታሪክ «የአይሁድ ጦርነቶች» በተባሉት መፅሐፍቱ ሕፃናትን በቤተ ልሔም ያስገደለው ታላቁ ሄሮድስ የሞተው ሚያዝያ 2 ቀን የሮም ከተማ ከተመሰረተች ከ750 ዓመታት በኋላ ነው በማለት ፅፏል:: የሮም ከተማ የተመሰረተችው ከጌታ ኢየሱስ ልደት ከ753 - 754 ኤ.ክ.ል.በ ከሆነ ሄሮድስ የሞተው ከጌታ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ ነው ማለት ነው:: ስለሆነም የእግዚአብሔር ልጅ የተወለደው በ6 ከ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው:: ምክንያቱም በማቴ 1:16 ላይ የተገደሉት ሕፃናት ሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በታች እንደነበሩ ተፅፏል:: ጥቂቶች ደግሞ በከዋክብት በሚደረገው ቆጠራ በመጠቀም የጌታ ልደት የሆነው በ7 አ.ክ.ል.በ (ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) ነው

ብሰዋል:: እነዚህ ዘገባዎች እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ከሆነ ራሳችንን ከእነርሱ እናርቅና ስፍራ ሳንሰጣቸው እዚሁ እንተዋቸውና እንለፍ::

## የእግዚአብሔር ልጅ የተሰቀለው መቼ ነው?

ይህን ጊዜ ለመቁጠር በጣም አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ በፊት በገጽ 141 ላይ (ፀነህ. 1፣2 እና 2:1) በመመስረት ስለ ሰባው ሱባኤ (ሳምንታት) ለመግለፅ ሞክረናል:: በእነዚህ ክፍሎች የፋርስ ንጉስ ቀዳማዊ አርጤክስስ በነገሰ በ20ኛው ዓመት ለጠጅ አሳላፊው ለነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዲሰራ እንደፈቀደለት ተፅፎአል:: በጥሩ ሁኔታ በተመዘገበ ታሪክ ይህ ንጉስ የፋርስ ንጉስ ሆኖ የነገሰው ከ465-464 ከ.ክ.ል.በ እ.አ.አ. ባለው ጊዜ ነበር:: ስለሆነም 445 ከ.ክ.ል.በ የንግስናው ሃያኛው ዓመቱ ነበር ማለት ነው:: ከ483 ላይ 445 ከ.ክ.ል.በ ብንቀንስ ጌታ የተሰቀለው በ38 ዓ.ም ማለት ነው:: (ዳን. 9:24-27) ውስጥ 62ኛውንና እና 7ኛውን ስለሚለው ሱባኤ (ሳምንታት) በገፅ 127 ይመልከቱ):: ነገር ግን ይህ የማይሆን ነገር ነው፣ ምክንያቱም ጴንጤናዊው ጲላጦስ በይሁዳ ላይ ገዢ የነበረው ከ26-36 ዓ.ም ስለነበርና ቀያፋም ሊቀ ካህናት የነበረው ከ18-37 ዓ.ም ስለነበር ነው:: እነዚህን ቀናት ሁሉ ስንቆጥር ከ533 ዓ.ም ጀምሮ በክርስትናው ዓለም የምጠቀምበትን ትክክል ባልሆነው የዳዮኒሲስ ኤክሲገስ ካሌንደርን ነው:: ሌላ የፋርስን ታሪክ በተመለከተ የጊዜ ቆጠራ የፋርስ ንጉስ የቀዳማዊ አርጤክስስን 20ኛውን ዓመት በ458 እና በ445 መካከል በ13 ዓመታት ልዩነት ያደርገዋል:: ስለሆነም አንድ ሰው በዚህ በሜዶናውያን ዓመት ቢቆጥር የፋርስን ንጉስ 20ኛውን ዓመት 451 አ.ክ.ል.በ ላይ ያደርገዋል:: ከ483 ላይ 451 ሲቀነስ ውጤቱ ጌታ የተሰቀለው 32 ዓ.ም ላይ ነው ወደሚለው ያደርሰናል:: አንድ ፕሮፌሰር ይህን በማፅደቅ በፋርሳውያን መነሻዎችና በግሪኩ ታሪክ ፀሐፊ በሆነው በሄሮዲት (ከ490-424 አ.ክ.ል.በ በነበረው) ላይ በመመስረት የፋርስን ታሪክ ፅፏል::

የአይሁድ ቀን አቆጣጠር በጨረቃ ልደት ላይ የተመሰረተና የዓመት ቀናቸው 360 ቀናት መሆኑን በአእምሮአችን መያዙ ለመረዳታችን የሚረዳን ይሆናል:: ስለዚህ ነው በራዕይ 11:2-3፤ 12:6፤ 14፣ 13:5 የተጠቀሱት $3^{1/2}$ ዓመታት በ42 ወርና በ1260 ቀናት የተገለፁት:: መፅሐፍ ቅዱስ የዓመቱ ቀናትን 360 ቀናት አድርጎ ስለሚቆጥር የአይሁድ ካሌንደር ከእኛ ካሌንደር የአምስት ቀናት ልዩነት አለው:: አይሁዶች ካሌንደራቸውን ከእኛ ካሌንደር ጋር ለማስተካከል አዳር ከተባለ አስራ ሶስተኛ ወር በአዳርና በኒባን ወራት (በጥርና በየካቲት መሃል ማለት ነው) መካከል መጨመር አስፈለጋቸው:: 483 ዓመታትን 360 ቀናት ባለው





የአይሁድ ቀን አቆጣጠር ብንቆጥር 2415 ቀናት ይኖሩናል (ይህም 7 ዓመት ማለት ነው):: በዚህ መንገድ የስድስቱን ወይም የሰባቱን ዓመት ጥያቄ ለንፈታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት በ32 ወይም 33 ዓ.ም ገደማ እናደርገዋለን::

## እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት መቼ ነው?

ይህ ሁኔታ በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከእግዚአብሔር በሲና ተራራ መገለጥ፣ ከአስርቱ ትዕዛዛትና ከመገናኛ ድንኳኗ መሰራት ጋር የተያያዘ (የተዛመደ) ነው:: በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ በእምነት በማረፍ በአስራ ሁለተኛው ወይም በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስራኤል ልጆች ወደ ከንዓን ገብተዋል ተብሎ በዘመኑ የሃይማኖት ሰዎች የተሰጠውን የተሳሳተ አቆጣጠር እንቃወማለን:: መፅሐፍ ቅዱስ ለራሱ እንዲናገር እንፍቀድና ትኩረታችንን ወደ ሚከተሉት ቀናት እናድርግ::

1. እንደ መሳፍንት 11:26 የእስራኤል ልጆች በእስራኤል ምድር በምስራቅ ዮርዳኖስ በምናሴና በገለአድ ለ300 ዓመታት መኖራቸውን እናያለን::
2. እንደ ሐዋርያት ሥራ 13:20 እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ድረስ ለ450 ዓመታት እግዚአብሔር መሳፍንት እንደ ሰጣቸው እንመለከታለን:: የእስራኤል ልጆች እስከ 12ኛውና 13ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከግብፅ ሳይወጡና ወደ ከነዓን ካልገቡ እዚህን 450 ዓመታት እንዴት እናስታርቃቸዋለን?
3. በ1ነገ. 6:1 መሠረት ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መስራት የጀመረው የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ከወጡ ከ480 ዓመታት በኋላ ነው:: የእስራኤል ልጆች እስከ 12ኛውና እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከግብፅ ሳይወጡና ወደ ከነዓን ሳይገቡ ከቆዩ እነዚህን 480 ዓመታት እንዴት እናስተናግዳቸዋለን::

## ምን የታመኑ የዓመታት ቁጥሮች ይኖሩናል?

በምንጥላቸው ቀናት ምትክ የታመኑትን ቀናት እንጠቀማለን:: እስራኤል በ1996 እ.ኢ.አ የኢየሩሳሌምን 3000ኛው የልደት ቀን አከበረች:: ከ3000 ላይ 1996 ብንቀንስ ወደ 1004 ከ.ኢ.ል.በ ያመጣናል:: ይህም ጊዜ ንጉስ ዳዊት የኢያቡሳውያንን ከተማ ድል ያደረገበትና ኢየሩሳሌምን የ12ቱ ነገዶች ዋና ከተማ ያደረገበት ጊዜ ነበር (2ሳሙ. 5:1-10፤ 1ዜና 11:1-8):: እንደ አይሁድ ቀን አቆጣጠር እነዚህ ቀናት በትክክል የታመኑ ናቸው:: ንጉስ ዳዊት በ1012 ከ.ክ.ል.በ ንጉስ ከመሆኑ አስቀድሞ ለ$7^{1/2}$ ዓመት በአይሁድ ነገድ ላይ በኬብሮን ነግሷል:: በዚያው ዓመት ንጉስ ሳኦል

ሞተ። በ ሐሥ. 13:21 መሰረት ሳኦል በእስራኤል ላይ ለ40 ዓመት ነግሷል። ስለሆነም በእስራኤል ላይ የነገሰው በ1052 ከ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው። ከእርሱ በፊት የመጨረሻው መስፍን የሆነው ሳሙኤል ነቢይ ሆኖ አገልግሏል። ሳኦል በነገሰበት 450 የዘመነ መሳፍንትን ጊዜ ላይ ብንደምርበት ወደ 1502 ከ.ክ.ል.በ ያደርሰናል። ከመሳፍንት በፊት እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት የተስፋይቱም ምድር ድል በማድረግ ያዧት። ይህን ለመፈፀም ብዙ አስቸጋሪ ዓመታት ፈጅቶባቸዋል። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ቆይተዋል። እስራኤላውያን ከግብፅ ከመውጣታቸውና በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ከመንከራተታቸው በፊት በግብፅ ለ430 ዓመታት ኖረዋል (ዘፀ. 12:40)። እነዚህ ቁጥሮች ልክ ናቸው፣ አቆጣጠሩም ትክክል ነው።

## ከቤተ መቅደሱ መሰራት ከ480 ዓመት በፊት ከግብፅ መውጣት ሆነ

እስከ አሁን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት አስተማማኝ (ትክክል) በሆኑት ቁጥሮች እየሰራን ነበር። ጥናታችን ስንቀል ግን የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ስለ ወጡበት ጊዜ ሌላ ችግር ይገጥመናል። ንጉስ ዳዊት በ1012 አ.ክ.ል.በ ከነገሰና ለ40 ዓመታት ከገዛ፣(2ሳሙ 5:4-5) ንጉስ ሰሎሞንም የነገሰው በ972 አ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው። እርሱ ደግሞ በእስራኤል ላይ ለ40 ዓመታ ገዝቷል። (1ነገ 11:42) ሰሎሞን በነገሰ በአራተኛው ዓመት ቤተ መቅደሱን መስራት ጀመረ (1ነገ. 6:1፣ 37) ይህም ዘመን 968 አ.ክ.ል.በ ነበር።

እንደ 1ነገ. 6:1 የቤተ መቅደሱ ግንባታ የተጀመረው ከግብፅ ከወጡ ከ480 ዓመታት በኋላ ነበር። ከሰሎሞን ንግስና ከአራት ዓመት በኋላ ይህን 480 ዓመት ብንቀንስ (ከ972-4 = 986) የእስራኤል ልጆች ከግብፅ የወጡት በ1448 አ.ክ.ል.በ ነበር ወደሚለው ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል። ይህን ቆጠራ ብንከተል እስራኤላውያ ከግብፅ የወጡበትን ጊዜ ወደ 50 ዓመት ልዩነት ያመጣዋል። የተባረከው የስነ መለኮት በጀርመን ካለችው ከውፐርታ ፐሮፌሰር የሆነው ዶክተር አብርሃም ሚይስተር (1901-1990) አዳም የተፈጠረው በ4160 አ.ክ.ል.በ ነው በማለት ቆጠራውን ጀመረና አብርሃም የተወለደው በ2212 አ.ክ.ል.በ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት በ1492 አ.ክ.ል.በ ነው ብሎአል። ስለሆነም እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት በ1500 ኢ.ክ.ል.በ አካባቢ ነው ወደሚለው ማጠቃለያ ልንደርስ እንችላለን። ሌሎቹን በመፅሐፍ ቅዱስ ሊረጋገጡ የማይችሉትን በኢንሳይክሎፒድያ ውስጥ ያሉትን አስተያየቶች ልናስወግዳቸው ይገባናል።





ለምሳሌ ከ1492 አ.ክ.ል.በ ወደ ኋላ ብንሔድ እስራኤላውያን በግብፅ ለ430 ዓመታት መቆየታቸውን እናውቃለን (ዘፀ. 12:40) ይህ ከገላትያ 3:16-17 ካለው ጋር ይስማማል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ሕግ የሰጠው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ኪዳን ከገባላቸው ከ430 ዓመታት በኋላ ነበር። እነዚህ በግብር የቆይታ 430 ዓመታት ወደ ኋላ ወደ 1992 አ.ክ.ል.በ ይወስዱናል። ይህ ጊዜ የእምነት አባት የሆነው ያዕቆብ በ130 ዓመቱ ከመላ ቤተሰቡ ጋር ወደ ግብፅ የወረደበት ጊዜ ነበር። ከእነዚህ 130 ዓመታት ብንነሳ የያዕቆብና የኤሳው ልደት በ2052 አ.ክ.ል.በ እንደነበር እንችላለን። እነርሱ ሲወለዱ አባታቸው ይስሐቅ 60 ዓመቱ ነበር። ይህ ማለት ይስሐቅ የተወለደው በ2112 አ.ክ.ል.በ ነበር ማለት ነው። ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም 100 ዓመቱ ነበር። ስለሆነም አብርሃም የተወለደው በ2212 ኢ.ክ.ል.በ ነበር ማለት ነው። በቻርቱ ላይ የአብርሃምን የልደት ጊዜ ወደ 2150 ኢ.ክ.ል.በ በማድረግ አክብበነዋል።

እነዚህ ገለፃዎች ሁል ጊዜ ትክክለኛውን ጊዜ መስጠት አዳጋች እንደሆነ ግልፅ ያደርጉልናል። ነገር ግን ከተጋነኑ ወዲያና ወዲህ ከሚያወዛውዙን ቁጥሮች ጋር መሆን አንፈልግም፣ ሆኖም በመፅሐፍ ቅዱስ በተሰጡት በጣም ልንረካ ያስፈልገናል። በመፅሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ሁኔታዎች በአመዛኙ ትክክለኛውን የተቃረበ ጊዜን ለመስጠት ያስችሉናል። መፅሐፍ ቅዱስ የደህንነት ታሪክ የእግዚአብሔርን የደህነትን እቅድ በመግለፅ የሚያሳስበን ነው። መፅሐፍ ቅዱስ በተቀዳሚ የሚገልፅልን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራውን እንጂ ቁጥርን አይደለም።

መግለጫ ክፍል 3:

# በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ የቤተ መቅደሶች መስፋፋት


በዚህ ክፍል በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የቤተ መቅደሱን የተሰያዩ ንድፎችና እነርሱም እንዴት እንደተቀያየሩ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈውን እናጠናለን::

የቤተ መቅደሱ መኖር ዋና ዓላማ የቅዱስ እግዚአብሔርና የኃጢአተኛው ሰው መገናኛ ቦታ ነው::በዚህ ቦታ ካህናት መስዋዕት ያቀርባሉ፣ ሊቀ ካህናቱ ደግሞ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቃሉ:: ከሰው ውድቀት በፊት ቤተ መቅደስ አልነበረም፣ ምክንያቱም ሰው ያለ ኃጢአት ስለነበር መስዋዕት የሚያስፈልገው አልነበረምና:: እንደዚሁም በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ቤተ መቅደስ አይኖርም፣ምክንያቱም ኃጢአት ለአንዴና ለዘላለም የተደመሰሰ ስለሚሆን ነው::

በቻርቱ ላይ የተሰያዩት ቤተ መቅደሶች በማዳን ታሪክ ውስጥ ጠቅላላውን ስፋት የያዙበትን የራሳቸውን መስመር መስርተዋል:: በአስር ሰዎችም ተከፋፍለዋል እሁን የእያንዳንዱን ይዘትና ፍቺ በግልፅ እንመረምራለን::

## 1. ቤተ መቅደስ ያልነበረበት ጊዜ

### ዘፍ 1 እና 2



ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በሚያስደንቅ ደስታ የሚደሰትና ከእግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ህብረት ነበረው:: ሰው ያለ ኃጢአት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ይኖር የነበረውም ያለ ኃጢአት በሆነ ዓለም ውስጥ ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር እና ከተፈጥሮ ጋር በነበረው ሕብረት ምንም የኃጢአት ዱካ (ምልክት) አልነበረም ምክንያቱም ኃጢአት አልነበረምና:: በኤደን ገነት የእግዚአብሔር መገኘት ከሰው ጋር ነበር (ዘፍ. 3:8):: ሰው በማንኛውም ጊዜ ከአምላክ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነበረው:: ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የቅርብ ግንኙነትና ደስታ በሰው ቃላት ሊገለፅ የማይቻል የሚቀጥልና ክብር የተሞላበት እውነታ ነበር ነገር ግን ሰሁለቱ ሰዎች ለአዳምና ሔዋን ብቻ የተወሰነ ነበር:: ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው






ሕብረት ያልታወከና ያልተቋረጠ ስለነበር ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቤተ መቅደስ ወይም መስዋዕት አያስፈልጋቸውም ነበር::

## 2. መስዋዕት


### ዘፍ 4:4፣ 8:20



ከሰው ውድቀት በኋላ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ሕብረት በማጣቱ ምክንያት መስዋዕትና መቅደስ አስፈለገው:: በቀደመው ታሪክ ማንኛውም ሰው ያለ ሁሉ ያለ ልዩነት መስዋዕት ሲያቀርብ ተስተውሰዋል:: ለምሳሌ ስለ ሰዎች ሲታሰብ ቃየንና አቤል፣ ኖህ፣ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብና ኢዮብን እንጠቅሳለን:: (ዘፍ.4:3-4፤ 8:20፤ 15:6፤ 26:25፤ 31:54፤ ኢዮብ 1:5):: ከቃየን በስተቀር ሁልጊዜ ሰዎች የእንስሳ ደም ይሰዉ ነበር:: ምክንያቱም ስለ ኃጢአተኛው በምትክነት በሚሞተው በደል በሌለበት እንስሳ ያምኑ ስለነበር ነው:: እግዚአብሔር የመስዋዕት ሥርዓት ሰጠ፣ ምክንያቱም ኃጢአተኛው ሰው እንደገና ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ እንዲችል፣ ይቅርታንና ስርየትን እንዲያገኝ ስላስፈለገ ነው:: እስከ ሙሴ እንኳን እያንዳንዱ የቤተሰብ ኃላፊ (አባት)፣ እያንዳንዱ የነገድ መሪ ስለ ራሱና ስለ ቤተሰቡ መስዋዕት ይሰዋ ነበር::

## 3. ተየአምልኮ ድንኳን

### ከ.ክ.ል.በ 1492 /1448 እስከ 968/961



እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከግብፅ ካወጣቸው በኋላ በሲና ተራራ ላይ አዲስ የመስዋዕትና የቤተመቅደስ አምልኮ ስርዓትን ሰጣቸው:: በዚህ ጊዜ ማንኛውም ሰው በያሰበት ያቀርብ የነበረው ግላዊ የመስዋዕት ጊዜ አከተመ::


በዚህ ምትክ ሙሴ የቤተ መቅደሱን፣ ከመስዋዕቶቹ፣ ከካህናትና ከአምልኮ ጋር ያለውን የተከበረውን ራዕይ (መገለጥ) ተቀበለ:: ቤተመቅደሷ የመገናኛ ድንኳን የእግዚአብሔር ማደሪያ በሚል ይታወቅ ነበር:: ግልጽ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር (ሽኪና) በዚህች ድንቅ ድንኳን ውስጥ ባለው በቅድስተ ቅዱሳን ያድር ነበር:: በየቀኑ ካህናት ተፈላጊውን መስዋዕት ያቀርባሉ:: ሊቀ ካህናቱበታላቁ የስርየት ቀን (ዮም ኪፑር) መላ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተራርቅ ነበር:: በዚህች ምድር ላይ በድንኳኗ በሚደረገው

መስዋዕቶችና በካህናቱ አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረቢያ መንገድ የነበራቸው እስራኤላውያን ብቻ ነበሩ:: ሌሎቹ አሕዛብም በጣዖት ቤታቸው ጣዖትን ያመልኩ ስለ ነበር በሰይጣንና በስራዊቱ ፊት የሚቀርቡበት መንገድ ነበራቸው (1ቆሮ. 10:20) :: ነገር ግን የድንኳኗ እውነተኛ አመልካችነት በጣም ጥልቅ የሆነ አመልካችነት ነበረው:: የድንኳኗ፣ የክህነቱና የካህናቱ አገልግሎት፣ የመስዋዕቶቹና የቤተ መቅደሱ ንዋየ ቅድሳቱ በሙሉ የጌታ የአዳኙ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ተምሳሌት ነበሩ:: በዕብራውያን መልዕክት «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና» ተብሎ ተገልጧል (ዕብ. 10:1)::

እንዲሁም *«እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው»* ተብሎ ተፅፏል (ቆላ. 2:16-18)::

## 4. የሰሎሞን ቤተመቅደስ

### ከ.ክ.ል.በ 968/961 - 586




ለ480 ዓመታት ገደማ ድንኳኒቱ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ መገናኛ ሆና አገልግላለች:: ንጉስ ሰሎሞን በነገሰ በአራተኛው ዓመት ትክሉን ቤተመቅደስ መስራት ጀመረ:: የቤተ መቅደሰሱም ክብር በኢየሩሳሌም ከተሰሩት ሁሉ በጣም የላቀ ነበር:: (1 ነገ 6:1) ይህን ታላቅ ሕንፃ ስመስራት መጠኑ ብዙ የሆነ ወርቅና ብር ተጠቅመው ነበር:: የቤተ መቅደሱ ሥራ በሰባተኛው ዓመት እንዳበቃ በተመረቀበት ቀን ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር (ሽኪና) ካህናቱ ገብተው ማገልገል እስከማይችሉበት ድረስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ገብቶ ነበር:: (1ነገ 8:10-11፤ 2ዜና 5:14):: በዚሁ ጊዜ ተንቀሳቃሽ የነበረችው የድንኳን መቅደስ የአገልግሎቷን ዘመን ፈፀመች::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ማንኛውም መስዋዕት ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ባሰራው ቤተመቅደስ የሚደረግ ሆነ:: ከዓመታት በፊት እግዚአብሔር ቤተመቅደሱ በሞርያ ተራራ ላይ የሚሰራበትን ትክክለኛውን ቦታ ለሙሴ ገልጾለት ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡ ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበት በአስራ ሁለቱ ነገዶች መካከል ሊሰራ ስላለው መቅደስ ቀደም ብሎ እቅዱን በዘፀ. 20:24 እና በዘዳ. 12:4-6 ላይ ሰጥቶ ነበር:: እርሱ ኢየሩሳሌምን መረጠ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ከሺ ዓመት በኋላ ከሞርያ ተራራ በስተ ሰሜን ባለው በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ዘላለማዊ ደህንነትንና ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅን ሥራ የሚፈጽም ነበርና:: (2ዜና.






5:19-21) ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱና በፈፀመው የማዳን ሥራ (ክርስቶስ) እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን የመቅደሱን፣ የመስዋዕቶቹንና የክህነትን ጥላና ተምሳሌት ለአንዴና ለዘላለም ፈፀመው::

## 5. የዘሩባቤል ቤተ መቅደስ

### ከ.ክ.ል.በ 516 እስከ 70




ባቢሎናውያን በ586 ከ.ክ.ል.በ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ ደመሰሱት (አፈራረሱት) ከ70 ዓመት በኋላ በ516 ከ.ክ.ል.በ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በእስራኤል ተሰራ:: ይህ የቤተመቅደሱም የተሰየመው በአይሁዱ መስፍን በዘሩባቤል ስም ነበር::

ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በኋላ ታላቁ ሄሮድስ የዘሩባቤልን ቤተ መቅደስ አስፋው ለአርባ ስድስት ዓመት አርባ ሜትር ከፍታ ያለውን የመቅደሱን አጥርና ትልቅ የሆነውን የቤተ መቅደሱን ቅርፅ ሰሩ (ዮሐ. 2:20):: በስተ ደቡባዊ ምስራቅ ዳርቻ በኩል የሚከበበው «የቤተ መቅደሱ ጫፍ» ተብሎ የሚጠራው ግንብ ስባ አምስት ሜትር ከፍታ ያለውና ወደ ቄድሮን ሸለቆ የሚዘልቅ ነበር:: ጠቅላላ አቋሙ ሐውልት ይቋስል ነበር:: በደቡባዊ ዳርቻ በኩል ርዝመቱ 488 ሜትር እና 283 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን በስተ ሰሜን በኩል ደግሞ 321 ሜትር ስፋት ነበረው:: አሁንም እንኳን ቢሆን በምዕራብ በኩል ባለው ቅጥር በቁፋሮ ቅርሶች የተገኙት ስለዚህ ታላቅ ግንብ ምስክርነታቸው ይሰጣሉ (ማቴ. 24:1-2) :: ዛሬ በምዕራብ በኩል ያለው ቅጥር «የልቅሶ አደባባይ» በመባል ይታወቃል:: ነገር ግን ሰሎሞን ስርቶት እንደነበረው ዓይነት ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ክብር በዚህ ቤተ መቅደስ አልተገኘም:: ነገር ግን (በዮሐ. 1:14) ያለው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት እስከሚፈፀም ድረስ ጌታ እግዚአብሔር በክብሩ ወደዚህ መቅደስ አልገባም:: ዮሐ. 1:40 የሚለው ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን::» ነው:: ወደ ቤተመቅደሱ በገባ ጊዜ ገንዘብ ለዋጮችን አስወጣ፣ ቤተ መቅደሱንም ከእርግብ ሻጮች አፀዳ:: (ዮሐ. 2:14-16) እዚያ ብዙ ታምራቶችን አደረገ፣ ሕዝቡንም አስተማረ (ማቴ. 21:14፤ ሉቃ 19:47) :: ቀራንዮ መስቀል ላይ በመስዋዕትነቱ የብሉይ ኪዳንን መስዋዕቶችን ፈፀማቸውና፣ በአጠቃላይ የሃይማኖት ሥርዓቶችን ከቤተ መቅደስ አስቀራቸው:: ስተወሰነ ጊዜ የተሰጠው የብሉይ ኪዳን

የክህነት አገልግሎት በእርሱ ወደ ፍፃሜ መጣ፣ ምክንያቱም ክርስቶስ እውነተኛው ሊቀ ካህናትና ዘላለማዊ ክህነት በሰማይ ስላለው ነው። «እነርሱም ያ መሐላ ካህናት ሆነዋልና፣ እርሱ ግን ጌታ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይፀፀትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና፣ ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል። እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፣ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው» (ዕብ. 7:20-24)።

## 6. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደስ

### ዮሐ 2:21




በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ትክክለኛውና እውነተኛው መቅደስ ተብሎ ተጠርቷል። አዳኙ «ስለ ሥጋው መቅደስ» (ዮሐ 2:21) በተናገረ ጊዜ ስለ ብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ሀሳብ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን የተናገረው ስለ ድንኳኒቱ፣ ስለ ሰሎሞንና ስለ ዘሩባቤልም ቤተ መቅደስ ነበር ። ምክንያም እነርሱ የሥጋው ቤተ መቅደስ ጥላ ነበሩና። ከዓለም ፍጥረት በፊት እንኳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ራሱን መስዋዕት አድርጎ ስለ ኃጢአታችን ራሱን በመስቀል ላይ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር። ስለዚህ መስቀል ከኃጢአት ያድነናል። ስለሆነም የቀራንዮ መስቀል አዳኙ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ ከሺ ዓመታት በፊት ጥላውን በድንኳኒቱና በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደሶች ላይ ጥሎ ነበር። ሙሴ ድንኳኒቱን በሰራ ጊዜ ጌታ በሲና ተራራ ላይ በገለፀለት ዓይነትና ምሳሌ መሰረት መቅደሱን ሰርቷል (ዘፀ. 25:9፣ 40፣ 26:30፣ 27፣ 8፣ 39:43)። ይህ ምሳሌ የመለኮታዊው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ነበር። በውጭ በሚታዩት በድኳኒቱ፣ በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደሶችና ንዋየ ቅዱሳቱ የመስቀል እውነትነት በምሳሌነት ተገልጾ ነበር። ኃጢአት የሌለበትና የእግዚአብሔር በግ ሆኖ እንከን የሌለበት መስዋዕት የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ነበሩ።

የብሉይ ኪዳን ስርዓት ጥላነት በአዲስ ኪዳን ተፈፃሚነትን ሲያገኝ በቤተ መቅደሱ በሚቃጠለው መስዋዕት መሰዊያ ቦታ ምትክ የኢየሱስ ክርስቶስ እግሮች በመስቀል ላይ በሚስማር ተቸነከሩ። በውጭው አደባባይ ባለው የመታጠቢያ ሳህን








ምትክ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጎን ደምና ውሀ ፈሰሰ። (ዮሐ. 19:34) ወርቅማው መቅረዝ በቆመበት ቦታ የክርስቶስ ቀኝ እጁ በምስማር ተቸነከረ። በቤተ መቅደሱ አስራ ሁለት ሕብስቶች ለመታሰቢያ በሚቀመጡበት ጠረጴዛ ቦታ የኢየሱስ ግራ እጅ በመስቀል ላይ በምስማር ተቸነከረ። በቤተ መቅደሱ በቅድስት ውስጥ ለፀሎት እጣን በሚጨስበት መሰዊያ ቦታ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና» ብሎ ፀለየ (ሉቃ. 23:34) በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የኪዳኑ ታቦት ከስርየት መክደኛና የሕጎቹ ፅላት በቆሙበት ቦታ የእግዚአብሔር ልጅ ራሱን አዘንብሎ «ተፈፀመ» ብሎ ጮኸ። የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋው መቅደስ ፍቺ ይህ ነው። በዚህ መቅደስ ማለትም በሥጋው መስዋዕትነት ብቻ ነው ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር መገናኘት የምንችለው (ዕብ. 10:4-10)።

## 7. የቤተ ክርስቲያን መቅደስ

### ኤፌ. 2:20፣ 2ቆሮ 6:16




ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ በሰራው ፍፁም በሆነ የማዳን ሥራ መሰረትነት በበዓለ ሃምሳ የመጀመሪያዋ ቀን ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተመሰረተች (ዮሐ. 7:39) እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ዘገባ ከዚያ ቀን ጀምሮ ብዙ የዳኑና ዳግም የተወለዱ አማኞች የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ «አባል ሆኑ» (2.ቆሮ 6:16)።


የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ የመሆን ጉዳይ ታላቅ ሚስጢር ነው (ኤፌ. 5:32)። እነዚያ «ሕያዋን ድንጋዮችና» «የመንፈሳዊ ቤት» የሆኑት ብቻ ናቸው ፍቺውን መጨበጥ (ማወቅ) የሚችሉት (1ጴጥ. 2:5)። በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ በመሰራት ላይ ስላለው ሕንፃ እናነባለን (ኤፌ. 2:21)። ኢየሱስ

ክርስቶስ ግንበኛው ነው:: ደሙ ደግሞ የዚህ ህንፃ ዋናው መገንቢያው መሳሪያ ነው:: እያንዳንዱ ዳግሞ የተወለደ አማኝ የዚህች የማትደመሰሰውን ሰማያዊ ሕንፃ ከጌታ ጋር አብሮ የሚሰራ ነው:: የማትደመሰሰበትም ምክንያት የመስኮታዊነት ባሕርይ ስላላትና ስዘላለም ፀንታ ስለምትኖር ነው::

ይህ እውነት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ፣ ሕንፃ፣ (ቤተ ክርስቲን) ወይም ትልቅ ካቴድራል እንዳይደለች ያመለክተናል:: እንደዚሁም ይህች ሰማያዊ ሕንፃ ቤተክርስቲያን በአሁኑ ዘመን በዚህ ምድር ላይ ሚኖሩ በስም ክርስቲያኖች ነን ባዮች የሆኑትና ስለ እግዚአብሔርና በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለው ደህንነት ለማወቅ የማይፈልጉትን የያዘች አይደለችም:: የዚህች ሕንፃ አባል የሚሆኑት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (መቅደስ) «ለእግዚአብሔር መኖሪያነት በመንፈስ» የሚሰሩና በንስሐና በዳግም ልደት የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት ብቻ ናቸው::

## 8. ሦስተኛው ቤተ መቅደስ

**2ተሰ 2:4**



እስከ አሁን ድረስ አብዛኞቹ የእስራኤል ሕዝቦች መሲህቸውን አላወቁትም በዚህ ምክንያት ነው በቀራንዮ መስቀል ላይ የተፈፀመውን የማዳን ሥራ የማይቀበሉት :: በተጨማሪም በዕብ 7:1-10፣ 18 የእስራኤል ሕዝብ ላይ እንደ ተፃፈው የመስዋዕቶች፣ የክህነት ሥራና የቤተ መቅደስ አምልኮ ከብዙ ዓመታት በፊት በክርስቶስ የተፈፀመ መሆኑን ሊያውቁ አልቻሉም:: ሃይማኖታውያን አይሁዶች ቤተ መቅደሱ ተመልሶ እስካልተሰራ ድረስ የእስራኤል መንግስት ያልተሟላ ሆኖ ይቆያል ብለው ያምናሉ:: ትክክሉ ቤተ መቅደስ ሲሰራ በማዳን ታሪክ ውስጥ በኢየሩሳሌም ከተሰሩት መቅደሶች ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ይሆናል::


እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ቃል አንድ ቀን የክርስቶስ ተቃዋሚ ዙፋኑን ሲተክል፣ ራሱን እንደ አምላክ እንዲመለክ የሚያደርግበትና የጥፋትንም ርኵሰት የሚያቆምበት ቦታ ይህ ቤተ መቅደስ ነው (ዳን. 9:24-27፤ ማቴ. 24:15፤ 2ተሰ. 2:4፤ራዕ. 11:1-2):: ይህ ሕንፃ, ከክርስቶስ ተቃዋሚ ጋር አብሮ ይደመሰሳል፣ ምክንያቱም ላልዳኑት የእስራኤል ሕዝብ እፍራሽ ዓላማ (ወደ ደህንነት እንዳይመጡ ማለት ነው) ስላለው ነው:: ቢሆንም የሃይማኖት ሰዎች ይህን ሦስተኛውን ቤተ





መቅደስ በእስራኤል በሞርያ ተራራ ላይ ለመስራት በየጊዜያቱ ብዙ ዝግጅቶች እያደረጉ ናቸው:: የቤተ መቅደሱን የመገልገያ እቃዎችና የክህነትን ልብሶች እየሰሩ ነበር:: ነገር ግን ለእኛ የሦስተኛው ቤተ መቅደስ መስራት የመጨረሻው ዘመን መሆኑን ከሚያሳዩን ምልክቶች ዋነኛው የቤተመቅደሱ መስራት ነው:: ጌታ ኢየሱስ በቅርብ እንደሚመጣ በግልፅ ይነግረናል::

## 9. በሕዝቅኤል ከምዕ. 40-48 ያለው ቤተ መቅደስ





በሕዝቅኤል 40 እና 48 መስዋዕቶችና ክህናት ስላሉት በዚህ ምድር ከአሁን በፊት ከቶ ስላልታየው ቤተ መቅደስ ነቢዩ ይገልፅልናል:: ይህ ቤተ መቅደስ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ የሺ ዓመት መንግስት ድረስ አይሰራም:: ቅርጹ (መልኩ) ልዩ የሆነ፣ በዓይነትና በመጠን በአጠቃላይ ከድንኳኗ፣ ከሰሎሞንና ከዘሩባቤል ቤተ መቅደስ የተለየ ይሆናል:: ክህነታዊ አገልግሎትና መስዋዕቶቹ ከበሉይ ኪዳኖቹ ጋር የማይወዳደር ነው:: እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ገለፃ የእግዚአብሔር ክብር ዳግም ይገባበታል (ይታይበታል) (ሕዝ. 43-1-5)::

በምዕ. 8:4፤ 9:3፤ 10:3-4፤ 18-19፤ እና 11:23 ነቢዩ እንዴት የእግዚአብሔር ክብር በእስራኤል የርኵሰት ኃጢአት ምክንያት (ሽከና ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ማለት ነው) ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ለቅቆ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ወደ ምስራቅ እንደሚሄድ ይገልፅልናል:: ነገር ግን በሕዝ 43:4-5 ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ከምስራቅ የደብረ ዘይትን ተራራ በማለፍ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ እንደገና ለመሙላት ስለ መመለሱ ይነግረናል:: እንደገና ሁሉን ቻይ አምላክ ከሕዝቡ ጋር ይሆናል:: ከሕዝ 40 እስከ 48 በተጠቀሰው ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር ስለሚገልፅ «እግዚአብሔር ከዚያ ነው» ተብሎ የተፃፈለት ቦታ ይህ ቦታ ነው ሕዝ 48:35::

በዚህ ቤተመቅደስ የሚሰውት ጥቂት መስዋዕቶች ምሳሌያዊ ፍቺ ይኖራቸዋል:: እንደ ጌታ እራት በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈፀመውን መስዋዕት እንደ መታሰቢያ ሆነው ያመለክታሉ::

## 10. ቤተመቅደስ የሌለበት ራዕይ 21 እና 22




ሰው በኤደን ገነት በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ቤተ መቅደስና መስዋዕት አልነበረም:: ይህም የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ያለ ኃጢአት ስለነበሩ መሆኑን ቀደም ብለን ጠቅሰናል:: የመፅሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ንጹህ፣ ስለሆነውና ስላልተበከለው እንዲሁም፣ ኃጢአትና ሞትን ስለማያውቀው ዓለም ይገልፃሉ:: ስለዚህ ነው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፈጥሮ በጨረሰ ጊዜ «እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበር» ተብሎ የተፃፈው (ዘፍ. 1:29-31)::

የመፅሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ደግሞ ሰዎች ኃጢአት በሌለባቸው አዲስ ሰማይና ምድር እንደሚኖሩ እንደገና እናነባለን:: ራዕይ 21 እና 22 በዚህ በአዲሱ ዓለም ኃጢአት ስለማይኖር ቤተ መቅደስ ካህናትና መስዋዕት አያስፈልጉም (ራዕ. 22:3)::

ስለሆነም የሰው ልጅ ታሪክ ኃጢአት በሌለበት ዓለም ጀምሮ ኃጢአት በሌለበት ዓለም ይጨርሳል:: እግዚአብሔር በእነዚህ ሁለት ጊዜያት መካከል የማዳን ዕቅዱን በመስቀል ላይ በተከናወነው የማዳን ሥራ ይሠራል:: በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በሙሉ የእግዚአብሔር ልጅ ለአንዴና ለዘላለም በኃጢአት፣ በሞትና በሰይጣን ወደሚከናወነው ዘላላማዊ ድል ያመለክታሉ:: አዲሱ ሰማይና ምድር በዚህ ላይ ብቻ ስለተመሰረቱ በአጠቃላይ ኃጢአት በዚህ ዓለም አይገኝም:: በዚህ ምክንያት መስዋዕት፣ የክህነት አገልግሎትና ቤተ መቅደስ አያስፈልጉም:: በሌላ አባባል በአዲሱ ዓለም መስዋዕትና የቤተመቅደስ አምልኮ አያስፈልጉም ምክንያቱም በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመው ደህነት ፍፁምና ዘላለማዊ ስለሆነ ነው:: ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ ንስሐ ከመግባትና ድንቁ አዳኝ በእርሱ የተፈፀመውን የደህንነት ሥራ በእምነት ከመቀበል በስተቀር የሚያደርገው ሌላ አይኖረውም:: ማንኛውም ደግሞ የተወለደና የዳነ አማኝ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር የሚገባው ለዘላለም በክርስቶስ ደም ፍፁም ንፁህ ከተደረገ ነው:: (ቆላ 2:10፤ ዕብ 10:14፤ 11:40):: ይህ ሰው ከክርስቶስ ሰማያዊ የሆነውን ክቡር ሥጋ በመስወጥ የተቀበሰና እንደ እግዚአብሔር ያለ ኃጢአት የሆነ ነው (ፊል.





3:20-21):: ኃጢአት የሌለበትና ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ሕብረት ስላለው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ሲፈልግ መስዋዕቶችና ቤተ መቅደስ አያስፈልጉትም:: ደህንነት በክርስቶስ ደም አማካኝነት ወደ ፍፁምነትና ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዘላለም ሕብረት ከመራ ዘላለማዊና ክብር የሞላበት ደስታ ይኖራል ማለት ነው:: ስለዚህም ዮሐንስ በራዕይ ወደ ፊት ስላለው ዓለም (አዲስ ሰማይና ምድር) መቅደስ አልተመለከተም:: በሰማይ ስላሉት ስለዳኑት ሲናገር ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርሷ ዘንድ አላየሁም በማለት ድፏል (ራዕ. 21:22):: የዳኑትና የተነጠቁት አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ናቸው፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ውስጥ ነው (ዮሐ. 14:20፤ 17:21-24):: እንደዚህ ያለው ሕብረት ወደ ፍፅምና ሲደርስ የመገናኛ ቦታ፣ በቤተ መቅደስ ያለው አምልኮ ወይም መስዋዕቶች መታሰቢያቸው ሁሉ ይጠፋል::

### መግለጫ ክፍል 4:

## በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሰባቱ ዘመናት

የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹትን የተለያዩትን ዘመናት መለየት ካልቻልን ልንረዳው አንችልም:: በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የእውነትን ቃል በቅንነት መናገር ብሎ የጻፈለት ቃል አስፈላጊ ነገር ነው (2. ጢሞ 2:15):: መፅሐፍ ቅዱስ ትጉህ ለሆነ የመፅሐፍ ቅዱስ ተማሪ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ መፅሐፍ አይደለም:: ምክንያቱም ግልፅነት ባለው መንገድና ሥርዓት ባለው መገለፅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ ነው::

በዚህ ዓለም በእግዚአብሔር የማዳን ሒደት ውስጥ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ዘመናት» ብለን የምንጠራቸውን ጊዜያት እናገኛለን:: (Dispensation) ዘመናት የተባለው ቃል ከግሪክና ከላቲን የተወሰደ ነው:: የግሪኩ ኦኮኖሚያ (Oikomia) የተባለው ቃል ዘጠኝ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል:: በላቲኑ ቨልጌት ዲስፐንሳቲዮ (Dispensation) ተብሎ ተተርጉሟል:: መጋቢ ወይም ቤት ሰብ ማስት ነው:: ከበስተኋላ ያለው ሀሳብ እግዚአብሔር የደህንነትን ታሪክ እንደ ቤት ሐላፊ ወይም መጋቢ ሆኖ የሚያካሂድ ነው ማለት ነው:: ይህ ኦኮኖምያ ወይም የደህንነት መጋቢነት በኤፌሶን 1:10፤ 3:2-9 ፤በቆላ 1:26 እና 1ጢሞ 1:4 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የአዲስ ኪዳን ቤት ክርስቲያን ምስጢር መጋቢ ነበር:: በጠቅላላው የማዳንን ታሪክ ሂደት ስንመለከት የተለያዩ ሰባት ዘመናትን መለየት እችላለን:: እነርሱም:-

1ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የመጀመርያው ዘመን «የፍጽምና ዘመን»

2ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሁለተኛው ዘመን «የሕሊና ዘመን»

3ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስተኛው ዘመን «የመግዛት ዘመን»

4ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አራተኛው ዘመን «የተስፋ ዘመን»

5ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አምስተኛው ዘመን «የሕግ ዘመን»

6ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ስድስተኛው ዘመን «የጸጋ ዘመን»


7ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሰባተኛው ዘመን «የሰላም ዘመን»ናቸው::





### 1. ድንግልና


#### ዘፍ 1 እስከ 2




ከውድቀት በፊት ሰው ኃጢአት በሌለበት በፍጽምና ዘመን ኖረ በአዳምና በሔዋን እንደዚሁም በአካባቢያቸው ባለው ተፈጥሮ በፍጹም ኃጢአት አልነበረባቸውም:: በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ሕብረት ፍጹም ያልታወከና ከጥፋትም ነጻ የሆነ ነበር:: ይህ ዘመን ስምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማንም አያውቅም:: ነገር ግን የሰው በደል በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል በጣም ሰፊ የሆነ መለያየትን አመጣ:: የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ሕብረት ያጡ ብቻ አልነበረም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ክብርም የጎደላቸው ሆኑ (ሮሜ 3:23) ኃጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ የፍጽምና ዘመን አከተመ::

### 2. የሕሊና ዘመን

#### ዘፍ.4:7 ሮሜ 2:12-16




ከፍፅምና ዘመን ቀጥሎ የሕሊና ዘመን ቀጠለ:: ከሰው ውድቀት በኃላ ማንኛውም ሰው ደህና አድረጎ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት አወቀ ዘፍ 3:22 ይህ ውስጣዊ የሆነ እውቀት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው:: ኃጢአተኛው ከበደል ነፃ አይደለሁም ማለትም አይችልም:: መፅሐፍ ቅዱስ ማንኛውም ሰው ሕሊና እንዳለው ይናገራል (ሮሜ 2:12-16):: በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ ማንኛውም ሰው ስለ ሠራው መልስ ይሰጥ ዘንድ በእግዚአብሔር ይጠራል::


ሰው መልካሙንና ክፉውን የማወቅ ነገሩ እስከ አሁን ያልተሰወጠ ስለሆነ ሰብዙ ሺህ አመታትም በሕሊና ዘመን ውስጥ ኖረዋል:: በደህንነት ታሪክ ውስጥ ይህ ዘመን ያበቃው በጥፋት ውሀ ፍርድ ጊዜ ነው:: በዚያን ጊዜ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ እዲገስፀው ወደማይፈቀድለት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር:: በክፋት የተሞላ ሆኖ ነበር (ዘፍ. 6:5):: የአመፅ ከፍታው በጣም ያየለበት ጊዜ ስለነበር እግዚአብሔር

ሰውን በመፍጠሩ እስከ መፀፀት ደረሰ አድርሶት ነበር:: (ዘፍ. 6:6):: ስለዚህም ከስምንቱ ከኖህ ቤተሰቦች በስተቀር መላው ዓለም በጥፋት ውሀ ጠፋ:: ኖህ በእግዚአብሔር ስላመነና በአስቸጋሪው ጊዜ እንኳን ታማኝ ሆኖ ስለቆመ እነዚህ ቤተሰቦች ለመዳን በቁ::

ከኖህ ሶስቱ ልጆቹ ከሴም፣ ከካምና ከያፌት ሦስቱ የሰው ዘሮች ተወለዱ እነርሱም ሴማውያን (ሴሜቲክ)፣ ከነዓናውያንና (ሐማይት) ያፌታውያን ናቸው::

### 3. የመግዛት ዘመን

**ዘፍ 9:6**




ከጥፋት ውሀ በኋላ ጌታ ከኖህ ጋር አዲስ ዘመን ጀመረ:: ይህም የመግዛት ዘመን የሰው ባለ ሥልጣንነት ዘመን ነበር:: የዚህ ዘመን ዋናው መሠረት ሕጉ ነበር:: *የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈሰሳል፣ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና (ዘፍ. 9:6)::*

ይህም ማለት ማንኛውም ሰው ይህን ሕግ የሚጥስና ሰውን የሚገድል በእግዚአብሔር ላይ አደጋ እንደጣለ ይቆጠራል፣ ምክንያቱም ሰው በእግዚአብሔር መልክ ስለተፈጠረ ነው (ዘፍ. 1:27):: ይህን ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ ሰውን ባለ ሥልጣን አድርጎ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነገር ሆነ:: ሰዎች በአንድነት መኖር እንዲችሉ በሥልጣን ተዋረድ የመግዛት አከሄድ ተፈጠረ መንግስት ተቋቋመ:: በገዢና ተገዢ ሂደትሌሎች ሃይሎች የሚገዙለት ሥልጣን ተመሰረተ:: ለምሳሌ መንግስት አመፀኞችን የመቅጣት ሥልጣን አለው:: ምክንያቱም በመንግስት ላይ ማመፅ (ለመንግስት ስልጣን አለመገዛት ማለት ነው) በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው:: ምክንያቱም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸውና::

ይህ መለኮታዊ ትዕዛዝ በሮሜ መልዕክት እንደምንማረው በአዲስ ኪዳንም የፀና ነው (ሮሜ 13:1-7):: ጌታ ኢየሱስ በመላው ዓለም ላይ የነገስታት ንጉስ ሆኖ በሺሁ ዓመት እስከሚገዛበት ጊዜ ድረስ ለስልጣን የመገዛት ነገር የማይለወጥ ነገር ነው::

ከዚህ በኋላ እውነተኛው አገዛዝ (የእግዚአብሔር መንግስት) በምድር ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ይገዛል:: ይህም ማለት ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፍፁማዊ አገዛዝ ሥር ይሆናል ማለት ነው::






ነገር ግን ይህ የመግዛት ዘመን በደህንነት ታሪክ ውስጥ ያበቃው በባቢሎን ግንብ ግንባታ ጊዜ ነው:: የሰው ዘር እንደገና አመፀኛ ሆነ:: የራሱንም ስም ለማስጠራት ጥረት አደረገ (ዘፍ. 11:1-9):: ሰዎች በራሳቸው ኃይል የሱማያውያን አገዛዝ ሂደት ለማወክ እድማ መቱ:: በእግዚአብሔር የተመሰረተውም የሕግ አገዛዝ የማይሰራ ሆነ፣ ምክንያቱም ይህ አመፀኝነት በሥራ ላይ እንዳይውል የሚገታው ኃይል በሰው ዘንድ አልነበረም::

ነገር ግን ይህን ዕድቅ ያልሆነውን ዕቅዳቸውን ጌታ ወደ ፍፃሜ አመጣው:: እግዚአብሔር ቋንቋቸውን በመደበላለቅ በምድር ላይ ተበታትነው በራሳቸው መንገድ እንዲሔዱ አደረጋቸው (ሐሥ. 14:16):: ስለሆነም በማዳን ታሪክ ውስጥ የመግዛት ዘመን ወደ ፍፃሜው መጣ::

### 4. የተስፋ ዘመን

**ዘፍ.12:1-3 ገላ 3:16**





አራተኛው ዘመን የጀመረው በአብርሃም መመረጥ ነው:: አብርሃም በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ በአንድ ነገር የተለየ ነበር:: በእግዚአብሔር ያመነ ሰውና እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ሰው ነበር (ዘፍ. 15:6፤ ሮሜ 4:3)::

አብርሃም የእስራኤል ሕዝብ አባት ሆነ:: በዚህ ምክንያት ከእግዚአብሔር ሦስት ተስፋዎችን ተቀበለ (ዘፍ. 12:1-3):: በመጀመሪያ ምድርን (የእስራኤል ምድር የሆነችውን) በሁለተኛ ዘሩ ትልቅ ሕዝብ እንደሚሆንና (የእስራኤልን ሕዝብ) በሶስተኛ ከዚህ ምድርና ሕዝብ ተስፋ የተገባለት መሲሁ የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ቀን እንደሚነሳ ነው:: እነዚህ ሦስቱ ተስፋዎች ቀጣዩና አዲሱ ዘመን ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ይገልፃሉ:: ሦስቱም በክርስቶስ ላይ የሚያተኩሩ ስለሆኑ እንደ ገላ 3:14-18 በክርስቶ የመጀመሪ መምጣት የተፈፀሙ ሆኑ::

የተስፋው ዘመን በሌላ ውድቀት ተፈፀመ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከቄሳር በስተቀር ሌላ ንጉስ የለንም ብለው እንዲሰቀል ለሮማውያን አሳልፈው በሰጡት ጊዜ መሲሁን መቃወማቸው ነበር::(ዮሐ. 1:11፣ 19:13-15፤ሐሥ.3:14-15፤ሉቃስ 19:14)

### 5. የሕግ ዘመን

### ሮሜ 10:4፤ ገላ. 3:19-26





የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሕግን ሰጣቸው:: አስርቱ ሕግጋት በሲና ተራራ ላይ በታወጁ ጊዜ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የሕግ ዘመን የተባለው አዲስ ዘመን ጀመረ:: ይህ ዘመን ከሌሎቹ ዘመናት ጋር ሲነፃፀር የጸጋ ዘመን ከተባለው ዘመን ጋር ሰብዙ መቶ አመታት ጎን ለጎን ሄዷል:: መፅሐፍ ቅዱስ በማዳን ታሪክ (Salivation History) ውስጥ ስለ ኃጢአት ሕግ ገባ ወይም ተጨመረ የሚለው ስለዚህ ነው (ሮሜ 5:20፤ ገላ. 3:19):: ኃጢአትን በሕሊናችን ማወቅ የምንችለው በሕግ በኩል ብቻ ነው (ሮሜ 3:20):: የዚህ የ5ኛው ዘመን ትልቁ ዓላማ ሰው ተስፋ ቢስ የሆነ፣ ደህንነት የሚያስፈልገው መሆኑን የሚያሳይ ነው:: አንድ ሰው ከሕግ አንዱን ቢተላለፍ በሁሉም በደለኛ ይሆናል (ያዕ. 2:10):: ስለሆነም የእግዚአብሔርን ፅድቅ መድረስ አይችልም:: ስለዚህ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ሞግዚት ሆነ (ገላ. 3:24):: የእግዚአብሔር ጽድቅ ሕግ በሚጠይቀው በሕግ ሥራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጽድቅ በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የሚገኝ መሆኑን ያስተምረናል (1ቆሮ.1:30) መፅሐፍ ቅዱስ እርሱ የሕግ ፍፃሜ መሆኑን ያረጋግጥልናል::በእርሱ የሚያምን ሁሉ ፃድቅ ነው (ሮሜ 10:4)::

ምንም እንኳን ሕግ «ተፈፀመ» በሚል አነጋገር በመስቀል ላይ በጮኸው በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመ ቢሆንም እስራኤል መሲሁን አላወቀችውም (ዮሐ. 19:30):: ቢያውቁት ኖሮ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር (2ቆሮ. 2:8) ይህ የሕግ ዘመን መሲሁን በመቃወም ተፈፀመ (ማቴ. 23:37-39)::

### 6. የምህረት ዘመን

### 2ቆሮ 6:1-2፤ ሐሥ. 4:12




ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመጣ፣ ከተሰቀለ፣ ከሙት ከተነሳና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እግዚአብሔር በጣም የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የሆነውን የጸጋ ዘመን አስገባ (ኤፌ. 1:1-10፤ 3:2-9) ይህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደሆነም ቀደም ብለን አውቀናል:: እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ወሰን የሌለውን የጸጋ ጊዜ





በወንጌል መስበክ በኩል ለዓለም ሰጥቷል:: በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ማንኛውም ሰው በበጉ (በኢየሱስ) ደም በኩል ለዘላለም የሚድን ይሆናል::

ይህ የጸጋ ዘመን በበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተጀመረ (ሐሥ. 2:1-41):: በቤተ ክርስቲያንም መነጠቅ ጊዜ ያከትማል (1ተሰ. 4:13-18) ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልዕክት ስለ ደህንነት ቀን ሲፃፍ ስለዚህ ለሁሉም ስለተሰጠው የፀጋ ጊዜ መናገሩ ነበር (2ቆሮ 6:1-2) ለሁለት ሺ ዓመታት ያህል በጸጋ ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው ያለነው፣ ዛሬም ቢሆን ጌታ የሚድኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየጨመረ ነው ያለው (ሐሥ. 2:47):: ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ዘመን እንዳለፉት ዘመን በጥፋት ይፈፀማል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ መነሳት ለሺዎች ዓመታት ወንጌልን ሰምተው ነገር ግን በክርስቶስ የተሰጠውን ደህንነት በተቃወሙት ላይ ለፍርድ ነው:: በዚህ ምትክ ሰዎች ሰይጣንን አውሬውን ያመልካሉ:: በራዕይ 13:16 666 የተነገረለትን ቁጥር ያለውን የአውሬው ምልክት በቀኝ እጃቸውና በግንባራቸው ሲቀበሉ የሰይጣንን ማህተም መቀበላቸው ነው:: ይህ ሲከናወን ሊያመልጡበት የማይችሉትን የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳቸው ላይ መጥራታቸው ነው:: ይህ የጸጋ ዘመን ከየትኛውም በምድር ላይ ከነበሩት ዘመናት የበለጠ በአስፈሪ ፍፃሜ ያበቃል::

### በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ አንቀጽ መካከል ያለ አጭር ጊዜ

### «አስፈሪው የታላቁ መከራ ዘመን»


የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምድር የምትነጠቅበትን ጊዜ ሰዎችም ሆኑ የሰማይ መላዕክት አያውቁትም (ማቴ. 24:23):: ነገር ግን አንድ የተረጋገጠ ነገር አለ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በንጥቀት ጊዜ ከአማኞች ጋር ይህችን ምድር ይተውና ወደ ሰማይ ይመለሳል:: በዚያ ጊዜ ሰዎች በንስሐ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮችና የሰማያዊ አባት ልጆች የሚሆኑበት የፀጋ ዘመን ያበቃል::

ቀደም ባለው ምዕራፍ ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ (በጸጋ ዘመን) በእስራኤልና በመላው ዓለም ላይ አጭር የሆነ የፍርድ ጊዜ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ የክርስቶስ ተቃዋሚ ገደብ የለሽ የሆነ ታላቅ ብጥብጥ በምድር ላይ እንዲያደርግ ይፈቀድለታል:: ይህ ጊዜ ባያጥር ኖሮ ማንም የማይድንበት አስቸጋሪ ይሆን ነበር (ማቴ 24:22)::

ይህ አስፈሪው የክርስቶስ ተቃዋሚ ዘመን እያንዳንዳቸው ሦስት ዓመት ተኩል ለሆኑ ሁለት ጊዜያት የተከፈለ ነው:: ይህም የምህረት እባት ምን ያህል አፍቃሪ እንደሆነ ያረጋግጥልናል:: ለሰዎች ዓመታት ከቆየው የፀጋ ዘመን በኋላ ለሰባት ዓመት የሚቆይ የፍርድ ዘመን ይከተላል:: በዘመናት ሁሉ ከነበሩት ይህ አስቸጋሪ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ያከትማል:: ጌታ በኃይልና በታላቅ ክብር ሲገለጥ የክርስቶስ ተቋዋሚ፣ ሀሰተኛው ነቢይና ሰዎች ሁሉ ይፈረድባቸዋል:: ነገር ግን እስራኤል ትድናለች፣ ምክንያቱም በመጨረሻ መሲኋን ትቀበላለችና::

## 7. የሰላም ዘመን

### ኢሳ 11:1-9፣ መዝ(72)1-17




ለእስራኤልና ለዓለም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ጊዜ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሰባተኛው ዘመን «የሺህ ዓመት ዘመን» የመሲሁ የሰላም ዘመን ተብሎ የሚጠራው ይጀምራል::

በዚህ ዘመን በክርስቶስ በመስቀል ላይ የተፈፀመው የማዳን ሥራ በፍጥረት ሁሉ ላይ የሚሠራ ይሆናል:: እርግማን በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮም ላይ ወድቋል/ደርሷል/:: ምድር ሾህና እሜክላ ታበቅላለች ሰውም በድካምና በጥረት ይሰራል (ዘፍ. 3:17-19):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን እርግማን ከፍጥረት ሁሉ ላይ ለማንሳት የሾህ አክሊልን ደፋ:: በሺሁ ዓመት ወንጌል የሚሰማ ብቻ ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ሲሰራ የሚታይም ይሆናል:: በአብዛኛው ከኃጢአት እርግማን ነጻ ሲወጣ በመላ ዓለም የተገለፀ ይሆናል (ሮሜ 8:19-25) የሰላም ንጉስ በምድር ላይ ሲገዛ እውነተኛው ሰላም መላ ዓለምን ይገዛል:: (በፖለቲካዎች ሁሉ ላይ እንኳን):: ይህ በምድር ላይ እጅግ አስደናቂ ዘመን ይሆናል:: የሰው ዘርም አስቀድሞ በገነት ይኖር እንደነበር ይኖራል:: ሆኖም ይህ ዘመን በሰው ኃጢአት ምክንያት ያከትማል ሰይጣን ለአንድ ሺህ ዓመት ከታሰረ በኋላ ከስራቱ ይፈታል:: እንደገና አብዛኛውን የሰውን ዘር እግዚእብሔርንና ክርስቶስን እንዲክዱት በማድረግ ይመራቸዋል:: ምንም እንኳን ሰው በሺው ዓመት በመለኮታዊ በረከቶች በደስታ እየኖረ መሲሁን ቢያየውም፣ ሁሉን በሚችለው ላይ ወደሚደረገው ግልፅ አመፅ





ራሱን አሳልፎ በመስጠት ራሱን ወደ ስህተት ይመራል:: ለጥፋትና ለኩነኔ ዲያብሎስን ይከተላል (ራዕ. 20:7-10)

እግዚአብሔር በተለያዩት ዘመናት ውስጥ ተራ በተራ ፍፁምና ዘላለማዊ የሆነውን ደህንነት ገልፇል:: ይህም ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያመለክቱ በተለያዩ ተከታታይ መገለጦች የተከናወነ ነው:: የኃጢአት ጨለማ በሰው ላይ ከወደቀ በኋላ የፀጋ ፀሐይ ቀስ በቀስ መውጣት ጀመረ:: የዓለም ደህንነት የንጋት ብርሃን ሙሉ ወደ ሆነው የመዳን ቀን እስከሚደርስበት ጊዜ ድረስ ከቀራንዮ መስቀል ብርሃኑ እየጨመረና እየጎላ የሚንፀባርቅ ሆነ (ምሳ. 4:18፤ 2ቆሮ 6:2):: ከራዕይ 21 ጀምሮ ወደ ፊት ባለው ክፍል ኃጢአት፣ ሞትና የክፋት ምንጭ የሆነው ዲያብሎስ ለዘላለም የተሸነፉ ይሆናሉ:: ከዚህ በኋላ የጊዜ ቆጠራ ስለማይኖር ዘመን ወይም ዓመታት አይኖሩም:: ደስታና ክብር የተሞላበት ዘላለምነት ብቻ ይኖራል:: የዳኑት በሙሉ ከእግዚአብሔር ልጅ ከተወደደው አዳኝና ከሙሽራው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራሉ (ራዕ. 22:1-5):: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በዘመናት ሁሉ ያመኑበትን፣ በብዙ መዝሙሮች የዘመሩለትንና ያመሰገኑትን በዘለዓለሙ አምልኮ ይፈፅሙታል::

ድካሞቼና ፈተናዎቼ ሲያበቁ
በዚያች ውብ ጠረፍ በደህና ስደርስ
ከማመልከው ጌታ አጠገብ ስገኝ
በዘመናት ሁሉ ደስታ ለእኔ ይሆናል::

ያ ነው ክብሬ የሚሆን ቻርለስ ዘ ገብርኤል 1956-1952 አዝማች ኢየሱስ ክርስቶስ *«በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሔዳለሁ::» (ዮሐ. 14:2)*
*«አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ::» (ዮሐ. 17:24)*
*«ዓይኖቼ ንጉሱን በውበቱ ያዩታል::» (ኢሳ. 33:17)* ይላል::

**«ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም::»**
**(ማቴ 17:8)**

# ምሥጋና

ከሁሉ አስቀድመን በዚህ በዘመነ ፍጻሜ በመንፈሱ በመካከላችን ተገኝቶ ይህንን እውነት ለእኛ ያካፈለንን እግዚአብሔርን ከልብ እናመሰግናለን:: እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔር መጠቀሚያው ሆና ይህንን መጽሐፍ በጀርመንኛ ቋንቋ ያዘጋጀልንን አባታችንንና ወንድማችንን ፓስተር ዮአኪም ላንገሐመርን ጌታ ይባርከው እንላለን:: ይህ « ይህች ዓለም ምን ትሆናለች» በሚል ርዕስ ብዙ ቁም ነገሮችን· ይዞ ተዘጋጅቶ ከብዙ ድካም በኋላ በእግዚአብሔር እርዳታ ለአንባቢያን እንዲበቃ የብዙ ወንድሞችና እህቶችን ተሳትፎ ጠይቋል:: እንደ ሰው ፀትኛውንም ዓይነት መጽሐፍ ቢጽፍ የእኛ እንጂ የእኔ ብቻ ለማለት አይደፍርም:: ምክንያቱም በውስጡ የሰዎችን ጠቃሚ ሃሳቦች፣ አስተያየት፣ ምክርና እርማት ማግኘቱ የማይቀር ነውና:: አሁንም ይህንን መጽሐፍ ለናዘጋጅ ከጀርመንኛ ወደ እንግሊዘኛ ትርጉም ወ/ም ማቲው ወከር፣ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ወ/ም ሽመልስ ረጋ፣ጽሑፉን በማረም መጋቢ ተኩ ከበደ፣ ወ/ም በድሩ ሁሴን፣ ወ/ም የራስሜ ጋሳቲስና ወ/ም ሽመልስ ረታ በኮምፒዩተር የጽሬት ሥራ የተባተፉትን እህት አባይነሽ አርጋንጉንና እህት ዲና በላይነህን ጌታ ይባርካችሁ እያልን ለበርካታ ዓመታት ከጀርመን ወደ ኢትዮጵያ እየተመላለስን ይህን መጽሐፍ በከፍተኛ ድካም በዚህ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ፣ ለማድረግ ያገዘንን እግዚአብሔርን በድጋሚ ከልብ እናመሰግናለን:: ክብር ለእግዚአብሔር እስከዘላለም ዓለም ይሁን!!

<u>አዘጋጆች:-</u>
ሚሽነሪ ሽመልስ ረታ እና ዮታ ረታ